
በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል

ሐምሌ ፲፱፻፹፮
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፪

$2.75

ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም

# ላንዳፍታ




## በዚህኛው እትም

- ❖ በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች
- ❖ ኑሮ በአሜሪካ
- ❖ አዳምና ሔዋን
  አላለልኝ ይሆን
  ዕጣዬ
- ❖ ልብ ወለድ
  የዴብራ ጦስ

# LANDAFTA

*An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine*

*(Amharic is the official language of Ethiopia)*

July, 1994 Vol. 3. No. 2

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ውጫ

# CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት - (ወርቃየሁ)

6 እንዲህ ሆነ
ዜናዎች ከኢትዮጵያ (ከኢትዮጵያ ወኪል)
ኤርትራ ኢትዮጵያውያንን ከአሰብ አባረረች
ባለከላሽኮቹ መነኩሴ
ድርቅና ረሀብ በኢትዮጵያ
የኢትዮጵያ ወታደሮች ሩዋንዳ ሊዘምቱ ነው

የጒሣ ፍጅት በሩዋንዳ (ሰይፉ መኩሪያ)
ጥንቅር (ከወርቃየሁ)

21 ልብ ወለድ
"የዴብራ ጦስ" (ገረሱ)

25 ኑሮ በአሜሪካ
"በእምነት ዙሪያ መሰባሰብ"

32 አዳምና ሔዋን
"ጓደኛ ለሚፈልጉ"
"አላለልኝ ይሆን!" (ትዝታ አለብኝ)
"ዕጣዬ" (አብረኸት)
"እውነትም ጣጤ" (ሀይሉ ሮበሌ)

41 የአበው ቅርስ
ቅኔ፤ ተረትና ምስሌዎች
"ተቆጥቶ የሚያስታርቅ ሽማግሌ" (አብዩ)
"ባላገርና ፖለቲካ"

44 የግጥም ጉባኤ
"የጥቁር ግሥላ ማንዴላ" (መሪጌታ ልሳኑ)

45 ቢስቁም ባይስቁም

46 ስፖርት (የፎቶ መግለጫ)
የሳንፍራንሲስኮ፣ የአትላንታና የቺካጐ ቡድኖች

47 ጨዋታና ሰንጠረዥ




ድርቅ በኢትዮጵያ



የአባ ገ.መስቀል ኢንተርቪው



የአዲስ አበባ ላስቲክ ቤቶች

---

የሽፋን ፎቶ - አባ ገብረ መስቀል መኩሪያ

---


"ላንዳፍታ" የግል መጽሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።
©COPYRIGHT LANDAFTA 1994

ላንዳፍታ
ሐምሌ ፲፱፻፹፮
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፪
LANDAFTA
July, 1994 V. III - No. 2

*Publisher/Editor*
*Mekonnen Gessesse*
*Contributing Editors*
*Girma Zegeye*
*Abera Sisay*
*Editorial Advisors*
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
*Editorial Assistant*
Woinishet Bekele

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Teslaye B. (Hoddo)
Yeshi Gessesse
Daton, OH
Rainbow Cafe
Denver, CO
Tibeb Taye
Dallas, TX
ET. Beauty Supply
L.A., CA
K RAH Market
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Addis Cafe
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Tampa, FL
Ibex Ethiopian restaurant
Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market
Indian Super Market
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

*Landafta*
*P.O.Box 49301*
*Atlanta, GA 30359*
Phone/Fax *(404)728-9122*

# ከአዘጋጁ

እንዴት ከረማችሁ። ይኸው ደግሞ ወር ቆጥረን ብቅ ብለናል። ምን ይዛችሁ ትሉ ይሆናል። አምዶቻችን ብዙ ነገር አዝለዋል። አገር ቤት ተሻግረን በወኪላችን አማካይነት ያገኘናቸውን ዜናዎች ይዘናል። "በእምነት ዙሪያ መሰባሰብ" በሚል ርዕስ ከአትላንታው ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ካህን ከአባ ገብረመስቀል መኩሪያ ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ ለ"ኑሮ በአሜሪካ" ትኩረት ሰጥተነዋል። የፎቶ ዜናዎችን ጀምረናል። ከሩዋንዳው እልቂት ብንማር ብለው ሰይፉ መኩሪያ አጠናቅረው የላኩልን ዘገባም ቀርቧል። "ባላገርና ፖለቲካ" የተሰኘው በኢትዮጵያ ወኪላችን አማካይነት የተላከልንን ጽሑፍ ይዘናል። ሌሎቹ እንግዲህ ቀደም ሲል በይቀጥላል ያለፍናቸው የገጠመኝ ታሪኮች ናቸው።

ውድ አንባብያን፤

ሌላም ዜና አለን። ሰላም ሰፍኖ፣ ጥሩ አስተዳደር አግኝቶ በሥርዓት ምርቱን አምርቶ ለመበልፀግ ያልታደለው ወገናችን ይኸው ደግሞ ለሌላ የከፋ ረሀብ ተጋልጧል። መቼ ይሆን ችግሩ ሲደርስ ብቻ ጊዜያዊ ዕርዳታ ለመፈለግ ከሚራኮት፤ ዘላቂ መፍትሔ ለመፈለግ የሚጥር መንግሥት ወገናችን የሚያገኘው? የረሀቡን ሁኔታ በተመለከተ ሰፋ ያለ ዘገባ ይዘን ቀርበናል። በረሀብ የተጎዱ ወገኖቻችን ሁኔታና በተጨማሪ በአዲስ አበባ "የጎዳና ላስቲክ ጎጆ ኑሮ"ን የሚያሳዩ ፎቶዎች አቅርበንላችኋል። ወርቃየሁ ከአ.አ. "እኛ ይህን እንመስላለን" ብለውናል። "አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳልና" የወገናችን ረሀብ የኛ ረሀብ፤ የወገናችን መጎዳት የኛ መጎዳት ነውና እኛም በውጪ ያለን ትንሽ 'ያደለን' ስደተኞች ወገኖቹ አስተዋጽዖአችንን ለማበርከት ወደ ኋላ እንደማንል ይታወቃል። የምንሰጠውን እርዳታ ለሕሊናችን ዕረፍት እንዲሰጠን ብቻ በማለት መግቢያ መውጫውን በማናውቀው ሁኔታ ከሆነ ደግሞ ወገናችንን ያድን ያልነው ወገናችንን እንዳይጎዳው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። በሕዝብ ሰቆቃና ችግር ድራማ እየሠሩን ለየጉዳያቸው እየተሯሯጡ "ዕርዳታ አምጡ" የሚሉትን በቅድሚያ እንመርምራቸው። ቀደም ሲል ለረሀብተኛው ተብሎ በብዙ አቅጣጫ የተሰበሰበው ዕርዳታ ለሌላም ነገር ውሏል የሚል ሀሜት ሰምተናል። የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። እና ዕርዳታ ለመስጠት በየኮሚኒቲያችን፣ በየእምነት ማዕከላችን፣ በየቡድናችን በምንዘጋጅበት ወቅት "ዕርዳታውን በማን በኩል ብንልክ በትክክል ለተራበው ወገን ይደርሳል?" የሚለውንም አብረን ማጤን ይኖርብናል። በተጨማሪም የኮሚኒቲ ማህበራት፣ የእምነት ማዕከላት (ቤተክርስቲያኖችና መስጊዶች)፤ ሌሎችም ይህን የከፋ ረሀብ ይፋ በማድረግ በያላችሁበት ዕርዳታዎችን እንድታስተባብሩ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

"በፍቅር፤ በሰላም በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥና መቻቻል"
የሚለው መርሆአችን ሁሌም እንደተጠበቀ ነው፤
የዕድገት መሠረቱ እሱ ነውና።

*Landafta is an independent magazine published in Amharic bi-monthly. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ረሀብ ቀን አይሰጥም !!

## እንዲህ ክፉ ነው







ከሞት ጋር የተፋጠጡ ወገኖች

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

ለመሆኑ እንደምን ከረማችሁ? ይሄ የፈረንጅ አገር ኑሮ ሩጫው ልብ ያወልቃል ይባላል። ኑሮ ከብልሃቱ እየገጠመላችሁ ይሆን? እኛ ደህና ነን። እግዚአብሔር ይመስገን አከራረማችን ደግ ነው።

በሚያዝያ ፋሲካ ጮማ ቆርጠናል፣ እንደአቅሚቲ ወዝ ያላት ነገር ቀምሰናል። ግንቦት 20ን በሰልፍ ወጥተን ለዓመት የሚበቃንን ዲስኩር ስንሰማ ውለናል። ሰሞኑን ደግሞ ድርቁም ረሃቡም እየጠና ስለመጣ ወደ እናንተው ዘንድ ወደ ፈረንጆቹ አገር ለመምጣት DV-1 በምትሉት ሎተሪ ላይ እየተረባረብን ነው።

ለፋሲካ የየአቅማችን ሞካክረናል። የቻለና አቅም ያለው ሰንጋ ጥሏል ሙክት አርዷል። ያም ያላደረሰው ከማን አንሼ ጠቦት ገዝቷል። ለሙክትና ለጠቦት እጁ ያጠረበት ቅርጫ ወስዷል። ሁሉም ያልሆነለት፣ ያልሞላለት ትንሽ ቅንጣቢ ቢጤ ገዝቶ አፉን አሟሽቷል። ተመሳስሏል።

ለፋሲካ በየቤቱ ቄጠማ ተጎዝጉዞ፣ ኮረዳዎች እንሶስላ ሞቀው፣ አዛውንቶችና ጎልማሶች የክት የአገር ባሕል ልብሳቸውን ለብሰው እያንዳንዷ ጎጆ የምትችለውን ያህል ተሰናድታለች። ዶሮውን፣ ቅቤውን፣ ዕንቁላሉን፣ አይቡን፣ ልብስ፣ ጫማ፣ ሽቶ ወዘተ ለመግዛት ሁሉም እንደአቅሙ በሽመታ ተራውጧል። ፕሮግራም ብሎ ነገር የማያውቀው የአበሻ ኪስ በአንዲት ሰሞን ሽመታ ብቻ ተሟጦ እንደማይሆን ተረጋግጧል።

ከቅባት ርቆ ሁለት ወር የከረመ አንጀት በክትፎው፣ በቁርጡ፣ በዱለቱ፣ በቅቅሉ፣ በዶሮው፣ በዳቦው፣ በኬኩ ቁንጣን ተቀስፎ ሰንብቷል። በአናቱ ደግሞ ጠላው፣ ጠጁ፣ አረቄው፣ ቪኖው፣ ቢራውና ውስኪው በያይነቱ ተንቆርቁሯል። የባህር ማዶ ሙዚቃና ጭፈራ ያሰኘው ዘመናይም ከቢጤው ጋር ነጭ ላብ እስኪያልበው ተንፈራግጧል። ዘመድ አዝማድ ወዳጅ ለወዳጅ ተገባብዟል። የቻለም ሙክት አስጎትቶ ያልቻለው ድፎ ዳቦ አስይዞ አክፋይ ተያይቷል። የእኔ ብጤውም ቅልጥም የሞላበት የመረቅና የዶሮ ፍትፍት ጠግቦ እስኪተርፈው በልመና ኮሮጆው ሞልቷል። "የበግ ቆዳ ያለሽ" እያለ ከየሰፈሩ ቆዳ የሰበሰበ ነጋዴም ደህና ፍራንክ ቦጭቋል። የየሰፈሩም ማቲ እስኪበቃው ፊኛ ነፍቶ ቦርቋል። እጅ አልሰጥ ብሎ ያስቸገረ ላጤ ሁላ ከፋሲካ ማግስት ጀምሮ ሶስት ጉልቻ መስርቷል። በማነህ ማነህ አርባዎቹን ዓመታት ያገባደደው አባት ወንደላጤ ሁላ በስንት ጣር በተገኘች ሚስት ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ "የእኛ ሙሽራ የእኛ ሎጋ በአሳር ተገኘህ በፍለጋ" ተብሎለታል። ጠና ጠና ያሉ ብዙ ሴተ ላጤዎችም መቀነታቸውን ፈትተዋል። መቼም ደንብ ነውና "የቤተ ዘመዱ ይታያል ጉዱ። ሙሽሪት ልመጂ አይባባ ሆድሽ" ተብላለች። ቁርበት ምን ያንቋቋሃል ቢሉት ባያድለኝ እንጂ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ ያለው አይነት መሆኑ ነው።

ግንቦትን ጎጆ ወጪው በሰርግ ብዙ ባይደፍረውም ኢሕአዴግ ደግሞ በተራው ዋና ሠርገኛ ሆኖ ሰንብቷል። ሐውልት ሲያስመርቅ፣ ሲዘፍንና ሲያዘፍን ከርሟል። ከትግራይ ምድር ከደደቢት ተነስቶ አዲስ አበባ ከምኒሊክ ቤተ መንግስት የገባበትን ዕለት አደባባይ በሰልፍ ወጥተን አክብረንለታል። የፖለቲከኞቻችንን ረጃጅም ዲስኩሮች አድምጠናል። የግንቦት ሃያ ዲሞክራሲና ነፃነት አንጀቱን ያራሰው ወገን ምድሪቱን ከፍ በይ ልርገጥሽ ማለት እስኪቀረው በደስታ ፈንጥዟል። ካለውም የጎደለበት ደግሞ ወደሽ ነው ገጣቢት ንጉስ ታመሰግኚ ሆኖበት ቆሽቱ እያረረ ግንቦት ሃያን አክብሮ ውሏል። ጥሩው ነገር ሁለቱም አንድ ላይ ከአደባባይ ሲተዛዘቡ ውለዋል።

እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው ሆነብንና ገዥዎቻችን በተለዋወጡ ቁጥር ትርፍም ባይኖረን አዲስ በዓል አናጣም .... የንጉሡን የልደትና የንግስ በዓል ሺ ዓመት ይንገሱልን እያልን በሆታና በዕልልታ አክብረናል። በደርጉም ጊዜ መስከረም ሁለትና ሜይ ዴይን ክንዳችን እስኪዝል ኢምፔሪያሊዝምን በመፈክር ስናወድመው ውለን ነበር። ዛሬም ኢሕአዴግ አዲስ አበባ የገባበትን ግንቦት ሃያ በሆታ፣ በዕልልታ፣ በመፈክር በክበሮ እያሳመርነው ነው። ... ሰውየው የቆላ ሰው ነው አሉ። ለንግድ እያለ ከደጋው አገር ይመላለሳል። አንድ ቀን አንድ ወዳጁ ያገኘውና

"አንተ ቆለኛ ከየት መምጣትህ ነው?"
ይለዋል
"ለንግድ ደጋ ወጥቼ" ሲል ይመልሳል።
"ምን ሸጠህ መጣህ?"
"ጥጥ"
"ምን ገዝተህ መጣህ?"
"ጥጥ"
"እንግዲያ ትርፍህ ምንድን ነው?"
"ዘጥ ዘጥ" አለ አሉ።

የእኛም ትርፍ ቢታሰብ ብዙ ከዛ አይዘልም። ለመሆኑ እናንተስ እንዴት አከበራችሁት ይሆን? ይሄ የድንጋይ ዘመን ኑሮአችን ይናፍቃችሁ ይሆን ወይስ ትዝም አይላችሁም? እኛ ደብሮን ወደዚያው ወደ እናንተ ልንመጣ DV-1 የምትሉትን ሎተሪ በርብርቦሽ እየሞላን ነው። ፈረንጆቹስ ቢሆኑ በየጊዜው የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ እየላኩ ከሚቸገሩ እንደኛችንን ተጠቃለን እዚያው ብንመጣ ሳይቀላቸው ይቀራል?

እኛም ምን እንደምንመስል የላኩላችሁን ፎቶ እዩት፤ እናንተም ላኩልን ታዲያ!

በሉ ደህና ክረሙልን! በቸር ይግጠመን።

የናንተው ወርቃየሁ

# ይህን እንመስላለን !!



በአዲስ አበባ አውራ መንገድ የላስቲክ መኖሪያ ቤቶች



የጎዳና ታዳጊ ልጆች (ደቡብ ኢትዮጵያ)



አባወራው ከአዲስ አበባው ቤታቸው ጎን



ታዳጊ ሕጻናት በጎዳና ልመና አዲስ አበባ



የጎዳና ታዳጊ ሕጻናት (ወለጋ)

እንዲህ ሆነ

## ከኢትዮጵያ የላንዳፍታ ዜና ወኪል የተላከ

### ኤርትራ ኢትዮጵያውያንን ከአሰብ አባረረች

የአዲሲቱ ኤርትራ ግዛት በሆነችው አሰብ ውስጥ በትምህርትና በልዩ ልዩ ስራ ላይ የነበሩ 480 ያህል ኢትዮጵያውያን በሻዕቢያ መንግስት መባረራቸውን የተለያዩ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። ከተባራሪዎቹ ውስጥ እዚያው አሰብ ከተማ ተወልደው ያደጉ እናቶች፣ አባቶች፣ ተማሪዎችና ሰርቶ አደሮች እንደሚገኙበት ታውቋል። ከየመንገዱና ከየተሰማሩበት ታፍሰውና መታወቂያቸውን ተነጥቀው እንዲባረሩ የተደረጉት እነዚህ ኢትዮጵያውያን በአራት የጭነት መኪናዎች ተጭነው በወታደር አጀቢነት ከአሰብ 71 ኪሎ ሜትር ርቀት ለሚገኘው የኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ ሰራዊት መሰጠታቸው ታውቋል። ከተባረሩት 480 ኢትዮጵያውያን መካከል 98 ያህሉ ከብዙ መንገላታትና ስቃይ በኋላ አዲስ አበባ የደረሱ ሲሆን የቀሩት በተለያዩ ስፍራዎች ተበታትነው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ኢትዮጵያውያኖች ወደ ኢትዮጵያ ምድር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ችግራቸውን ለመንግስት ሹማምንትና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጭምር ለማቅረብ ያደረጉት ሙከራ ምንም ውጤት እንዳላስገኘላቸውና ያለ እንዳች መጠለያና የዕለት ደራሽ ዕርዳታ በሞት አፋፍ ላይ እንደሚገኙ በምሬት ይናገራሉ። አዲሲቱ ነፃ አገር ኤርትራ ካላት 3 ሚሊዮን ሕዝቧ መካከል ሁለት ስስተኛ የሚሆነው አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ እንደሚፈልግ የዓለም ምግብ ድርጅት መግለፁ ይታወሳል።

* * *

### የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአህድ) ፓርቲ ሆነ

በፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የሚመራው የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ወደ ፓርቲነት መሸጋገሩን አስታወቀ። ድርጅቱ ወደ ፓርቲነት እንዲሸጋገር ያስገደደው የሽግግር መንግስቱ በቅርቡ ያወጣው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ መሆኑን ጠቅሶ በኢትዮጵያዊነት አቋሙ እንደሚጠናከርና መጠሪያውም አንድ መንግሥት፣ አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ፣ አንድ ድንበር የሚለውን መርሁን ለማመልከት "መኢሕድፓ" ተብሎ መሰየሙንም አስታውቋል። "ኢትዮጵያን የማፈራረሱ ረቂቅ ስልት በባዕዳን ታቅዶ በኢትዮጵያውያን የአጭርና የረጅም ጊዜ ተግባረት ተጀምሯል" ሲል በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የኃላ ፖለቲካ የኮነነው የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያኖች ላይ የጥፋት ደመና ማንዣበቡን አመልክቷል። በተያያዘ ዜና በርካታ የብሔር ብሔረሰብ የፖለቲካ ድርጅቶች በወጣው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ መሰረት የተጠየቀውን መመዘኛ በማሟላት ወደ ፓርቲነት መለወጣቸውን ይፋ አድርገዋል። በአዋጁ መሰረት ሕጉ የሚጠይቃቸውን መመዘኛዎች አሟልተው በፓርቲው ያልተመዘገቡ ማናቸውም ድርጅቶች ሕጋዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንደማይችሉ በአዋጁ ተደንግጓል። እንደ አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት አዋጁም ሆነ በውስጡ የተመለከቱት መመዘኛዎች መንግስት የፖለቲካ ድርጅቶችን ለማገድ የተጠቀመበት ዘዴ ነው ሲሉ ይተቻሉ።

* * *

### መነኩሴው ባለክላሽ የቤተክርስቲያኗን ምዕመናንና ካህናትን አተራመሱት

ዕሁድ ሚያዝያ 16 ቀን 1986 ዓ.ም በዕለተ ሆሳዕና በቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን መቅደስ ውስጥ ከጠዋቱ በ12 ሰዓት አካባቢ አንድ የደብሩ መነኩሴ ተኩስ ከፍተው እንደነበር ከስፍራው ከደረሱት ዘገባዎች ታውቋል። መነኩሴው አባ ተክለ ብርሃን ከውነ የተባሉ ከዚህ ቀደም የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋይ የነበሩ ሲሆን በምንኩስና ልብሳቸው ውስጥ ሸሽገው ይዘውት በነበረ ክላሽ ጠመንጃ በተኮሱት ጥይት ለፀሎት የሄደው ሕዝብ ከቤተክርስቲያኑ ግቢ ለመሸሽ የተገደደ ቢሆንም በሰው ሕይወት ላይ የደረሰ አንዳችም ጉዳት አለመኖሩ ተዘግቧል። በስነ ስርዓት ጉድለት ምክንያት ከስራ ታግደው የነበሩት እኚህ መነኩሴ የጥቃታቸው ዒላማ በቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪዎች ላይ እንደነበርም ለማወቅ ተችሏል። መነኩሴው በቁጥጥር ስር በዋሉበት ወቅት ከክላሽንኮቭ ጠመንጃው ሌላ አንድ ሽጉጥና አንድ ቦንብ የተገኘባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በተያያዘ ዜና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ-ስብከት ጳጳስ በሆኑት በአቡነ ቶማስ መኖሪያ ቤት ግቢ ላይ በትንሣኤ በዓል ዕለት ቦንብ መወርወሩን አንድ የዜና ምንጭ ዘግቧል። በፍንዳታው የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ከመበጣጠሳቸውም በስተቀር በሰውም ሆነ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት የለም።

* * *

### የሊዝ ፖሊሲ ፀድቆ ወጣ፤ በአዲስ አበባ ተግባራዊ ሊሆን ነው

የአዲስ አበባ ከተማ የኪራይ ስሪት ፖሊሲ (ሊዝ) ፀድቆ መውጣቱንና ከሰኔ ጀምሮ ለተግባራዊነቱ እንቅስቃሴ እንደሚደረግ የክልሉ ምክር ቤት አስታውቋል። የአዲስ አበባ ከተማን በአምስት ዞኖች በመከፈል ለአንደኛ ደረጃ ቦታዎች በካሬ ሜትር 6000 ብር የሚያስከፍለው ይህ አዋጅ በአውጪው ምክር ቤት የከተማዋን የልማት ዕቅድ ለማሟላትና የነዋሪዎቿንም የኑሮ ደረጃ ሊያሻሽል

ይችላል ቢባልለትም በአብዛኛው የከተማ ነዋሪ ዘንድ ግን ድንጋጤን ፈጥሯል። የመሬት ባለቤትነት በመንግስት ይሁን ወይስ በግል የሚለው ጥያቄ እልባት ሳያገኝ ተግባራዊ ሊሆን የታወጀው የሊዝ ፖሊሲ የቤት መስሪያ ቦታን በ175 ካሬ ሜትር ገድቦታል። ከመነሻው ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞ የገጠመው የሊዝ ፖሊሲ በተለይም በንግድ ከሚተዳደረው ሕብረተሰብ ብርቱ ተቃውሞ ተሰንዝሮበታል። በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አባላትም የሊዝ ፖሊሲው የዜግነትን መብት የሚጋፋ ነው ሲሉ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል። ስለ ፖሊሲው አስተያየታቸውን የሰጡት የግል ባለሐብቶችና የከተማዋ ነዋሪዎች አዲሱ የሊዝ ፖሊሲ የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለኪሳራ የሚያጋልጥ፣ ኢንቨስተሮች ገንዘባቸውን ለልማት እንዳያውሉ የሚያስበረግግ፣ የመኖሪያ ቤትን እጥረት የሚፈጥር፣ ስራ አጥነትን የሚያባብስ፣ በቤት እጥረት የተነሳ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ቢሮአቸውን ከአዲስ አበባ እንዲነቅሉ የሚገፋፋ ነው ሲሉ ይነቅፋሉ። የሊዝ ፖለሲው በፈጠረው ስጋት ምክንያት የግል መኖሪያ ቤታቸውን ለድርጅቶች ጽሕፈት ቤትነትና ለውጪ አገር ዜጎች መኖሪያነት ያከራዩ ግለሰቦች ተከራዮቹ በአስቸኳይ እንዲለቁላቸው እየጠየቁ መሆኑንም የተለያዩ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። በዚህም ምክንያት በአዲስ አበባ የሚገኙ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሹማምንት የተፈጠረውን አሳሳቢ ሁኔታ በአሜሪካ ኒውዮርክ ለሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት በጽሁፍ አስታውቀዋል ተብሏል። በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንና በተባበሩት መንግስታት ልዩ ልዩ ዘርፎች ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ የውጪ ዜጎች በሁኔታው አሳሳቢነት ላይ ተሰብስበው መወያየታቸውንም ለማወቅ ተችሏል። የሊዝ ፖሊሲው በሚፈጥረው ውጥረትና ምስቅልቅል የተነሳ የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት (ኑሮ) ሊናጋ ይችላል ተብሎ የሚገመት ሲሆን የአለም አቀፍ ድርጅቶች ዋና መስሪያ ቤቶችም ከኢትዮጵያ ለመልቀቅ ሊገፋፋቸው ይችላል የሚል ፍራቻ አለ።

* * *

## አቶ አበራ የማነአብ አሁንም ከእስር አልተፈቱም

በአዲስ አበባ ግዮን ሆቴል በተካሄደው የሰላምና የዕርቅ ጉባኤ ላይ ለመካፈል ኢዲኅቅን ወክለው መጥተው በሽግግር መንግስቱ የታሰሩት አቶ አበራ የማነአብ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነፃ ቢያሰናብታቸውም እስካሁን ከእስር ቤት አለመውጣታቸው ታውቋል። ሚያዝያ 5 ቀን የዋለው የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት አቶ አበራ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲለቀቁ የወሰነ ሲሆን ለወህኒ ቤቱም ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር። ይሁን እንጂ የልዩ አቃቢ ህግ አቶ አበራ የማነአብ በቀይ ሽብር ወንጀል የሚጠረጠሩበት ምርመራ ተጣርቶ ክስ እስኪመሰረትባቸው ድረስ በእስር ቤት እንዲቆዩለት በመጠየቁ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት እስካሁን ሊፈቱ አልቻሉም። አቶ አበራ የማነአብን አስመልክቶ አመነስቲ ኢንተርናሽናል መግለጫ ማውጣቱንና ይህንኑ መግለጫ ለሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንትና ለሚመለከታቸው ባለስልጣኖች መላኩን ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ በሜርኩሪ ንግድ ይታማሉ ሲል ወሬውን ያሰራጨው ጋዜጣ ዋና ስራ አዘጋጅ ዳንኤል ክፍሌ የአንድ ዓመት ተኩል እስራት ተፈርዶበታል። የሽግግር መንግስቱ የዳኝነት አሰራር ፍትሃዊ አይደለም በማለት በርካታ ወገኖች የሚያማርሩ ቢሆንም የፍትህ ሚኒስትሩ አቶ ማንተመሥላሴ የሽግግሩን ሶስት ዓመታት በኢትዮጵያ የዳኝነት ታሪክ "ወርቃማ ዓመታት" ሲሉ አወድሰዋል።

* * *

## የቀድሞዎቹ የአየር ኃይል አብራሪዎች የታሰሩበት ምክንያት ታወቀ

በኢትዮጵያ አየር መንገድ የቴክኒሽያኖችና የአብራሪዎች ማሰልጠኛ ውስጥ በመምህርነት ሲያገለግሉ የነበሩት የቀድሞዎቹ የአየር ኃይል ፓይለት መኮንኖች የታሰሩት በጦርነቱ ወቅት ለተሰሩት የጦር ወንጀለኞች ተጠያቂ በመሆናቸው ነው ሲሉ የመከላከያ ሚኒስትር አቶ ሰዬ አብርሃ ለውጭ አገር የዜና ወኪሎች በሰጡት መግለጫ ገልፀዋል። በተያያዘ ሌላ ዜና ሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጦር አባላት መካከል መርጠ ያስቀራቸውን የጦር ምርኮኞች በየበረሃው ባቋቋማቸው ሚስጢራዊ ካምፖች ውስጥ በማኅር ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እየፈፀመባቸው መሆኑን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው የዜና ምንጮች ዘግበዋል። በኢትዮጵያውያኑ የጦር ምርኮኞች ላይ የሚደረገው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እንዲገታ የዓለም ሕብረተሰብ በኤርትራ መንግስት ላይ ግፊት ሊያደርግ እንደሚገባው የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ከኤርትራ ስለተባረሩት ኢትዮጵያውያን እንዳችም ተቃውሞ ያላሰማው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ምርኮኞቹንም በተመለከተ የተለየ አቋም እንደማይኖረው የእስካሁኑ ዝምታ በቂ ማስረጃ ነው ሲሉ ተቀናቃኝ ወገኖች የሽግግር መንግስቱን ይተቻሉ።

* * *

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
ETHIOPIAN
AIRLINES

## ጦርነት በምሥራቅ ኢትዮጵያ

በምሥራቅ ኢትዮጵያ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኘው ኢተሀድ የተሰኘው ቡድን በሽግግር መንግስቱ የመከላከያ ሰራዊት በተሰነዘረበት ጥቃት ጠቅላይ ሰፈሩ በቁጥጥር ስር መዋሉንና ከጥቃቱ የተረፈው ሰራዊትም መበተኑን የሽግግር መንግስቱ የመከላከያ ሚኒስትር አቶ ሰዬ አብርሃ ለውጭ አገር ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል። እንደመከላከያ ሚኒስትሩ መግለጫ በሰሜን ምዕራብ ኦጋዴንና በደቡብ ምሥራቅ ሐረርጌ ይንቀሳቀስ በነበረው በዚህ እስላማዊ አክራሪ ቡድን ላይ የተወሰደው የሐይል እርምጃ ብዙ ቅድመ ዝግጅት ያልተደረገበትና ሰፊ ያልሆነ ዘመቻ ነበር ብለውታል። በኢተሀድ ላይ በተሰነዘረው በዚህ ወታደራዊ እርምጃም ከመንግስት ወገን ምንም ጉዳት አለመድረሱን ጠቁመው በኢተሀድ ላይ የደረሰው ጉዳትም ከቁጥር የማይገባ ነው ሲሉ ገልፀውታል። በኦጋዴን አካባቢ ያለውን ችግር መንስኤም ሲያብራሩ "ችግሩ ፖለቲካዊ የሆነና ከሶማሊያ ሁኔታ ጋር ተመሳይ መሆኑን ጠቅሰው የአንድ ጎሳ ቡድን የኦጋዴን አካባቢን ለመቆጣጠር መሞከሩና የአክራሪነት አዝማሚያ መሆኑን ጠቁመዋል። አያይዘውም ኢተሀድ በምስራቅ ኢትዮጵያ ዋንኛ የእስላም አክራሪ ቡድን እንደሆነ ጠቅሰው ቡድኑን ለመቆጣጠር የአሜሪካንንም ሆነ የማንኛውም የውጪ እርዳታ መጠየቅ እንዳላስፈለጋቸው ገልፀዋል። በአሁኑ ወቅት በኦጋዴን የሰራዊት ክምችትና የከባድ መሳሪያ እንቅስቃሴዎች እንዳሉ የአይን ምስክሮች ሲገልፁ በሽግግር መንግስቱ የአክራሪ እስላሞች ግንባር የሚል ስያሜ ያገኘው የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር "ኦጋዴንን ነፃ ለማውጣት ረጅም ጊዜ አይወስድብኝም። ኦጋዴንና ሕዝቦቿ ነፃነታቸውን በቅርቡ ይቀዳጃሉ" ሲል ወታደራዊ መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል።

በተያያዘ ሌላ ዜና ይኸው የእስልምና አክራሪ ቡድን ከአረብ አገሮችና ደጋፊዎቻቸው የመሣሪያና የገንዘብ ሃይል እንደተለገሰላቸው በተለይም ኤደን፣ ኢራቅና ሊቢያ የቅርብ የጦር አማካሪዎች እንደላኩላቸው አልሻጥ የተባለው አረብኛ ጋዜጣ ዘግቧል። የመከላከያ ሚኒስትሩ የውጪ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት ስለመኖሩ ተጠይቀው ሲመልሱ የውጪ ጣልቃገብነት አለመኖሩን ገልፀዋል። የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) በአንዳንድ የገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ስለሚያደርገው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ሲያብራሩም ኦነግ በፖለቲካ ደረጃ መኖሩን ቢያምኑም ወታደራዊ እንቅስቃሴው ግን በሰኔ 1984 ማክተሙን ተናግረዋል። ስለመድኅን ፓርቲ የሽምቅ ውጊያ ተጠይቀው ሲመልሱ በወረቀት ላይ እንጂ በተግባር የተፈጠረ እንዳችም ሁኔታ አለመኖሩን አስምረውበታል። በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር ሁመራ አካባቢ የእርሻ መሬትን በተመለከተ በሁለቱ አገሮች ገበሬዎች መካከል አለመግባባት የተነሳ የሱዳን ወታደሮች ከገበሬዎቻቸው ጎን ተሰልፈው ችግር ፈጥረው ነበር ካሉ በኋላ ነገር ግን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ችግሩን ለማስወገድ ስምምነት ላይ ተደርሷል ሲሉ አክለው ገልፀዋል። በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ አማጺ ሱማሌዎች በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆኑ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን ከስፍራው የሚደርሱት የዜና ዘገባዎች ይጠቁማሉ። ባለፈው ወራት ዜናችን ስለመፍረሱ የተዘገበው የቀራሂው ጀግና የደጃዝማች አፈወርቅ ወ/ሰማያት ሐውልት በእስልምና ደንብ መሰረት እንዲቀበር መደረጉን ለማወቅ ተችሏል። ሁኔታውን የተከታተሉ አንዳንድ ታዛቢዎች የእኚሁን ጀግና ኢትዮጵያዊ ሐውልት በቆመበት ስፍራ እንዲፈርስ መደረጉ ሳያንስ በእስልምና ደንብ መሰረት መቀበሩን "ታሪክን የማጥፋት ሴራ" ሲሉ በምሬት ይናገራሉ።

* * *

## ጅቡቲ መላኩ ተፈራን አሳልፋ ሰጠች

ለብዙ ኢትዮጵያውያኖች እልቂት ተጠያቂ ናቸው የሚባሉት የቀድሞው የደርግ ባለስልጣን ሻለቃ መላኩ ተፈራ በስደት ከነበሩበት ጅቡቲ "ሕገ ወጥ ነዋሪ" ተብለው እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ በሽግግር መንግስቱ እጅ ገብተዋል። ኢሕአዲግ ስልጣን በያዘበት ወቅት ጅቡቲ የገቡት ሻለቃ መላኩ ተፈራና ሻለቃ በጋሻው አታላይ በኮሎኔል መንግስቱ የስልጣን ዘመን የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትና የክፍለ ሀገራት ኢሠፓ ከፍተኛ ሹሞች እንደነበሩ የሚታወስ ነው። በተለይም ሻለቃ መላኩ ተፈራ በጎንደር ሕዝብ ላይ የጭካኔና የአረመኔነት ተግባር በመፈጸማቸው በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻና በቀል ማሳደራቸው በብዙ ወገኖች ዘንድ ይነገራል። በመሆኑም እኚህ የቀድሞ ባለስልጣን ለፍርድ እንዲቀርቡ መደረጉ ራሱ ሲያስቃዩት የኖሩትን የጎንደር ሕዝብ ስሜት በከፍተኛ ደረጃ ሊስብ እንደሚችል ይታመናል። ይሽም ሁኔታ ግለሰቡን ይዞ ላቀረበው ኢሕአዲግ ጥሩ ግምትና የባለውለታነት ስሜት ሊያሳድር ስለሚችል የጎንደር ሕዝብ በመጪው ምርጫ ለኢሕአዲግ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ።

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ በጅቡቲ የስራ ጉብኝት ካደረጉ ከ48 ሰዓታት በኋላ ጅቡቲ "ህገ ወጥ ነዋሪዎች" ብላ ያባረረቻቸው እነዚህ ባለስልጣኖች በኢትዮጵያ መንግስት እጅ መግባት የሁለቱ አገሮች ባለስልጣኖች የእስረኞች ልውውጥን በተመለከተ የተፈራረሙት ውል ውጤት ሳይሆን እንዳልቀረ ተመልክቷል። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ዘግናኝ ግፍ የፈፀሙ ወንጀለኞች ለፍርድ መቅረብ የብዙዎች እርካታ ቢሆንም በአንፃሩ ደግሞ ወንጀሎችን በማደኑ ሰበብ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን የማደኑ ሂደት እንዳይጀምር የብዙዎች ስጋት ነው።

ሻለቃ መላኩ ተፈራ በጅቡቲ ቆይታቸው ወቅት ባልታወቁ ግለሰቦች የግድያ ሙከራ ተደርጎባቸው እንደነበረ የሚታወስ ሲሆን "በ8 ጥይት ስለመታሁት አይተርፍም። ገድየዋለሁ" ብለው ለዜና ማሰራጫዎች የገለፁ ግለሰብ እንደነበሩ ይታወሳል። ሁለቱ ባለስልጣኖች ፍርድ ቤት በቀረቡበት ወቅት ብዛት ያለው ሕዝብ የፍርድ ቤቱን ቅጥር ግቢ አጨናንቆ ነበር። በሻለቃ መላኩ ተፈራም ላይ የስድብና የእርግማን ናዳ የወረደባቸው ሲሆን በአንዳንድ ግለሰቦችም ተተፍቶባቸዋል። ሻለቃ መላኩ ለአንድ የግል ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ ህሊናቸውን የሚፀፅታቸው አንዳችም ነገር አለመኖሩንና በስልጣን ዘመናቸው የፈፀሙት ሁሉ አምነውበትና ለዓላማቸው ሲሉ መሆኑን ተናግረዋል። ይህ በዚህ እንዳለ የጅቡቲ የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ማህበር ባወጣው መግለጫ የሁለቱን የቀድሞ ባለስልጣኖች ለኢትዮጵያ መንግስት አሳልፎ መስጠት አውግዟል። እንደመግለጫው አባባል ሁለቱ የቀድሞ ባለስልጣኖች በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ጥብቅ ክትትል ሲደረግባቸው እንደነበር ተጠቅሶ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች በተካሄደው የግድያ ሙከራ በተአምር የተረፉና ለብዙ ወራት ህክምና ሲደረግላቸው እንደነበር ተመልክቷል። በዚህ የግድያ ሙከራ መነሻነትም በጅቡቲ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ጥበቃ እንዲያደርግላቸው ቢጠይቁም ሳይሳካላቸው መቅረቱንና ለፖለቲካ ስደተኝነታቸውም እውቅና እንዳያገኙ፤ ወደ ሌላ አገርም እንዳይሄዱ ታግደው መቆየታቸውን አትቷል። በመጨረሻም ሁለቱ ባለስልጣኖች በሚቀርብባቸው ክስ የሞት ቅጣት ሊጠብቃቸው እንደሚችል እየታወቀ የጅቡቲ መንግስት በወንጀለኛ ልውውጥ ስም በጅቡቲ ደቡባዊ ድንበር ላይ ለኢትዮጵያ ባለስልጣናት አስረክቦ ለእስር እንዳበቃቸው ጠቅሶ ማህበሩ ድርጊቱን አውግዟል።

*        *        *

## የአምባሳደር ማርክ ባስ የስንብት ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካዊው አምባሳደር ሚስተር ማርክ ባስ በኢትዮጵያ ቆይታቸው ወቅት ከስራ ኃላፊነታቸው አኳያ ስለተገነዘቡት ጉዳዮች ለጋዜጦች መግለጫ ሰጥተዋል። አምባሳደሩ በሰጡት በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫቸው በሶስቱ የሽግግር ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እየሰፈነ መሆኑን እንደተመለከቱና ይህም ለሰብአዊ መብት አከባበር መሻሻል መርዳቱን አውስተዋል። አምባሳደሩ በስራ ዘመናቸው ማጠናቀቂያ ወቅት ላይ በሰጡት በዚህ መግለጫቸው መንግስታቸው ያለ ፍርድ ታስረው ስለሚገኙት እስረኞች ጉዳይ መቆርቆሩን ጠቅሰው በተለይም ሶስት ሺህ የሚሆኑ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ምርኮኞች በደዴሳና በሁርሶ እንደሚገኙ፤ እነዚህም ምርኮኞች ለፍርድ እንደሚቀርቡ ወይም እንደሚለቀቁ ከሽግግር መንግስቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር መነጋገራቸውን ጠቁመዋል። ይህ መቼ ሊሆን እንደሚችል ግን ጊዜውን በውል አልጠቀሱም። በሽግግሩ ዘመናት ውስጥ የተከናወኑ ጉዳዮችን በአብዛኛው አወድሰዋቸዋል። በፖለቲካው ሳቢያ ወህኒ ለወረዱት ግለሰቦችና ጋዜጠኞች ጭምር ምህረት እንዲደረግላቸው ፕሬዚደንት መለስ ቃል ገብተውልኛል ሲሉ ተደምጠዋል። የአምባሳደሩን መግለጫ የተከታተሉ የግል ሚዲያዎች አምባሳደሩ እንደ አንድ ዲፕሎማት ሳይሆን እንደ አንድ የመንግስት ባለስልጣን መግለጫ የሚሰጡ መሆናቸውን ተችተው ፅፈዋል። በተያያዘ ሌላ ዜና የአሜሪካ ኢምባሲ በኢትዮጵያ እየተፈፀመ ይገኛል ስለሚባለው የሰብአዊ መብት መጓደል ከኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ጋር በቅርብ ተገናኝቶ ለመስራት ፍላጎት እንዳለው የኤምባሲው አንደኛ ፀሐፊ ለጉባኤው ጽሕፈት ቤት በላኩት ደብዳቤ ጠይቀዋል ሲል አንድ የዜና ምንጭ ዘግቧል። አምባሳደር ማርክ ባስ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ሰፍኗል፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ በተሻለ ሁኔታ ተከብሯል ባሉ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከኢሰመጉ ጋር ለመስራት ከኤምባሲው ጥያቄ መቅረቡ የድርጅቱን ጥረት በስልት ለማዳከም ይሁን ወይም ከልብ የሰብአዊ መብት ችግሮችን ለማቃለል በግልጽ የታወቀ ነገር የለም። አሜሪካ ከዚህ ድርጅት ጋር ተቀራርባ ለመስራት ጥያቄ ማቅረቧ ወደፊት ሊፈጠር የሚችለውን የአቋም ለውጥ ያመለክታል የሚሉ ወገኖችም አልጠፉም።

በሌላ በኩል የአሜሪካ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰብአዊ መብት ረገጣ ያሳሰበው መሆኑን ገልጧል። የአሜሪካንን መንግስት አቋም በሚያንፀባርቀው የ"VOA" ርዕሰ አንቀጽ ባሰፈረው በዚህ ሐተታ የሽግግሩ መንግስት በጋዜጦች ላይ የወሰደው የእሥራት እርምጃ እንዳሳሰበውም ተወስቷል።

*        *        *

## በአየር መንገዱ መዋቅር ተግባራዊነት ሠራተኛ ማኅበሩና ማኔጅመንቱ ተፋጠዋል

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ማኅበር አዲሱን የድርጅቱን መዋቅር በጥቂት ሠራተኞች አስተባባሪነት በተግባር ላይ ለማዋል ማኔጅመንቱ የሚያደርገውን ጥረት በመቃወም ለአየር መንገዱ ሠራተኞች ማሳሰቢያ አስተላልፏል። እንደሠራተኛ ማኅበሩ ማሳሰቢያ የአየር መንገዱ ቦርድ የሠራተኞችን ፍላጎትና ጥያቄ በመናቅ ጥናትና ጥራት በጎደለው መንገድ ድርጅቱን የማዋቀር ሂደት እየገፋበት መሆኑን ጠቅሶ ለዚህም ከ60-70 የሚደርሱ ሰዎችን በማስተባበር ላይ መሆኑን ይፋ አድርጓል። ይኸም የድርጅቱ መዋቅር በሰራተኛው ተሳትፎና ፈቃደኝነት በተግባር ላይ እየዋለ ነው ለማለትና ሰራተኛውን በውድቀቱ ተጠያቂ ለማድረግ የተሸረበ ሴራ መሆኑን የሰራተኛ ማኅበሩ አጋልጧል።

የሰራተኛ ማኅበሩ በዚህ መግለጫው በጠየቃቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ችግር እንዳይደርስበትና ያለአግባብ መወገዙን የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ባሳየው አቋም ከቦርዱ የተሰነዘረበትን ነቀፋና ማዋከብ ለሰራተኞቹ ግልጽ አድርጓል።

ስለዚህም አየር መንገዱን በሚጎዳ መልኩ በሚደረገው የማዋቀር ሂደት ላይ ያለውን ብርቱ ተቃውሞ ለማኔጅመንት ቦርዱ ማቅረቡን ጠቅሶ የተቋቋመው ግብረ ኃይል እንዲፈርስና ድርጅቱም በዚህ ላይ ያለውን አቋም በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እንዲሰጥ መጠየቁን አስረድቷል። በሌላ በኩል የቀድሞዎቹ የአየር መንገዱ ባለስልጣኖች ከስራ የመባረራቸው መንስኤ ለቦርዱ ሊቀመንበር ለአቶ ስዩ አብርሃ የፃፉት ደብዳቤ መሆኑን አንድ የዜና ምንጭ ይፋ አድርጓል። ባለስልጣናቱ በዚህ ደብዳቤያቸው አዲሱ መዋቅር ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ቦርዱ ልምድ ያላቸውን የአየር መንገድ ባለሙያዎች እንዲያማክር ያስገነዘቡና የተማፀኑ ቢሆንም ከቦርዱ የተሰጣቸው ምላሽ ግን ደብዳቤውን የፈረሙትን የአየር መንገዱን ባለስልጣኖች ከስራ አባርሯቸዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ አዲሱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስራ አስኪያጅ ዶ/ር አሕመድ ኬሎ African Airlines ከተሰኘ መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የአየር መንገዱን መዋቅር መለወጥ ያስፈለገው ድርጅቱን ከውድቀት ለማዳን ነው ሲሉ ገልፀው እርምጃውን ንፁህ የንግድ ውሳኔ ነው ብለውታል። እ.ኤ.አ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከተሾሙበት ጊዜ ድረስ እንግሊዝ አገር በአካውንቲንግና በፋይናንስ ሙያ ሲያስተምሩ የነበሩት ዶ/ር አሕመድ ኬሎ አየር መንገዱ ከኤርትራ አየር መንገድና ከመሳሰሉት የጎረቤት አገሮች ድርጅቶች ጋር በጋራ ሊሰራ እንደሚችል ጠቁመው የአየር መንገዱ ስም ግን እንደማይለወጥ ተናግረዋል። በተያያዘ ሌላ ዜና አየር መንገዱን የመሰረቱትና ለ15 አመታት በዋና ስራ አስኪያጅነትና በቴክኒክ አገልግሎት ዲሬክተርነት የመሩት አምስት እውቅ አሜሪካውያን የአቪዬሽን ኤክስፐርቶች ባሰራጩት ግልጽ ደብዳቤ የድርጅቱን መዋቅር በመለወጥ ሰበብ የተወሰደው እርምጃ ድርጅቱን የሚያዳክም፣ እጅግ አሳሳቢ ብቻም ሳይሆን መገታት ያለበት አጥፊ አካሄድ ነው ሲሉ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል። የአየር መንገዱ ሰራተኞች፣ የስራ ኃላፊዎችና የማኅበር መሪዎች ጥናቱ እንደገና በባለሙያዎች እንዲታይ በጽሁፍ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱ ቀርቶ ጭራሽ ከስራ የመባረርና የመታሰር ያስከተለባቸው መሆኑ እንዳሳዘናቸው አሜሪካውያኖቹ ኤክስፐርቶች ገልፀዋል። በተጨማሪም የመንግስት ባለስልጣናት በአየር መንገዱ ላይ ሊወስዱ ያቀዱትን እርምጃ እንደገና እንዲያጤኑት በጥብቅ አሳስበው ይህን አቤቱታ የሚያቀርቡት የሞራል ግዴታ ስላለባቸው መሆኑን አስገንዝበዋል።

* * *

## የመድኅን ፓርቲ የማጥቃት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ጀመርኩ አለ።

በኮሎኔል ጎሹ ወልዴ የሚመራው የመድኅን ፓርቲ ለሰላም ያደረገው ጥረት ሁሉ መሟጠጡንና ከእንግዲህ በፓርቲው የሽምቅ ተዋጊ ኃይል የጥቃት እርምጃዎች መጀመሩን ባወጣው መግለጫ ይፋ አድርጓል። መግለጫው እንደሚያመለክተው ከ50,000 በላይ የሚሆነው የኮማንዶ ቡድን ግዳጁን ለመፈፀም በተጠንቀቅ ላይ እንደሚገኝ ገልጿል። እያይዞም የወታደራዊ ጥቃቱ የመጀመሪያ ዒላማ የኢሕአዲግ ሰራዊት መሆኑን ገልፆ የመሳሪያ ክምችቶችን ማጋየት፣ የፖለቲካ ሰዎችን ማስለቀቅና የመሳሰሉትን ወታደራዊ ግዳጆች መፈጸም ነው ብሎአል። ፓርቲው አለኝ የሚለው 50,000 የሠራዊት ቁጥር የተጋነነ ሳይሆን እንደማይቀር የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ የፓርቲያቸው ወታደራዊ ቅድሚያ ዝግጅት እየተጠናቀቀ ነው ካሉ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሚያዝያ 27 ቀን በደብረ ብርሃን ከተማ ከሚገኘው ወህኒ ቤት 500 (አምስት መቶ) እስረኞችን በኃይል የማስፈታት እርምጃ ተወስዷል። የመድኅንን ፓርቲ "እስረኞችን የማስፈታት እርምጃ የወሰድኩት እኔ ነኝ" ሲል በይፋ ኃላፊነቱን እስከወሰደበት ጊዜ ድረስ የመንግስትና የግል ሚዲያዎች ማንነታቸው ያልታወቀ የታጠቁ ኃይሎች የወሰዱት እርምጃ ሲሉ ወሬውን አሰራጭተዋል። ደብረ ብርሃን የሚገኙ ዜና ዘጋቢዎችና የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚገልፁት የደብረ ብርሃኑ ኦፕሬሽን ታጣቂ ኃይል ከተማዋ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ተልዕኮውን አጠናቆ እስከተመለሰበት ጊዜ ድረስ የነበረው እንቅስቃሴ ስልታዊ እንደነበረ ዘግበዋል። እንደ ዜና ዘገባዎቹ ከሆነ ታጣቂው ኃይል ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ሲሆን ከኢሕአዴግ ታጣቂ ጋር ተመሳስሎ ወደ ከተማዋ መግባቱ ተረጋግጧል። ከባድና የነፍስ ወከፍ መሳሪያ፣ ቦምብና በሽራ የተጠቀለለ ግዙፍ መሳሪያ የታጠቀ ኃይል ከተማዋን በምሽት ሲያጥለቀልቅ በአለባበስ በትጥቅና በእንግድነታቸው የትኛው የመንግስት፣ የትኛው የተቃዋሚ ኃይል ጦር መሆኑ አይለይም ነበር ተብሏል። ከምሽቱ 5 ሰዓት ላይ በከተማዋ አራቱም ማዕዘናት ድብልቅልቁ የወጣ የከባድ መሣሪያ ተኩስ ለአንድ ሰዓት ያህል መካሄዱም ይነገራል። እንደ አይን ምስክሮች ከሆነ በምሽቱ የነበረው የከባድና ቀላል መሳሪያዎች ተኩስ ኢሕአዴግ ከተማዋን በተቆጣጠረበት ዕለት ከተሰማው ተኩስ እንኳን ይበልጣል ተብሏል። ከሽግግር መንግስቱ የመከላከያ ጦር ጋር ተመሳስሎና ተቀላቅሎ የገባው ታጣቂ ኃይል ከአራት እስትራቴጅያዊ ቦታዎች ላይ ከተማዋን በከባድ መሳሪያ አጥሮ 5 ሰዓት ላይ ድብልቅልቅ ያለ የማደናገሪያ ተኩስ በመክፈት ኦፕሬሽኑን መጀመሩ ታውቋል። በዚህ ኦፕሬሽን ወህኒ ቤት ከነበሩት እስረኞች መካከል የተወሰኑት በስም ዝርዝራቸው እየተጠሩ ቡድኑን ተቀላቀሉ ሲሆን

ሌሎችም በነፃ ተለቀው ወደፈለጉበት መሄድ የሚችሉ መሆናቸው ተነግሯቸዋል። ከመንግስት ጦር በኩል የአፀፋ የተኩስ መልስ ያልተሰጠ ሲሆን ታጣቂው ቡድን ስራውን አጠናቆ ከሄደ ከሰዓታት በኋላ የመንግስት ጦር የታጣቂ ቡድኑን አቅጣጫ ተከትሎ ጉዞ መጀመሩን የአይን ምስክሮች ይናገራሉ። በዚህ ኦፕሬሽን መስፍን አራጋው የተባለ የወህኒ ቤቱ ጠባቂ ፖሊስና አንድ እስረኛ መሞታቸው ታውቋል። የአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ ያሳሰበው የሽግግሩ መንግስት ከባድ መሳሪያ የታጠቀ ብዙ ሺህ ጦር በደብረ ብርሃን ማስፈሩን ለማወቅ ተችሏል። ደብረ ብርሃን ከተማ የታጣቂው ቡድን ተልዕኮ ከተጠናቀቀበት ሰዓት ጀምሮ ፀጥ ያለች ቢሆንም ለሽምቅ ውጊያ አመቺ በሆኑት ስትራቴጂካዊ ቦታዎች ላይ ችግሮች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል። በጣርማ በርና ወደ ደብረ ሲና በሚወስደው አውራ ጎዳና ላይ ታጣቂ ኃይሎች ጥቃትና ዘረፋ ተካሂዷል። በደብረብርሃን አካባቢው በሚገኙ የቀድሞ ጦር አባላት ላይ ጠንከር ያለ ክትትልና አፈና በመደረጉም ላይ ነው።

በሌላ በኩል ኮ/ል መንግስቱ አቋቁሜዋለሁ የሚሉትን የጥቁር አንበሳ ጦር ለማጠናከር ሰሞኑን በሳውዲት አረቢያ የጠረፍ ከተማ የቀድሞ የጦር ሹማምንት ስብሰባ ማድረጋቸው ታውቋል። ከፋኝ የተሰኘውም ድርጅት የጦር ጄኔራሎች መሸሙ የተዘገበ ሲሆን መንግስት ስለዚህ ድርጅት ወታደራዊ ድል የዘገበ አንድ ጋዜጣ አዘጋጅ በገንዘብና በእስራት ገደብ መቆጣቱ ካለው ፍራቻ ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቷል።

የሽግግር መንግስቱን በጠመንጃ ኃይል እንፋለማለን የሚሉ ድርጅቶች መበራከት የአገሪቷን የሰላም ሁኔታ ሊያደፈርስና ወደ ሌላ የጦርነት አዘቅት ውስጥ እንዳይከታት ጉልህ የሆኑ የሕዝብ ስጋቶች አሉ። ማንነታቸው በማይታወቅ ታጣቂ ኃይሎች በየአውራጎዳናዎች ላይ የሚደረገው ዝርፊያ ባልታወቀ ምክንያትና ባልታወቁ ሰዎች ጨለማን ተገን በማድረግ የሚፈፀሙ ግድያዎች ለዚህ ስጋት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የመከላከያ ሚኒስትሩ አቶ ስዬ አብርሃ ሰሞኑን ባደረጉት አንድ ቃለ ምልልስ ተቃዋሚ ወገኖች በምንም ሁኔታ ጦርነት ማስነሳት አይችሉም ሲሉ በልበ ሙሉነት ተናግረዋል። በደብረ ብርሃኑ ኦፕሬሽን የተደናገጠው የሽግግር መንግስቱ የመከላከያ ሰራዊት የእነዚህን ተቃዋሚዎች አከርካሪ ለመስበርና መቀጣጫ በእልህና በቁጣ እያደባ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

## የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ሩዋንዳ ሊዘምቱ ነው

በመቶ ሺህ ለሚቆጠሩት ሩዋንዳዎች ዕልቂትና በሚሊዮን ለሚቆጠሩት ደግሞ መሰደድ ምክንያት የሆነውን የሩዋንዳ እርስ በእርስ ጦርነት ለማብረድ የኢትዮጵያ መንግስት 800 ያህል ወታደሮችን ሊልክ ነው። ከኡጋንዳ፣ ከጋና ከኢትዮጵያ ለሚውጣጣው 5000 ያህል ጦር ለየሀገሪቱ መንግስታት ጥያቄውን ያቀረቡት የተ.መ.ድ. ዋና ፀሐፊ ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ናቸው ተብሏል። የሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ም/ቤት በጉዳዩ ላይ መክሮ የወሰነው አለመሆኑንና ለስምምነቱም ባዕድ መሆኑን ዜናውን የዘገበው የዜና ምንጭ ጠቁሟል። እንደወታደራዊ አዋቂዎች እምነት አሁን ያለው የመከላከያ ሰራዊት ከአንድ ብሄርና የፖለቲካ ድርጅት የተውጣጣ የሽግግር ጊዜ ሰራዊት እንጂ ለአለምአቀፍ ግዳጅ ተልዕኮ ብቃት ያለው አይደለም። ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት ጦሩ የገበሬ ሰራዊት እንጂ የመደበኛ ጦር ሠራዊት ብቃት የሌለው በመሆኑ ነው ይላሉ።

* * *

## የኢሕአዴግ አንዱ አባል ድርጅት ራሱን አከሰመ

በስልጣን ላይ ያለው ኢሕአዴግ አንዱ አባል ድርጅት የሆነው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መኮንኖች ንቅናቄ (ኢዲመአን) ራሱን ማክሰሙንና ከእንግዲህ የፖለቲካ ድርጅቱ ሕልውና ማክተሙን ባወጣው መግለጫ ይፋ አድርጓል። በኢትዮጵያ መደበኛ ጦር ሰራዊት ውስጥ በምርኮና በልዩ ልዩ ምክንያቶች አፈንግጠው ከኢሕአዴግ ጋር በወገኑ መኮንኖችና ወታደሮች የተቋቋመው ይህ ድርጅት በጦርነቱ ወቅት የቀድሞውን መንግስት ቁልፍና ወታደራዊ ሚስጢሮችን አሳልፎ በመስጠት ለመንግስት የጦር ስትራቴጂ ውድቀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ተብሎ ሲነቀፍ ቆይቷል። ከኢሕአዴግ ጋር ወግኖ የቀድሞውን መንግስት ሰራዊት ሲጨፈጭፍና ሲያስጨፈጭፍ በኋላም ሲጠቁምና ሲያሳፍን የነበረ ነው በማለት በምሬትና በጥላቻ አይን የሚመለከቱት ወገኖች ቁጥር ቀላል አይደለም። ድርጅቱ በኢሕአዴግ አባልነቱ በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ መቀመጫ የነበረው ሲሆን በሽግግሩ ዓመታት ውስጥ የቀድሞውን የመከላከያ ተቋም በማፈራረስና ሰራዊቱን በመበታተን በጠቋሚነትና በስለላ ተግባር ጭምር በማገልገል ጉልህ አስተዋጽኦ መድረጉን ብዙዎች ይስማሙበታል።

ድርጅቱ ስለመፍረሱ ዝርዝር መግለጫ ባይሰጥም ትግሉን ከሌሎች ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር ለመቀጠል መወሰኑን አስገንዝቧል። እንደአንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት ድርጅቱ ከመነሻው ተቃዋሚዎችን ለማዳከም ኢሕአዴግ ያቋቋመውና በመሳሪያነት የተጠቀመበት እንደመሆኑ እንድም የቀድሞውን ጦር በድርጅት አባልነት አቅፎ ለመጓዝ ካለመፈለግ፣ ወይም ጨርሶ እምነት ያልጣለባቸው በመሆኑ ለመፍረስ የበቃ ነው ይላሉ። የድርጅቱ አባላት በኃላፊነት ላለመጠየቅ፣ ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ወይም ከስም አርአያነትን ለማሳየት ነው የሚሉም እንዳሉ ታውቋል።

* * *

# ሕገመንግስትና ሕገመንግስታዊ ጉባኤ

## የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል በሕገመንግስት ሊፀድቅ ነው

ለኢትዮጵያ የወደፊት መተዳደሪያ ሕግ ይሆናል በተባለው ሕገ መንግስት ውስጥ የብሔሮችና የብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል ድረስ የሚሰጥ መብት እንደሚፀድቅ ይጠበቃል። በሕገመንግሥቱ ላይ ሕዝቡ ዳር እስከ ዳር ተንቀሳቅሶ ንቁ ተሳትፎ አድርጎበታል ሲሉ የመንግሥት ባለስልጣኖች ቢናገሩም የነበረው እውነታ ግን ከዚህ ፍጹም የሚርቅ መሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው። በብዙ የአገሪቱ ክፍሎች የተካሄደው ውይይት ቀዝቃዛና ተቃውሞ በዝምታ የተገለፀበት ነበር ሲሉ የግል ሚዲያዎች በየቦታው ተዘዋውረው የተመለከቱትን ዘግበዋል።

በሕገ-መንግስቱ የመገንጠል ጥያቄ ላይ በተደረገው ውይይት በፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊና በዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል መካከል ከወትሮው ለየት ያለ ክርክር ተደርጎ ነበር። ባለፉት ሶስት የሽግግር ዓመታት ከኢሕአዴግ ጋር በቅርበት ሰርተዋል የሚባሉት ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል በመገንጠል ጥያቄ ላይ ከፕሬዚዳንቱ ጋር ሰፊ የሃሳብ ልዩነት ማሳየታቸው ብዙ ወገኖችን አስገርሟል። በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የተላለፈውን ይህን ውይይት ብዙ ኢትዮጵያውያኖች በትዝብትም በእንክሮም ተከታትለዋል።

ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል በሰጡት አስተያየት የመገንጠል ጥያቄ በተሳሳተ የታሪክ ትርጉም ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ታሪክ ጋር አዛምደው በስፋት አብራርተዋል። አያይዘውም አንድ ሰው አገር ሊያፈርስ ይችላል፣ ነገር ግን ብቻውን አገር ሊገነባ አይችልም ካሉ በኋላ ለመገንጠል ጥያቄ ሕገመንግስታዊ ዋስትና መስጠት ለአገር ጠንቅ በመሆኑ እስከነአካቴው መነሳት የለበትም ሲሉ አቋማቸውን በድፍረት አስታውቀዋል። ይህ አስተያየታቸው አብዛኛውን መቀመጫ ኢሕአዴግ በያዘው የተወካዮች ም/ቤት ውስጥ ቁጣ አስነስቶባቸዋል።

ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ከዶ/ር ኃይሌ የተሰነዘረው አስተያየት በጣም የሚያስፈራ ነው ሲሉ ቁጣ በተቀላቀለ አነጋገር የተሰማቸውን ስጋት ገልፀዋል። እንደፕሬዚዳንቱ እምነት "ስለ ታሪክ ብዙ ሊባል ይችላል። በጣም ግማሽ ሐቅ ስለሆነ። የመገንጠል ጥያቄ የመብት ጥያቄ የዲሞክራሲም እምብርት ነው" ብለውታል። አያይዘውም እያንዳንዱ ብሄርና ብሄረሰብ ኢትዮጵያዊነትን ፈልጎና አምኖ የሚያገኘው ክብር እንጂ በግድ እንደእንቆቆ የሚጋተው መሆን የለበትም ሲሉ የግላቸውንና የድርጅታቸውን አቋም ግልጽ አድርገዋል። የም/ቤቱን ውይይት በጥሞና ሲከታተሉ የነበሩ ወገኖች ፕሬዚዳንቱ የታሪካችንን ግማሽ ሐቅነት መቀበል የመቶ አመት ታሪክ ሲሉት የነበረውን የኢትዮጵያን ታሪክ ቢያንስ ወደ ግማሹ ወደ አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመት ከፍ ስለሚያደርገው ጥሩ መሻሻል ነው ሲሉ ተችተዋል። ረቂቅ ሕገመንግስቱን ለማጽደቅ ባለፈው ግንቦት 28 ቀን 1986 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያ ምርጫ ተካሂዷል። 548 መቀመጫ ለሚኖረው የሕገመንግስት ጉባኤ አባላት 1470 ዕጩዎች መቅረባቸውንና 38 የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፈውበታል ሲል የምርጫ ቦርድ መግለጫ ሰጥቷል። እንደመግለጫው 15 ሚሊዮን ሕዝብ በምርጫው የተሳተፈ መሆኑ ሲገለጽ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕገ-መንግስቱ ዝግጅትም ሆነ የሕገ-መንግስት ጉባኤ አባላት ምርጫ ሂደት የአንድ ድርጅት የበላይነት የነገሰበት ከደርግ ሕገመንግስት ያልተሻለ ፋይዳቢስ ጥረት ሲሉ ያጥላሉታል። አልፈው ተርፈው የፖለቲካ ድርጅቶችና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምርጫው ራሳቸውን እንዲያገሉ ጥሪ አስተላልፈዋል። ከእነዚህም መካከል የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት፣ መአህድ፣ መድኅን፣ የኢትዮጵያ የሰላምና የዲሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ም/ቤት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እንደተቃዋሚ ድርጅቶቹ እምነት የሽግግር መንግሥቱ ሕገመንግስት ለማርቀቅ የሚያደርገውን ሩጫ ትቶ ለብሔራዊ ዕርቅና ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት ለመመስረት ራሱን ለድርድር መዘጋጀት አለበት ባዮች ናቸው።

ለሕገመንግስት ጉባኤ አባላት ለውድድር የቀረቡት በአብዛኛው በኢሕአዴግ ስር ያሉ ድርጅቶችና የግል ተወዳዳሪዎች ብቻ ስለመሆኑ በየጊዜው በመንግስትና በግል ሚዲያ የተሰራጩት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለዚህ ምርጫ ኢሕአዴግና በየብሄሩ ኢሕአዴግ ያደራጃቸው "ተለጣፊ" ድርጅቶች ያለ ምንም ተፎካካሪ ለውድድር ሊቀርቡ እንደሚችሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች አስቀድመው ገምተው ነበር። ፕሬዚዳንት መለስ በግንቦት 20 ዕለት ባደረጉት ንግግር የግል ተወዳዳሪዎች ቁጥር ከፍ ብሎ መታየት አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች የራሳቸውን አባላት በግል ተወዳዳሪ ሽፋን በማቅረባቸው ነው ሲሉ ከምርጫው ራሳቸውን ባገለሉ ድርጅቶች ላይ ያነጣጠረ ትችት ሰንዝረዋል። እንደአንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት ከ90% በላይ የሚሆኑት የሕገ-መንግስት ጉባኤ አባላት የኢሕአዴግ አባላት ይሆናሉ። "ታማኝ ተቃዋሚ" ይሆናል የተባለለት በዶ/ር ፈቃደ ገዳሙና በዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል የተቋቋመው ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ያቀረብኳቸው ጥያቄዎች አልተመለሱልኝም በማለቱ ከምርጫው ራሱን አግልሏል።

(ወደ ገጽ ይዞራል)

## ዳግም ድርቅና ረሃብ በኢትዮጵያ
## በሺዎች የሚቆጠሩ እየሞቱ ነው።



የሽግግር መንግስቱ የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን በሰጠው መግለጫ ከ6.7 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ሕዝብ ለረሃብ መጋለጡን መግለጹ ይታወሳል። እንደኮሚሽኑ መግለጫ በረሃብ ከተጠቃው መካከል 5.5 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ በተፈጥሮ አደጋ፤ 1.2 ሚሊዮን የሚሆነው ደግሞ በጎሳ ግጭት ቀዬአቸውን ለቀው የተሰደዱ የኤርትራ ተፈናቃዮችና ከጎረቤት አገሮች ከስደት የተመለሱ ናቸው ተብሏል። አያይዞም በአሁኑ ጊዜ የተከሰተው የረሃብ አደጋ በድርቅ ብቻ የተከሰተ አለመሆኑን አመልክቶ በአንዳንድ አካባቢዎች ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በረዶ በመጣል፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የአንበጣና የአይጥ መንጋ በሰብል ላይ ጉዳት ማድረሱን እንዲሁም በገንዲ በሽታ የእርሻ በሬዎች መሞት ጭምር መሆኑን ገልጿል።

የሽግግር መንግስቱ ጠ/ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ ሰሞኑን በደቡብ ኢትዮጵያ ረሃቡ ባጠቃቸው አካባቢ ባደረጉት ጉብኝት ምንም ዕርዳታ ያልደረሳቸው፣ መኖራቸውና መራባቸው እንኳ የማይታወቅ ብዙ መቶ ሺህ ረሃብተኞች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። በሰሜን ኦሞ (ጋሞጎፋ) ክልል በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከአምስት ሺህ ሕዝብ በላይ ማለቁንና አሁንም ከዚያ የሚበልጠው ሞቱን በመጠባበቅ ላይ መሆኑን የአካባቢው ባለስልጣኖችና የአገር ሽማግሌዎች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረድተው መንግስት በአስቸኳይ እርዳታ እንዲያቀርብላቸው ተማጽነዋል። ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደቀረበው ዘገባ ከሆነ በአካባቢው ከብቶች አልቀዋል። ከረሃብና ከድርቁ ጋር በተያያዘ ውሃ ወለድ በሽታዎች፣ ወባና ተቅማጥ የብዙ ሕዝብ ሕይወት እያጠፉ መሆኑን አካባቢው በውኃ ሙላት በድልድዮች መሰበርና በአውራ ጎዳናዎች አለመኖር የተነሳ በከብት ጀርባ እንኳ ዕርዳታ ለማድረስ እንደሚያስቸግር ተገልጿል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ያህል ህዝብ በረሃብ እየረገፈ መሆኑን መንግሥት እንዳላወቀ ጠቅሰው 6.7 ሚሊዮን የተባለው የረሃብተኛ ቁጥር ከ7 ሚሊዮን በላይ ሳይሆን እንደማይቀር ግምታቸውን ሰጥተዋል። ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር መንግስት የችግሩን መጠን አያውቀውም የሚሉ ወገኖችን ግምት አጠናክሯል። ከዚህም በመነሳት ዘግናኝ የሕዝብ ዕልቂት ሊከሰትና ከተሞችም በረሃብተኞች ሊጥለቀለቁ ይችላሉ የሚል ከፍተኛ ፍራቻ አለ። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ጠኔን የሚያድር ኢትዮጵያዊ እንደሌለ፣ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ እንዳልተከሰተ፣ የምርት እጥረት እንጂ የገንዘብ እጥረት የለም ሲሉ የነበሩት የመንግስት ባለስልጣኖች በሺህ የሚቆጠሩ ወገኖች በረሃቡ ማለቃቸውን አምነዋል። መንግስታዊ እንደሚያመለክቱት በዕርዳታ ፈላጊው ረሃብተኛ ቁጥርና በተረዱት መካከል ሰፊ ልዩነት የሚታይ በመሆኑ በመጪው የክረምት ወራት ከመገናኛ ችግር ጋር ተዳምሮ ብዙ የዕርዳታ ፈላጊ ሕዝብ ሊያልቅ እንደሚችል ባለሙያዎች ስጋታቸውን ይገልጻሉ። ከዚህም ሌላ በዲሞክራሲያዊ አሰራርና በቅንጅት አለመኖር የተነሳ ችግሩ መጋጋሉን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይናገራሉ። መንግስት የረሃብተኛውን ቁጥርና አደጋ ያንዣበባቸውን አካባቢዎች በትክክል አለማወቁም አስደንጋጭ ዕውነታ ነው ሲሉም እነዚሁ ወገኖች ስጋታቸውን አበክረው ይገልጻሉ።

ለረሃብተኛው ሕዝብ ዕርዳታ ለማሰባሰብ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ስለመሆኑ መንግስት ቢያሳውቅም የዕርዳታው መጠን ከዕርዳታ ፈላጊው ጋር ጨርሶ እንደማይመጣጠን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ባለሙያዎች ይናገራሉ። ከዚህም ሌላ በዕርዳታ ማሰባሰቡም ሆነ የማከፋፈል ተግባር ላይ በመንግስት ላይ አመኔታ የማጣት አዝማሚያዎች በግልጽ ይንፀባረቃሉ።





በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት አስተባባሪነት ከነጋዴዎች ዕርዳታ ለማሰባሰብ በተካሄደ አንድ ስብሰባ ላይ ይህ ሁኔታ ጎልቶ ተንፀባርቋል። የንግዱ ሕብረተሰብ አሁን በአገራችን የተከሰተው ረሃብ መነሻዎቹ 80% ሰው ሰራሽና የመንግስት ፖሊሲ ስህተት ናቸው ባይ ነው። አያይዞም የምንረዳው ማንና እነማን መሆናቸውን ማወቅ ስለሚያስፈልግ የንግድ ም/ቤቱ በሚያቋቁመው ኮሚቴና በራሱ መንገድ ለረሃብተኛው ዕርዳታውን ለማከፋፈል ውሳኔ ላይ ደርሷል። በዚህ ስብሰባ ላይ ከተሰነዘሩት አስተያየቶች አዲስ አበባ አንድ ኩንታል ጤፍ 320 ብር እየተሸጠ አሥመራ ላይ ግን 260 ብር የመሸጡ እንቆቅልሽ ዕርዳታ መስጠት ብቻም ሳይሆን በማከፋፈሉም ላይ የቅርብ ክትትል ያስፈልጋል በማለት ጠቁመዋል። ይህ ሁኔታ በረሃብተኛው ስም የሚሰባሰበው ዕርዳታ በኢትዮጵያ መንግስት የኤኮኖሚና የፖለቲካ ተቋሞች ላይ ከፍተኛ የበላይነት እንዳላት ለሚነገርላት ኤርትራ ሊጓጓዝ ይችላል ከሚል ጥርጣሬ የመነጨ እንደሆነ ይታወቃል።

የአሜሪካን መንግስት ከለገሰው 81,700 ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የተረከበው 81,300 ቶን ብቻ መሆኑን አንድ የዜና ምንጭ ጠቅሶ 400 ቶን ያህል የምግብ ዕርዳታ የት እንደገባ አልታወቀም ሲል በሚላከው ዕርዳታ እህል ላይ ዘረፋ ሳይካሄድ እንደማይቀር ስጋቱን ገልጧል። በተያያዘ ዜና ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሚጫነው እህል መጠን ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣቱን ሌላ አንድ የዜና ምንጭ ጠቅሶ ከደብረዘይትና ከዱከም አካባቢ በሳምንት ከ2000-2500 ኩንታል ጤፍና ጥራጥሬ በኤርትራውያን ነጋዴዎች እየተገዛ ወደ ኤርትራ ተልኳል ሲል ዘግቧል። በሌላ በኩል የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት በረሃብ የተጎዱ ወገኖችን ለመርዳት ለመንግስት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። ይሁን እንጂ በመንግስት ተቀባይነትን ባያገኝም እንኳ ሕዝቡን በማስተባበር ወገን የማዳን የዜግነት ግዴታውን እንደሚቀጥልበት ም/ቤቱ አሳውቋል።

---

(ከገጽ የዞረ)

ለሕገመንግስታዊ ጉባኤ አባላት ምርጫ ማስፈፀሚያ 41 ሚሊዮን ብር መመደቡን ከመንግስታዊ ምንጮች የተገኘው ዜና ያረጋግጣል። ኢሕአዴግ ስልጣን የያዘበትን የግንቦት 20 በዓልን ለማክበርና የሕገመንግስት ጉባኤ አባላትን ምርጫ ለማካሄድ የተደረገውን ከፍተኛ ዝግጅትና ወጪ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች በረሃብ ስቃይ በሞት አፋፍ ላይ በሚገኙበት ሁኔታ መሆኑን አስመርኩዘው ተቃዋሚ ወገኖች በምሬት ይቃወሙታል።በአዲሲቱ ነፃ አገር ኤርትራ ከ21 ሚሊዮን ብር በላይ የሚፈጅ የሕገመንግስት ማርቀቅ ተግባር ሊጀመር መሆኑና በዶ/ር በረከት ሀ/ስላሴ የሚመራ ሕገመንግሥታዊ ኮሚሽን መቋቋሙን በአንድ የዜና ምንጭ ይፋ ሆኗል። ዶ/ር በረከት ሀ/ስላሴ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነመንግስት ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው ሲሆኑ በአንድ ወቅት ደርግ ባቋቋመው የመርማሪ ኮሚሽንም ውስጥ በአባልነት መሥራታቸው ይታወሳል። አዲሱ የኢትዮጵያ ሕገመንግስት ቁልፍ የሆኑ ኃላፊነቶችን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጥ በመሆኑ ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣን ሳይጨብጡ እንደማይቀር ይገመታል።

## TASTE OF ETHIOPIA

**ETHIOPIAN CUSINE**

197 Auburn Av.
Atlanta, GA 30303
(404)681-9406

**ባህላዊ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት**

በንጹህ ጤፍ እንጀራ
ምሳና ራት
ምሳ - ከ$4 እስከ $6 ብቻ
ራት - ከ$4 እስከ $6 ብቻ
(ለልዩ ዝግጅት ዋጋችን ለየት ሊል ይችላል)
የምግባችንን ጣዕም ይወዱታል!
ዋጋችንም ርካሽ ነው!
ብቅ ይበሉ!

LUNCH $4.00 TO $6.00
DINNER $4.00 TO $6.00
*(Special order price may vary from the above.)*
Open 11:00 A.M. to 11:00 P.M. 7 days a week

## ኢንተርናሽናል ፊልምና ቪዲዮ
## International Film & Video

**ታደሰ አስራት**
*Tadesse Asrat*


የጋብቻ ሥነ ሥርዓትን
ክርስትናና ልደትን እንዲሁም ቤተሰብዎን
በቪዲዮ ለማስቀረጽ ከፈለጉ

I F V



በስልክ ቁጥር
*(404) 377-4058* ደውሉልኝ።

ከኢትዮጵያ የመጡ ቪዲዮ ቴፖችን ወደ
አሜሪካን ሲስተም በተጨማሪ የአሜሪካን ቪዲዮ
ቴፖችን ወደ ኢትዮጵያ ሲስተም መቀየር
ይቻላል።




## RE/MAX®
**today's inc.**
an independent member broker

*ቤት መግዛት ለምትፈልጉ*
*መሬት ገዝታችሁ መሥራትም*
*ሆነ Subdivision ውስጥ ለማሠራት የምትፈልጉ*
*ሁሉ ደውሉልኝ እረዳችኋለሁ።*

የክሬዲት ሆነ የሥራ ማጣት ችግር
ቢኖርቦትም ጭንቀት የለም ወገኖች
ደውሉልኝ።

ሁልጊዜም ኮሚሽን የምከፈለው
በሚሸጠው ሰው ነው።

WOW!
YO! YO!



*Have Cash?*
*Bad Credit?*
*No Job?*
*No Problem*
*Just Call me.*

- *Residential*
- *Commercial*
- *Business*
- *Relocation*
- *Forclosures*
- *HUD*



*Selamawit "Sammy" Tadesse*
*Realtor*

**ሰላማዊት ታደሰ**

*Remax Today's Inc*
*1597 Phoenix Blvd. Suit - 5*
*College Park, GA 30349*

*Tel - (404) 907-0525*
*or 907-0183*
*Fax - (404) 907-0524*

# የጎሣ ፍጅትና የመሣሪያ ንግድ በሩዋንዳ

ከሰይፉ መኩሪያ

በምዕራብ ሩዋንዳ ዙሪያ አቋርጦ ደቡብ ዩጋንዳን ጨረፍ ያደርግና በታንዛኒያ በኩል ወደ ቪክቶሪያ ሀይቅ ውስጥ የሚፈሰው የካጌራ ወንዝ የሬሳ መከማቻ ሆንዋል። የጐሣ ፍጅት የሚካሄድባቸውን አካባቢዎች እያቋረጠ የሚጓዘው ካጌራ ወደ አስር ሺህ የሚሆን ሬሳዎችን እየጠራረገ ወስዶ ቪክቶርያ ሀይቅ ሲያራግፍ በየጠርዙና በየጥሻው እየተዝረከረከ የቀረው ሬሳ አካባቢውን የአውሬና የውሻ መፈንጫ አድርጐታል። የዩጋንዳ መንግሥት የጉዳዩን አስጊነት በመገንዘብ የዕዳት ዘመቻ መጀመሩንና የሬሳ ሥጋ ለመብላት የሚርመሰመሱትን አውሬዎች በጥይት እንዲደበደቡ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ዘቦች ማቆሙ ታውቋል።

በዘር ወይም በጐሣ ልዩነት ላይ የተመሠረተ መንግሥት ይዋል ይደር እንጂ ግዜውን ጠብቆ ፍርስርሱ እንደሚወጣ የሳውዝ አፍሪቃና የሩዋንዳ ሁኔታዎች መስክረዋል። በጐሣ ተከፋፍሎ ፍጅት ማካሄድ ውጤቱ ምን እንደሚሆን በጉልህ ያሳየን የሩዋንዳው ግድያ ወደ 200 ሺህ ሕይወቶችን ሲያወድም አንዳንድ ታዛቢዎች ዕልቂቱን 'የጥቁር ሕዝብ ዕድል' ብለው ሲጠሩት፣ ሌሎች የፍጅቱን አሰቃቂነት እየጠቀሱ "ታዲያ ይህ ሕዝብ በነጭ መገዛት ይነሰውን?" በማለት ይጠይቃሉ። የጐሣ አለመግባባት ትውስ የሚላቸው አንዳንድ አፍሪቃውያኖችም የሩዋንዳው ፍጅት 'ነግ በኔ' እንዳይሆንባቸው በሥጋትና በአንክሮ የራሳቸውን ሁኔታ ያጤናሉ። ከሩዋንዳ ምን ትምህርት መቅሰም ይቻላል?

የሩዋንዳው ፍጅት በውስጡ የተለያዩ ነገሮች ያዘለ ሲሆን፣ ቀረብ ብለው ሲያጤኑት የዘር አድልዎና የጐሣ ቅሬኔዎች እየተባባሱ ሄደው ቀስ በቀስ የውጪ ኃይሎችንም እያካተቱና የግድያ መሣሪያዎች እያካበቱ ሁኔታውን አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዳደረሱት እንረዳለን። በሩዋንዳ ለሚኖሩት የሁቱና የቱትሲ ጐሣዎች መጨፋጨፍ ተጠያቂው የአገሪቱ መሪዎችና ተቃዋሚዎቻቸው ቢሆኑም፣ ሁኔታውን በማባባስና ትጥቁን በማቅረብ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባቸው ሌሎች የውጪ መንግሥታት መኖራቸውንም እንገነዘባለን።

## የሁቱና የቱትሲ ጐሣዎች፤-

የሩዋንዳ ሕዝብ 14% የቱትሲ ተወላጅ ሲሆን የተቀረው 86% የሁቱ ተወላጅ ናቸው። ሁለቱ ወገኖች መቃቃር የጀመሩት በአስራ ሰባተኛው መቶ አመት የሩዋንዳ Kingom አገሪቱን አደራጅቶና ከፋፍሎ መግዛት ከጀመረ በኋላ መሆኑን አንዳንድ ጸሐፊዎች ይናገራሉ። በዛ ግዜ ከፍተኛ ሥልጣን የያዙትና የመንግሥት ተጠሪ የነበሩት የቱትሲ ተወላጆች ሲሆኑ የተቀረው ሕዝብ (ማለትም የሁቱ ተወላጅ) በድህነት እርሻ ላይ የተሰማሩ ነበሩ። ይህ በይዘቱ የመደብና የጐሣ ቅራኔዎች ያዘለ ችግር ቢሆንም ቅሉ ብዙ ጸሐፊዎች በሁለቱ መሐል ያለው ግጭት የብሔር (Tribe) ግጭት ከመሆን ይልቅ የጐሣ (Ethnic) ግጭት መሆኑንና በአጠቃላይ ሲታይ የሶሻል ግጭት መልክ ያለው ነው ይላሉ። ሥልጣኑን የያዙት የቱትሲ ተወላጆች በግብርና ሥራ ላይ የተሠማሩት የሁቱ ሰዎችን ይንቃሉ።

በ1961 ዓ/ም የሩዋንዳው Kingdom ይገለበጥና በሁቱ ተወላጆች የሚመራ መንግሥት ሥልጣኑን ይይዛል። ይህ አዲስ መንግሥት ገና ሥልጣን ላይ እንደተቀመጠ ከገለበጣቸው የቱትሲ መሪዎች ውስጥ ሀያውን ይገላል። ወዲያውኑ ተያይዞ የተስፋፋው ግድያ በየሰፈሩና በየመንደሩ በመግባት ሃያ ሺህ የሚሆኑ የቱትሲ ተወላጆች ይገደላሉ። አዲሱ መንግሥት ከዚህ ግድያ በኋላ አገሪቱን ለአስራ ሁለት ዓመቶች ሲገዛ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቱትሲዎች አገራቸውን ጥለው ወደዩጋንዳ ይሰደዳሉ።

በ1973 ዓ/ም በተካሄደው የሥልጣን ለውጥ፣ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትና የሁቱ ተወላጅ የሆኑት ሀብያሪማና ፕሬዚዳንት ሆነው ሥልጣኑን ይጨብጣሉ። ጊዜና የፖለቲካው ችግር እየጨመረ ሲሄድ ሀብያሪማና አገራቸውን ለማስተዳደር ባለሁለት ጭንቅላት ፖሊሲ ለመከተል ይሰናዳሉ። ለዚህ ዓላማ በቁጥጥራቸው ስር ያሉትን ሁለት የፖለቲካ ቡድኖች እንዳስፈላጊነቱ በመጠቀም ባንድ በኩል ለውጪው ዓለም ሰላምን ፈላጊ ሆነው ሲቀርቡ፣ በሌላ ወገን ጠላቶቻቸውን መግደል፤ ሕዝብን ደም ማቃባት ቀጠሉ።

በሀብያሪማና ቁጥጥር ሥር የነበሩት ሁለቱ የፖለቲካ ቡድኖች National Republican Movement for Democracy (MRND) እና በሁቱ አክራሪዎች የተገነባው Committee for Defence of Republic (CDR) ነበሩ። የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ በፕሬዚዳንቱ ፈቃድ የመድብለ (multi) ፓርቲ ሥርዓት ተካሂዶ የጥምር መንግሥት (coalition) ሲቋቋም፣ ሁለቱ ቡድኖች የየራሳቸው ሚሊሺያ እንዲያቋቁሙ ተፈቀደላቸው። የጥምር መንግሥት የተባለው ቀስ በቀስ በአንደኛው ቡድን በMRND እየተዋጠ ሄዶ መንግሥታዊ ፖሊሲ በማካሄድ ከቱትሲዎች ጋር ሥልጣን ለመካፈል "ዝግጁ ነኝ" ብሎ ሲቀርብ ሁለተኛው ቡድን CDR ይህንን ድርድር በመቃወም ውስጥ ውስጡን በግድያ ይሠማራል።

የሀብያሪማና አጀማመር ደህና መልክ ነበረው። ገና ሥልጣኑን እንደያዙ ሩዋንዳን ያለ ጐሣዊ አድልዎ ለማስተዳደር ቃል ገብተው ነበር። ቃል ኪዳናቸው ግን አልተጠበቀም። ከፕሬዚዳንትነታቸው ጋር አብሮ የመጣው ነገር የአገሪቱን ሀብትና ቁልፍ የመንግሥት ሥልጣኖች ለፕሬዚዳንቱ ቤተዘመድና ጓደኞች መከፋፈሉ ነበር። ይህ አገዛዝና በየጊዜው የሚካሄዱት ግድያዎች የቱትሲ ተወላጆችን ስላስጨነቃቸው ራሳቸውን በሩዋንዳ ፔትሪዩቲክ ፍሮንት (RPF) ሥር በማደራጀት ለውጊያ ይቀርባሉ።

በ1990 የሀብያሪማናን መንግሥት ለመገልበጥ ግንባሩ ወረራውን ሲጀምር ይህ ሁኔታ ፕሬዚዳንቱን በጣም ስላበሳጫቸው ቶሎ ብለው ለወገኖቻቸው መትረየሶችና ጥይቶች ያድላሉ። የተሰጣቸውን መትረየሶች ደግነውና የፕሬዚዳንቱን ካድሬዎች እይተከተሉ በየመንገዱና በየሰፈሩ በመግባት ሁለት ሺህ የቱትሲ ተወላጆችን ይገድላሉ። የፔትሪየቲክ ግንባሩ በበኩሉ የፕሬዚዳንቱ ደጋፊዎች ናቸው በሚላቸው ሰዎች ላይ ተመሳሳይ ግድያ በማካሄድ የጐሣ ግጭቱን ያባብሰዋል። ይህ ሁኔታ በሁለቱም ወገን የማያስፈልግ ተጽዕኖ በማምጣቱ ሁለቱም ወገኖች ለመነጋገር ይስማማሉ። በመጨረሻም ባለፈው ዓመት August ላይ የሰላም 'ትሪቲ' ይፈራረማሉ።

ሀብያሪማና ከፔትሪየቲክ ግንባር ጋር የተፈራረሙትን 'ትሪቲ' እንዳልፈለጉት ያስታውቅ ነበር። ምንም እንኳ 'ትሪቲው' የሀብያሪማና ፕሬዚዳንትነት እንዲቀጥን ቢፈቅድም ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች ለቱትሲ ተወላጆች RPF እንዲሰጥ ያዝ ነበር። ለምሳሌ የአገር ውስጥ አስተዳደር በፔትሪየቲክ ግንባር ስር እንዲሆን ተብሎ ነበር። ሀብያሪማና የራሳቸው ፕሬዚዳንትነት መቀጠሉ ቢያስደስታቸውም ሌሎች ቁልፍ ቦታዎች ለጠላቶቻቸው መሰጠቱ እያደር ይከነክናቸው ጀመር።

በሥልጣን ማካፈል ወይም በሥልጣን ሽሚያ ግፊት ይህን ያህል ልምድ የሌላቸው ሀብያሪማና ርዳታና ምክር ፍለጋ ወደ ጐረቤት አገሮች ይሄዳሉ። ውስጣዊ ተቃዋሚና ዓለማቀፋዊ ግፊቶችን ማንከረባበት ታላቅ ልምድ ያካበቱትን የዛየሩን ፕሬዚዳንት ሞቡቱ ሴሴሴኮን ሄደው ያነጋግራሉ። የቶጐ ፕሬዚዳንት ናሲምቤ እይዲማንንም እንዲሁ ሄደው ያነጋግራሉ። የተሰጣቸውን ምክር ተመርኩዘው ይሁን አይሁን ባይታወቅም ሀብያሪማና በአንዱ ፓርቲያቸው (MRND) ከግንባሩ ጋራ ሰላምን ሲደራደሩ በሌላኛው (CDR) ሰላምን አፍራሽ ግድያ ቀጠሉበት።

ይህ 'ትሪቲ' ለሩዋንዳ ሰላምን ያስገኛል እየተባለ ሲጠበቅ ሌላ ያልተጸበቀ ነገር ደረሰ! 'ትሪቲው' በተፈረመ በስምንት ወሩ የሩዋንዳውንና የቡሩንዲን ፕሬዚዳንቶች ይዞ የነበረው አውሮፕላን አየር ላይ እንዳለ ብትንትኑ ይወጣል። ሁለቱ ፕሬዚዳንቶችም ሕይወታቸው በዛው ያልፋል። የፕሬዚዳንታቸውን መሞት የሰሙት የሁቱ ተወላጆች ይህን ድርጊት የፈጸሙት ቱትሲዎች ናቸው በማለት እንደገና አዲስ የጐሣ ፍጅት ይጀምራሉ።

## የውጪ መንግሥትና የሩዋንዳው ፍጅት፤-

የሠላሙ 'ትሪቲ' ከተፈረመ በኋላ የሩዋንዳ ችግር የሠላም ካባ ይልበስ እንጂ እንዴ ቦግ እንዴ ጥፍት እያለ ውስጥ ውስጡን ይነድ ነበር። ይህን ዝግ ያለ ሁኔታ በመጠቀም ሁለቱም ወገኖች ራሳቸውን ለማጠናከር የወታደራዊና የዲፕሎማዊ ሥራዎችን በሰፊው ተያይዘውት ነበር።

በተለይ መሣሪያ አቅራቢ ናቸው ከሚባሉ የውጪ መንግሥታቶች ጋር የሩዋንዳ መንግሥት ጐላ ያለ ግንኙነት ሲያካሄድ ፔትሪያቲክ ግንባሩም የበኩሉን ከማድረግ አልተቆጠበም ነበር። አንድ በሩዋንዳ ላይ የቀረበ ዘገባ ሩዋንዳ ውስጥ የሚካሄደው ፍጅት ውስጥ የውጪ መንግሥታትና ዓለም አቀፋዊ መሣሪያ ሻጮችም እጅ እንደገባበት ይነገራል። በሩዋንዳ ፍጅት እጃቸው በደም ተበክሏል በመባል የሚጠቀሱት አገሮች ራሺያ፣ ሩማንያ፣ ምስራቅ ጀርመን፣ ዩጋንዳ፣ ግብፅ፣ ሳውዝ አፍሪቃና ፈረንሳይ ናቸው።

## የድሮ ሶሻሊስት አገሮች፤-

ከበርሊን ግንብ ፍርስራሽ ጋር እንደ አፈራ የተነነው የሶሻሊስት ስርዓትና ግዛት ከሚታወቅባቸው ዝናዎች አንዱ የወታደር ትጥቅና መሣሪያዎችን በገፍ ማምረት ሲሆን፤ ሶሻሊዝም ድምጥማጡ ሲጠፋ እነዚህ የወታደር ትጥቅና መሣሪያዎች ግን አብረውት አልጠፉም ነበር። በየጦር ፋብሪካውና በየመጋዘኑ የተቀመጡት የግድያ መሣሪያዎችና ትጥቆች ገዥና ወሳጅ እስከመጣላቸው ድረስ ታሽገው ተቀምጠዋል። ሶሻሊዝም ውሃ ሲሆን በነዚህ አገሮች ውስጥ ሰፍኖ የነበረው አለመረጋጋትና የውጪ ምንዛሪ ጥማት የመጋዘኖቹን በር በመክፈት የድሮ ሶሻሊስት አገሮችን የመሣሪያ ቸርቻሪነት ይፋ አወጣው። ይህንኑ በሚመለከት የተጻፈ አንድ ዘገባ፣ ብዛቱ ይህ ነው ሊባል የማይቻል የካላሽንኮቭና የወታደር መሣሪያዎች በተለይ የምሥራቅ አፍሪካን አካባቢ እንዳጥለቀለቀው ጠቅሶ ይህ የመሣሪያ ግዢ ሊከናወን የበቃው ቤልጅየም ውስጥ የሚኖሩና ትውልዳቸው አፍሪቃዊ የሆኑ ደላሎች ባካሄዱት ግንኙነት መሆኑን ገልጧል። በማያያዝም በተለይ ሩዋንዳ ውስጥ አለ የሚባለው የካልሽኮቭና የሌሎች መትረየሶች ብዛት አገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት የብስክሌቶች ቁጥር መብለጡንም ጠቅሶ የፔትሪያርክ ፍሮንት ሙሉ ትጥቁ የመጣው ከሩማንያ ሲሆን ዋና መሣሪያው ከላሽንኮቭ መሆኑን አጋልጧል።

## ግብፅና ፈረንሣይ፤-

የድሮ ሶሻሊስቶች የመሣሪያ ሽያጩን ቢያጧጧፉትም ቅሉ የሩዋንዳውን ፍጅት በይበልጥ ደም በደም ያደረገው ከግብፅና ከሳውዝ አፍሪቃ የተገዙት መሣሪያዎች ናቸው። "አቅራቢና ገዢ ይህንን ስምምነት ለሌላ ሦስተኛ አካል እንዳያካፍሉ" የሚል ስምምነት የተጻፈበት የሽያጭ ውል ላይ በመፈረም ስድስት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሣሪያ ሩዋንዳ ከግብፅ ገዝታለች። ይህ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ላይ ነበር። በተጨማሪም ከስድስት ወር በኋላ (Oct. 1992) ሌላ ስድስት ሚሊዮን ዶላር አካባቢ የሚያወጣ መሣሪያ ሩዋንዳ ከሳውዝ አፍሪቃ ላይ ገዝታለች።

ሩዋንዳ ከግብፅ የገዛችው መሣሪያ ሊገኝ የተቻለው በክፍያ ሳይሆን በዱቤ ነበር። ለክፍያው ዋስ ሆኖ የቀረበው አንድ የፈረንሳይ ባንክ ነበር። ስምምነቱም ሩዋንዳ በመጀመሪያ አንድ ሚሊዮን ልትከፍል፣ በቅጣዩ ዓመት እምርታ ለዓለም ገበያ ከምታቀርበው የሻይ ቅጠል ሽያጭ ላይ ሌላ ሚሊዮን ዶላር ልትጨምር፣ ከዚያ በኋላ ለአራት ዓመቶች በያመቱ አንድ ሚሊዮን በመክፈል ዕዳዋን እንድትጨርስ የሚል ነበር። የሩዋንዳ ችግር ገና ሳይለይለት ይህን ለመሠለ የማያስተማምን ዕዳ እሺ ብላ ዋስትና በመቆም ፈረንሳይ ለሩዋንዳ "'ድብቅ' የመሣሪያ ዕርዳታ" መስጠቷ ነው በማለት አንዳንድ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ሆኖም ሩዋንዳና ፈረንሳይ ያልጠበቁት ነገር ቢኖር ፔትሪያቲክ ፍሮንቱ በአዲስ ኃይል ወረራውን አካሂዶ የሻይ እርሻውን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ መቻሉን ነበር። ምርቱ በጦርነት ሳቢያ ተበላሽቶ መና ሲቀር ፈረንሣይ በሕግ ዋስትናዋን እንድታሟላ የምትጠየቅ ሆነች።

ጦርነቱ እንደተጀመረ በሴንትራል አፍሪቃ ሪፓብሊክ ውስጥ ካሰፈረቻቸው ሠራዊቶች ውስጥ ሦስት መቶውን ወደሩዋንዳ በማስገባት ሁኔታውን በቅርብ ስትከታተል ቆይታ ተጨማሪ ሠራዊት እንደገና በማስገባት እነሆ ዛሬ ስምንት መቶ የሚጠጉ የፈረንሣይ ወታደሮች ሩዋንዳ ውስጥ ሰፍረዋል። ፈረንሳይ ለዚህ ሥራዋ ምክንያቴ ነው ብላ ያቀረበችው "የዜጐቼን ደህንነት ለመጠበቅና " "ዩጋንዳ ሩዋንዳን ትወራለች ብለን ስለምንሰጋ ሩዋንዳን ከወረራ ለማስጣል ነው" የሚል ነው። አንዳንድ ታዛቢዎች ፈረንሣይ በ'ፍራንኮፎን' አፍሪቃ ውስጥ ስሟን ለማስከበርና በተለይም ዛየር ውስጥ አለሁ ባይነቷን ለማጠናከር የወሰደችው እርምጃ የሩዋንዳን ሁኔታ ያባብስ እንጂ አያቀዘቅዘውም ይላሉ።

## ዩጋንዳ፤-

የሩዋንዳ ጐረቤት የሆነችው ዩጋንዳ በቱትሲ ለሚመራውና አሁን ጦርነቱን በማፋፋም ላይ ለሚገኘው ፔትሪያቲክ ፍሮንት ድጋፍዋን ሰጥታለች። የዩጋንዳ ፕሬዚዳንት ሙሴቪኒ ስልጣኑን ከሚልተን ኦቦቴ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ከመንጠቃቸው በፊት ባካሄዱት ትግል የሩዋንዳ ፔትሪያቲክ ፍሮንት ከጐናቸው በመሰለፍ የትግል ዕርዳታ ያደረገላቸው ድርጅት ነው። አገራቸው ውስጥ የሚደረገውን ግድያና አድልዎ በመሸሽ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሩዋንዳ ዜጐች መሰደዳቸውና ከነዚህም ውስጥ አብዛኞቹ በዩጋንዳ መስፈራቸው ሲታወቅ ብዙዎቹ ለዩጋንዳ ሠራዊት በወታደርነት ሲያገለግሉ የቆዩ ናቸው። ለምሳሌ ያህል የፔትሪየቲክ ግንባር መሪ ፓል ካጋሜ የዩጋንዳ መረጃ ክፍል ሀላፊ ጄኔራል ነበር። እነዚህ የቱትሲ ተወላጆች ናቸው ፕሬዚዳንት ሀብያሪማናን ለመገልበጥ የተነሳሱት። የቱትሲዎቹ ዓላማ ለዩጋንዳ ግልፅ ነበር። ፔትሪየቲክ ፍሮንት ተዋጊዎች ወረራውን ከመጀመራቸው በፊት ዘመዶቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ለመሰነባበት በዩጋንዳ ከተሞች ውስጥ ከነትጥቃቸው ይዘዋወሩ እንደነበርና በመጨረሻም አንድ የእግር ኳስ ስታድዮም ውስጥ ተሰባስበው መመካከራቸውን አንድ ዘገባ ጠቅሷል። ይህ ዘገባ አያይዞም የዩጋንዳው ፕሬዚዳንት ሙሴቪኒ የፈረንሣይ ባለሥልጣኖች እንደሚገምቱት ሩዋንዳን የመውረር ፍላጐት እንደሌላቸው ገልጦ፣ የሙሴቪኒ ምኞት በትግል የተባበሯቸው የቱትሲ ተወላጆች ሥልጣን እንዲይዙላቸው ነው ብሏል። የዩጋንዳ ዕርዳታ ዋነኛ መሆኑን ከጦርነቱ ሂደት መገንዘብ ይቻላል። ምግብ፣ መጠለያ፣ ነዳጅ፣ ጥይትና 'ባትሪ' የሚጐርፈው ከዩጋንዳ መሆኑ ታውቋል። ሆኖም ባለፈው ወር ፕሬዚዳንት ሙሴቪኒና የአሜሪካው የውጪ ጉዳይ ረዳት ሚኒስትር የሩዋንዳን ፍጅት እንደሚቃወሙና፣ ግድያውና ተኩሱ ታግዶ የዕርዳታ መስጫ መንገዶች እንዲከፈቱ የሚጠራ የጋራ መግለጫ ማውጣታቸው ታውቋል።

## ደቡብ አፍሪቃ:-

የደቡብ አፍሪቃ አካባቢ አገሮችን በልዩልዩ የጦርና የኢኮኖሚ ተጽዕኖዎች ይረብሽ የነበረው የሳውዝ አፍሪቃ አፓርታይድ መንግሥት አንዱ የመሣሪያ ሽያጭ ነበር። በአፓርታይድ መንግሥት ስር ይተዳደር የነበረው የመሣሪያ ፋብሪካ -Armscor- በ1992 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ ስድስት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሣሪያ ለሩዋንዳ መሸጡን ጠቅሰናል። Armscor ወደፊት በአፍሪካ ውስጥ ምን ዓይነት ሚና እንደሚኖረው የታወቀ ነገር ባይኖርም ሳውዝ አፍሪቃ ውስጥ በመጣው የመንግሥት ለውጥ አሰራር Amscor ከመንግሥታዊ ድርጅትነት ተላቆ ወደግል ድርጅትነት እንደሚቀየር የሚጠባበቁ አንዳንድ ታዛቢዎች፤ መሣሪያ የሚያመርት የግል ድርጅት ምርቱን ለመሸጥ ሲል በየሽኩቻውና በየግርግሩ እጁን ከማስገባት እንደማይቆጠብ ጠቅሰው (ይህ ከሆነ) ሁኔታው ለአፍሪቃውያኖች ደም መፋሰስ አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይናገራሉ።

## የተባበሩት መንግሥታት፤-

የሩዋንዳ መንግሥትና የፔትሪየቲክ ፍሮንት የተፈራረሙት 'ትሪቲ' 'የአሩሻ ስምምነት' በመባል ይጠራል። ከዚህ የ'አሩሻ ስምምነት' በኋላ የተ.መ.ድ. የሰላም ጠባቂ ኃይሎች በሩዋንዳ ሰፍረው ነበር። ከዚህ በፊት በሶማሊያ ውስጥ ጣልቃ ገብ ሆኖ የደረሰበትን ውርደትና ሽንፈት ለመሸፈንና የወደፊት ስሙን ለመጠበቅ የአሩሻው ስምምነት ለተባበሪት መንግሥታት ጥሩ ዕድል ከፈተለት። ይህንን ለመገንዘብ ስምምነቱን ያላንዳች ችግር በሥራ ለማዋል ተ.መ.ድ. ተስፋ ነበረው።

ሩዋንዳ ሕልውናዋን በሚመለከት ከተ.መ.ድ. ጋር ስትገናኝ ይህ የመጀመሪያው አልነበረም። ከ1899 ዓ.ም. እስከ 1916 ድረስ የጀርመን ቅኝ ግዛት

ሆና ከኖረች በኋላ በሊጋ ኦፍ ኔሽን (የተመድ ቀዳሚ ድርጅት) ትዕዛዝ መሠረት በቤልጂየም ስር እንድትደዳደር ተደርጎ ለአርባ አምስት/ስድስት ዓመታት በቤልጂየም ሥር ከቆየች በኋላ በ1962 ላይ ነፃነቷን ያገኘች አገር ናት።

የዘንድሮው የተ.መ.ድ. ሚና በሰላም ጠባቂዎች አማካይነትና በተዋጊዎች ስምምነት ለሩዋንዳ ሰላምን ማግኘት ሲሆን ከልዩ ልዩ አገሮች ተውጣጥቶ የመጣው የ'ሰላም ጠባቂ ኃይል' እርስ በርሱ ለመነጋገር የቋንቋ ችግር ብቻ ሳይሆን የሩዋንዳን ኦፊሲያላዊ ቋንቋ ፈረንሳይኛን እንኳ መጠቀም የሚችል አልነበረም። የሀብያሪማና አውሮፕላን ብትንትኑ ሲወጣ የተጀመረው የጉሣ ፍጅት የተካሄደው የተ.መ.ድ. 'ሰላም ጠባቂ' ወታደሮች ዓይን ስር መሆኑን አንዳንድ ዘገባዎች ጠቅሰዋል። "ከላይ የተላለፈልን ትዕዛዝ ስለሌለ አንድችም የጥበቃም ሆነ የመከላከል ሥር ማካሄድ አንችልም" በማለታቸው ለሩዋንዳው ደም መቃባት አስተዋጽዖ አድርጓል በማለት ተ.መ.ድ.ን የሚወነጅሉ ዘገባዎች ቀርበዋል።

በአሁኑ ሰዓት የፔትሪየቲክ ግንባር ኬጋሊን ከዛሬ ነገ ይይዛል እየተባለ ይጠበቃል። ተ.መ.ድ.ም ተጨማሪ የሰላም ጠባቂ ወታደሮች እንደሚልክ በተወሰነው መሠረት የተለያዩ የአፍሪቃ አገሮች ወታደሮቾ እንደሚያቀርቡ ቃል ገብተዋል።

አብዛኞቹ የየራሳቸው አገር ውስጥ የጐሣና የሃይማኖት ግጭት ያሉባቸው አገሮች ሲሆኑ ይህን ከመሰለ "ሰላም ጠባቂ" ኃይልና ተ.መ.ድ.ን ከመሰለ የጦር አዛዥ ሊገኝ የሚችለው ውጤት ዘለቄታ ይኖረዋል ለማለት ያዳግታል። የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ለሆሳስ በሆነበት በአሁኑ ወቅትአፍሪቃዊውን ችግር በአፍሪቃዊ 'ሰላም ጠባቂ' ለመፍታት መወሰኑ ጥሩ ቢመስልም ዘለቄታዊነት ያለው መፍትሔ ለማምጣት አፍራቃዊ አመራር ስለሌለበት የሱማሌን መሳይ ውጣ ውረድ አይመጣም ብሎ ለመናገር አይቻልም። በቅርቡ የወጣ አንድ ሪፖርት፣ ይህ ጉዳይ ያሳሰባቸው የዚምባቡዌው ሮበርት ሙጋቤ የአፍራቃ አንድነት ድርጅት ሩዋንዳን ዝም ብሎ መመልከቱ ድርጅቱ እንደሚጠየቅበትና ይህንንም ጉዳይ በቱኒዙ ስብሰባ ላይ ራሳቸው እንደሚያነሱት መናገራቸውን ገልጿል።

የሩዋንዳ ፍጅት ቀኑን ጠበቆ እንደሚረጋጋ ቢታመንም ቅሉ ፍጅቱ በሩዋንድ ዜጐች አዕምሮ ውስጥ ጥሎት የሚያልፈው የጥላቻና የጐሰኝነት ስሜት ስር የሰደደ እንደሚሆንና የሩዋንዳ ሕዝቦች ወደፊት ገና ብዙ ውጣ ውረድ እንደሚገጥማቸው የተከታተልኳቸው ዘገባዎች ይደመድማሉ።

---

የዚህ ዘገባ አቅራቢ ሰይፉ መኩሪያ በአትላንታ ከተማ የሚኖሩ 'ፍሪላንስ' ጋዜጠኛ ናቸው።

---


# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ

## We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices

***We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !***

| DESCRIPTION | QTY(lb) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Miten Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME______________
ADDRESS______________
______________
CITY______ ______
STATE________ZIP________
Tel. ( )______________

**WE DO MAIL ORDER**

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23

# ጥ ን ቅ ር

## ከዚህም ከዚያም

( ወርቃየሁ ከአ/አ ያጠናቀረው)

በዚህ ዓምድ ስር ከተለያዩ የአገር ውስጥ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና ሕትመቶች የተሰባሰቡትን የሕዝብ ብሶቶች፣ ሹክሹክታዎች፣ አሽሙሮች፣ ፌዞችንና ቁምነገሮችን በማሳጠርና በማጠናቀር አቅርበንላችኋል።

## የአራዳ ሹክሹክታ

"ይሄ የሊዝ ገንዘብ አሰባሰብ ጉዳይ አይገርምም? ለ99 ዓመት ማከራየት ከዚያም 1/3ኛውን አሁኑኑ መቀበልና አዲስ አበባን ቶኪዮ ማድረግ። ጥንት በነበረው መንግስት ግብር በየአመቱ ይሰበሰባል። አሁን ግን የ99 ዓመቱን 1/3ኛ የ33 ዓመቱን አንድ ጊዜ ተቀብሎ የሚቀጥለው መንግስት በምን ሊጠቀም ነው? ወይስ ገንዘቡን ሰብስቦ ወዴት ለመሄድ?"

## ? ? ? አንድ ጥያቄ አለኝ ? ? ?

* በውኃ ጥሙ ስናማርር መብራቱም ተጨምሮ ፅልመት ውጦናል። ከእንግዲህ የቀረን ደግሞ ምን ይሆን?
አበበ - ከፈረንሳይ ለጋሲዮን
** የመጣውን ለመቀበል ሴሚናር።

* መነኩሴው አውቶማቲክ ከታጠቁ እኛ እንዴት ልንሆን ነው? በላቸው - ከኡራኤል
** ምሽግ ያብጁ።

* ከደባሌ የአይን ፍቅር ይዞኛል እንዴት አድርጌ ልንገረው? ፋንታዬ - ከቃሊቲ
** አይንሽ ምን ይሰራል?

* አብዮት ልጆቿን ትበላለች ሲባል ነበር። ዴሞክራሲ ደግሞ ምኗን ትበላ ይሆን?መኑር ከ4 ኪሎ
** ምናልባት እራሷን።

* በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም የሚለው ተረት መቼ ነው የሚደርሰው? ይትባረክ - ከአዋሽ
** ቁናው ከሄደበት ሲመለስ።

* ጂሚ ካርተር የእምባ ጠባቂ ተቋም የሚያቋቁሙልን ምን ለመሆን ፈልገው ነው? የሺመቤት - ከአዲስ አበባ
** እስከዛሬ ያለቀሱትን ለማባበል ነው።

* የፍትሕ ሚኒስትሩ 3ቱን ዓመት ሲዘክሩ "ወርቃማው ዘመን" ብለውታል እናንተስ ምን ትሉት ይሆን? አለም - ከፈረንሳይ ለጋሲዮን
** ዘመነ ጅራፍ ብለነዋል። አቅምሰውን የለ!!

* አዳሜ እየተነሳ "ግልጽ ደብዳቤ ለፐሬዚዳንት መለስ" ይላል። እሳቸው ለግልጹ ደብዳቤ መልስ የሚሰጡት መቼ ነው? ሐብታሙ - ከዲላ
** ምናልባት ከምርጫው በኋላ "በሚገባቸው ቋንቋ"

* "ወንዱን ወንድ አማረው" ያላችሁት የማንን ሞራል ለመንካት ነው? የሺመቤት - ከአዲስ አበባ
** ቆሞ የሚሸናውን።

* ወገን በረሃብ በሚቀጠፍበት በዚህ አስከፊ ዘመን ፒያሳ ቬርሙዳ ውስጥ ውስኪ እየተራጩ ከበሮ የሚደልቁትን ምን እናድርጋቸው? ደንድር - ከፒያሳ
** አይዞህ! ከበሮውም ይቀደዳል። ጠርሙሱም ይሰበራል።

* የወያኔን ሶስተኛ ዓመት ንግሥ ለማክበር የተለጠፉትን ፖስተሮች ሌሊቱን ቀዶ የጨረሰው ማን ይሆን? ፀጋዬ - ከጎንደር
** ለዚህች ለዚህችማ ወንድ ይጠፋል ብለህ ነው?

* የዘንድሮ ግንቦት ሃያ እንዴት ይከበር ይሆን? ሳምሶን - ከሞጆ
** ግማሹ በከበሮ "ደርብ" እያለ ግማሹ በጠኔ እየተጠራሞተ ነዋ።*

* እናታችንን ከሚገዛትና ከሚሸጣት የቱ ይበዛል? ከልጆቿ - ኢትዮጵያ
** የሚያስማማት።

* የኤርትራ ባለስልጣኖች ትናንት ሲያወግዟት ወደነበረችው ኢትዮጵያ የሚያመላልሳቸው ምን ይሆን? አሊ - ከደሴ
**ለጥገቷ አሞሌ ጨው እያመላለሱ ሳይሆን ይቀራል?

*በአዲስ አበባ ስንት የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ይኖሩ ይሆን? ቀለሟ - ከአየር ጤና
** የግንቦት ሃያን ሰልፍ አላየሽም?

* የትምህርት ፖሊሲው ተቃውሞ በዛበት የምትሉት ወሬ አጥታችሁ ነው?
ሙናዬ - ከአዲስ አበባ
** እርሶ ደግሞ ስንተኛ ክፍልና የማን ዘመድ ቢሆኑ ነው የቆረቆሮት! (ከጦማር የተወሰደ)

## ልብወለድ

# የዴብራ ጦስ

### (በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ)

ከገረሱ

ካለፈው የቀጠለ

## ክፍል ስምንት

ካሣሁንና ፈጠነ ባወጡት ሁለተኛው እቅዳቸው መሠረት ዴብራን ከጓደኛዋ ጋር ለማውጣት ብዙ ዝግጅትም አላስፈለጋቸውም። ፈጠነ ዋናው ዓላማው ጓደኛውን ካሣሁንን ከዴብራ ለማላቀቅና ከኢትዮጵያዊት ሴት ጋር ለማገናኘት ስለሆነ የመጀመሪያው ዕቅዱ እንደተሳካለት ቆጥሮ ስለሁለተኛው ዕቅድ ብዙም አልተጨነቀም። የገባው ቃል በመሆኑና በተለይም ሃሳቡ የመጣው ከሱ ስለሆነ ነው እንጅ ለመሄድ ያሰበው እሱ ቀደም ሲል የነበረውን ግምት የሚያስቀይር ሁኔታ ይኖራል የሚል ጥርጣሬ አልነበረውም።

ከዴብራ ጋር የያዙት ቀጠሮ እንደማምሻው ሆኖ ጠዋት ላይ ካሣሁን ለራሔል ስልክ ደወለ። ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሳ ጀምሮ ነበር ሲያስታውሳት ነበር። ያቺ ሲኒማ ቤት የተሳሳሙት፣ የሷ መቅለስለስ፣ ዝምታዋ ሁሉ እየመጣበት ስላስቸገረው ነበር ስልኩን ያነሳው። እንደ ዕድል ያነሳችው እሷ ነበረች።

"አሎ ራሔልን ነበር እባኮን፤' አለ። የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ በመሆኑና በስልክ ድምጿን ስላለመደው አንስታ "አሎ" ያለችው እሷ መሆኗን አላወቀም።

"ማን ልበል?" አለች፤ እሷም እንዲሁ አላወቀችውም።

"ካሣሁን ነኝ፤" አላት።

"ታዲያስ?" አለችው። ድምጿ ቀየር አለ።

"ሥራ ከመሄዴ በፊት ልደውልልሽ ብዬ ነው፤ ታዲያስ ሥራ እንዴት ነው?" አላት።

"ከልኩ አያልፍም ባክህ፤ ያንተስ እንዴት ነው፤" አለችው።

"ያው ነው ባክሽ፤" አላትና ቀጥሎ የሚላትን ያስብ ገባ። "የዚያን ዕለት እኮ ለብቻችን ስላልነበርን ብዙ አላወራንም፤ ስለኔም ብዙ አልነገርኩሽም።" አለት። አሁን እንኳ ለማውራት ፈልጎ አልነበረም። በዚያው በወረው አመካኝቶ ቀጠሮ ለመያዝ ነበር።

"ወደፊት እናወራዋለን፤ መቼ ጊዜ ይጠፋል ብለህ ነው፤" አለችው።

"ታዲያ ለምን የፊታችን ቅዳሜ ወይም እሁድ እንገናኝም፤" አላት።

"ኡ! ይህን ቅዳሜስ አልችልም።

"እሁድስ ቢሆን፤"

"እሁድም ጉዳይ አለብኝ።" አለችው።

'ይኸው እንግዲህ!' አለ በሆዱ። 'መቼ ይሆን የኛ ሴቶች ስልጠን ብለው ሲጠየቁ እሺ የሚሉበት ጊዜ የሚኖረው። ተለማመጡን! ለምኑን! አንድ ነገር ተጠይቀው ጥቂት ሳይግደረደሩ ምንም ቢፈልጉት እንኳ ቶሎ እሺ አይሉም፤' ዴብራ ትዝ አለችው።

"በይ እሺ እንግዲህ ሲመችሽ ደውይልኝ" ብሎ ተሰናበታት። "ነይ! አትምጭ!" ብሎ አተካራ መግጠም አልፈለገም፤ የምን ልምምጥ ነው!

እሷም ሁኔታው ሳይገርማት አልቀረም። ለማንኛውም "ደህና ሁን!" ብላ ስልኩን ዘጋችው።

መደወሉ አናደደው። ስልኩን ከዘጋውም በኋላ ያለው ነገር ስላልተፈጸመ ጥቂት ይናደድም እንጅ እሷን ማሰቡን አላቆመም። እሷ ካልደወለች እኔ አልደውልላትም ሲልም ወሰነ። ተነስቶም ወደ ሥራው ሄደ።

ማምሻውን በዕቅዳቸው መሠረት ፈጠነ ቀደም ብሎ ካሣሁን ቤት ተገኘ፤ አንዳንድ ጉዳዮችንም ለመመካከር ጭምር።

"ዋናው ነገር፤" አለ የውጪ ሴት በማውጣት ልምዱን ያለው ካሣሁን፤ "ዋናው ነገር ቀልጠፍ ማለት ነው፤ ማወቅ ያለብህና ቀድሜም እንደነገርኩህ ዙሪያ ጥምጥም የሚባል ነገር የለም። ይሆናል! ይሆናል ነው! አይሆንም! አይሆንም ነው። እነሱ መግደርደር የሚባል ነገር አያውቁም፤ ደስ ካለችህ ውበቷን አድንቅላትና ቀረብ በላት፤ ከዚያ ሌላውን ለሷ ተወው፤" አለው። ዴብራን መጀመሪያ ያገኘበት ዕለት የነበረው ሁኔታ ለአፍታ ትዝ አለው።

"ምን ብዬ ነው ውበቷን የማደንቀው ደግሞ?" አለው ፈጠነ።

"እንደኛ ሴቶች የሚንጠባረሩ መሰለህ? ደስ ነው የሚላቸው።" አለ ካሣሁን።

"እባክህ ይህን የኛ ሴቶች፤ የኛ ሴቶች የምትለውን ነገር አቁም። የኛ ሴቶች ውበታቸውን ስታደንቅላቸው ይጠላሉና ነው እንዲህ የምትለው?" ይላል ፈጠነ የካሣሁን ልብ አሁንም ዴብራ ላይ መሆኑ እያሳሰበው።

"ቢገባቸው አይደል! አንዱ የነገረኝን አንዴ ልንገርህ። አንዷን አበሻ ፓርቲ ላይ ያገኛትና ተዋውቋት "ዓይንሽ በጣም ደስ ይላል" ይላታል። መልሷ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? " ማሽሟጠጥህ ነው!" ብላ ዳንሱ ወለል ላይ ጥላው ሄደች። አይገርምም! ይህ ሰው ዓይኗ ማርኮት ይሆናል፤ እሱ ደስ የሚለው ዓይን ይሆናል፤ ታዲያ ይህ ይባላል፤"

"ስማ! አንዷ እንደዚህ አደረገች ብለህ ሁሉንም በዚህ ማማት ደግ አይመስለኝም። በኛ ባህል ደግሞ ይህ አባባል ያልተለመደም ሊሆን ስለሚችልም ይሆናል፤" አለ ፈጠነ።

ካሣሁን እንደ መሳቅ አለ፤ " ስማ ፈጠነ ልምዳችንን ቢገባህና ብታስታውሰው የእኛ ሴቶች የወንድን ወንድነቱን የሚረዱለት ኮራ ሲል ነው። 'ምንትስዬ፤ ቆንጆዬ፤ ስትላቸው ይንቁሃል፤ ወይ እንደቅድሟ ያሉት ደግሞ እንደ ስድብ ይቆጥሩታል፤ እኔ የማውቀው ይህን ነው።"

"ትገርመኛለህ፤ ከመቼ ወዲህ ደግሞ እንዲህ ማሰብ እንደጀመርክ ያላወቅሁ አይምሰልህ" ይላል ፈጠነ።

"ያው እንደ ልማድህ ዴብራን ማውጣት ከጀመርክ በኋላ ልትል ነው፤ መቼ አጣሁት፤' ይላል ካሣሁን።

"የአበሻ ሴት ፈልገህ ማግኘት ካልቻልክበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤ አይ ካስሽ። ደግሞም ዴብራን ለማውጣትህ እንደ ምክንያት አድርገህ ልታቀርበው እንደተነሳህም አድርጌ እቆጥረዋለሁ አንዳንዴ፤" ይላል ፈጠነ በትዝብት።

"ባክህ እሱን እርሳው፤ ይልቅስ ሰዓታችን ደርሷል እንሂድ፤ ለማታሳምነኝ ነገር ስንጨቃጨቅ ብንውል ዋጋ የለውም።" ይልና ይነሳል።

ካሣሁን ሊሸነፍ ሲል መሸነፉን ሳለመቀበል አርዕስቱን የሚያቋርጥበት መንገድ ሁሌ እንዳለው ፈጠነ ስለሚያውቅ በክርክሩ ሊቀጥል አልፈለገም። በተግባር አሳይቶ ሊያሳምነው የሚችል መሆኑ እየተሰማው በኩራት ተነሳ። ወደ ሁለተኛውም የፍልሚያ ቦታ ሄዱ።

የተቃጠሩበት ምግብ ቤት ልክ በሰዓቱ ደርሰው መቀመጫቸውን እንደያዙ ዴብራ ከአንዲት ሌላ ልጅ ጋር ወዲያውኑ መጡ።

ካሣሁን ሰዓቱን አየና ዞር ብሎ በኩሩት ፈጠነን ተመለከተ። ካሣሁን ሊል የፈለገውን ፈጠነ ለመረዳት አልተሳነውም።

"ምን ልትል ነው?" አለው ፈጠነ ካሣሁንን እነ ዴብራ ዋደነሱ ለመምጣት የለበሱትን ካፖርት አውልቀው በመስቀል ላይ መሆናቸውን እያየ።

"የዚያን ዕለት እነ ሰናይት ስንት ሰዓት እንዳስጠበቁን ትዝ አይልህም?" አለው ካሣሁን እየተዝናና።

ፈጠነ ሊመልስለት ፈልጐ ነበር፤ የነዴብራ መድረስ አቋረጠው።

ተነሱና ተዋወቁ። ፈጠነና ዴብራ በወሬ ካልሆነ በዓይን ተገናኝተው አይተዋወቁምመ ነበርና እነሱም ተዋወቁ። ዴብራ ጊዜ አላጠፋችም። ጓደኛዋን ከካሣሁንም ቀድማ ለፈጠነ አስተዋወቀችሁ።

"ሲንቲያ፤ ይህ ነው ያልኩሽ ሰው፤ እሱ " አለች ዴብራ ወደ ካሣሁን ዞር ጠጋ ብላ "የኔ እስዊት ሀርት ነው፤"

"ሃይ! አለችና እጇን ወደ ፈጠነ ዘረጋች፤ አንጀት ከሚያርስ ፈገግታ አከለችበት።

ፈጠነ የሁኔታው መፍጠን ከአሰበው በላይ ሲሆን ትንሽ ድንግርግር አለው። ሰላምታውን ተቀበለ፤ እሱም ከውስጡ ማፈርን ያዘለ ፈገግታ ሰጣት። ካሣሁን ደረቱን ነፋ አደረገ።

ሁሉም ሲቀመጡ ዴብራ "I missed you honey" ብላ ካሣሁንን እዚያው ከንፈሩን ሳመችው። ካሣሁንን ራሱንም ቢሆን ትንሽ ያሰፈረው ሁኔታ ነበር። ፈጠነ ድንገት ሁኔታውን በአካባቢው ያሉ ሌሎች አበሾች አይተው እንደሆነ በማለት ገልመጥ ገልመጥ ብሎ አየ።

ሲንቲያ እንደ ዴብራ አልነበረችም። ትንሽ ቀዝቀዝ ያለች መስሎ ታየው። "መልኳ ግን ከኛዎቹ ልጆች በምንም አይለይም፤ እንዲያውም ይህች ሳታምር ትቀራለች?" እያለ ፈጠነ ያስብ ገባ። ከሰናይት ግን የበለጠ እንደምታምር ሕሊናው ተቀብሎታል። እና ታዲያ ትክ ብሎ ሊያያትም ፈራ።

ሰረቅ እያደረገ ማየቱን ያየችው ዴብራ ወደ ሲንቲያ ዞር ብላ "ነግሬሽ የለ! ዓይነ አፋሮች ናቸው፤" አለች።

"There is nothing wrong with that!" አለችና መለስ ብላ ፈጠነን በሞላ ፈገግታ ስትመለከተው እሱም የሚለው ጠፍቶት ፈገግ አለላትና አንገቱን ደፋ። እንደዛ መባሉን ግን አልወደደም።

"ቆይተሃል እዚህ አገር" አለችው ሲንቲያ ፈጠነን "አዎ ብዙ ቆይቻለሁ፤" አላት። አንቺስ! አይባል ነገር እሷ ያለችው አገሯ ነው፤ የሞኝ ጥያቄ፤ ብቻ ቁርጥ ያለ መልስ ሰጣትና እፍረቱን ያስታምም ገባ።

ራት ከመታዘዙ በፊት መጠጥ ተጠየቀ። ሲንቲያ፣ ዴብራና ካሣሁን የወይን ጠጅ አዘዙ። ፈጠነ ሄኒከን ቢራ አዘዘ። በራት ትዕዛዝ ላይ ዴብራ የወሰደችው ጊዜ ፈጠነን ገረመው። እሷና ሲንቲያ ያዘዙት ብዙ ነገር ሲመጣ የተቀመጡበት ጠረጴዛየሚበቃ መስሎ አልታየውም። ለማንኛውም ራት መጣ። ራቱንም ሲያዙ፣ የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ ሲያደርጉ ሁኔታቸው ያስፈራው ጀመር፤ በተለይ የዴብራ። "ምን ዓይነት ከውካዋ ናት?" አለ በሆዱ።

ፈጠነን ያስጨነቀው የዴብራ ቀልጠፍጠፍ ማለት ብቻ ሳይሆን "እንደዚህ ሲበለቃቀጡ ያየ አበሻ ምን ይል?" የሚል ሃሳብ ነበር። ለዚህም ነው፣ ወይ ዴብራ ወይ ሲንቲያ አንድ ነገር በተናገሩ ቁጥር ገልመጥ ብሎ አጠገባቸውን ያለውን ጠረጴዛ አበሻ ይኑርበት አይኑርበት ለማረጋገጥ የሚመለከተው።

ጨዋታው ደራ፤ በአብዛኛው የምታወራው ዴብራ ነበረች። አንደኛ ነገር ድምጿን ዝግ አድርጋ ማውራት አለመቻሏ ፈጠነን ምቾት አልሰጠውም። በወሬ መሐል ከሲንቲያ ጋር ይጠቃቀሱና አጠገባቸው ካለው ጠረጴዛ ላይ ያሉት ሰዎች ዘወር ብለው እስኪያዩ ድረስ ማስካካታቸው እረፍት ነሳው። ከሁሉ ያናደደው ካሣሁን እነሱን ልምሰል እያለ የሚያደርገው ሁኔታ ነበር። ሁሌ የሚያውቀው ካሣሁን መስሎ አልታይ አለው። ለመምሰል የሚደረግ ነገር ምን ያህል እንደሚያስጠላ ካሣሁን እንዴት ሊረዳ እንዳልቻለ ገረመው። ቢሆንም የሲንቲያ ሁኔታ ደግሞ ሌላ ነገር ፈጠረበት። ደስ ትላለች፣ በተለይ ስትስቅና ፈገግታ ስትሰጥ ሰስታ የምታስቀረው ነገር የለም። ሙሉ ፈገግታ ነው የምታስጠው። ሌላ አንድ የገረመው ነገር ቢኖር እነ ዴብራ ይሉኝታን ፈርተው ማድረግ የሚፈልጉትን ከማድረግ፣ ማለት የሚፈልጉትን ከማለት ወደኋላ አለማለታቸው ነው። ይሉኝታ የምትባል ቃል በመዝገበ ቃላታቸው ላይ ስለመኖሩም የሚያጠራጥር ሁኔታ ነበር የገጠመው። ብቻ ምን ቸገረው፤ "ቢሆንም እኮ ሲንቲያ ደስ ትላለች፤" አለ በሆዱ። ምግብ ሲታዘዝ የሚፈልጉትን ያላንዳች መግደርደር፣ ወይም ለክፋዩ አዝኖ አነስ ያለ ነገር ማዘዝ

የሚባል ነገር የለም። ሁለቱም ቢሆኑ አበላላቸው በጣም ገረመው። ብዙ ይበላሉ፤ ያዘዙትን ጥርግ አድርገው ነው የሚበሉት፤ ሰው ምን ይለኛል የለ! ዴብራ ብቻዋን የበላችውን እሱና ካሣሁን የበሉትን የሚበልጥ መስሎ ታየውና ገረመው። "የምን የሰው ሆድ መገመት ነው፤" አለ በሃሳቡ። ስታወራ እየበላች፣ ስትስቅ እየበላች፣ መብላት! መብላት! ብቻ። "ምን ዓይነት appetite ቢኖራት ነው" አለ በሆዱ። 'የሴት ልጅ ሆዷ ቁጥብ ነው' የሚለው አባባል እንደማይሠራ ተረዳ።

በዚህ ላይ ጨዋታቸው፤ መደሰት ሲባል መደሰት ነው፤ በይሉኝታ ተወጥሮ ማድረግ የሚፈልጉትን ነገር ከማድረግ ተቆጥቦ መጨነቅ ወይም ደብሮ መደበር የሚባል ነገር የለም! "ምን ዓይነት አስተዳደግና ልምድ ነው?" አለ በሆዱ።መሐል ላይ ለሚጠየቀው ነገር አጫጭር መልስ በመስጠት ብቻ ቁጭ ብሎ ሁኔታቸውን ይታዘብ ጀመር። ብቻ ምን ቸገረው? ሲንቲያ እንደሆነ ደስ የምትል ልጅ ናት!

"Honey, ከዚህ በኋላ እዚያ ክለብ ነው የምንሄደው፤ አይደል?" አለችው ዴብራ ካሣሁንን። "የትኛው ክለብ ነው?" አለች ሲንቲያ ካሣሁን መልስ ከመስጠቱ በፊት።

ዴብራ ክለቡን ነገረቻት።

"ከሱስ ያኛው ይሻላል?" አለችና ሲንቲያ ሌላ ክለብ ጠራች።

"እሱ ምን ደስ ይላል? ቀዝቀዝ ያለ ቦታ ነው" አለቻት ዴብራ።

የሚሻለውን ክለብ ለመወሰን በዴብራና በሲንቲያ መሐል አተካራ ተነሳ። ካሣሁን አንዴ ዴብራን አንዴ ሲንቲያን ከማየት በስተቀር እሱ ግን የመወሰን መብት የሌለው መሆኑን ሲያይ ፈጠነን ገረመው። በመጨረሻም ሁለቱም ክለብ ለመሄድ ዴብራና ሲንቲያ ወስነው ካሣሁንን አዩት። ፈጠነ ግን እስከ መኖሩ የተረሳ መስሎት ኩሩ ልቡ ከውስጥ ተቆጣች። ካሣሁን ውሳኔውን ሲቀበል ፈጠነን አልጠየቀም፤ ድሮስ ፈጠነ ምን ያውቅና?

ራት እንዳበቃ ዴብራና ሲንቲያ ተነስተው ይቅርታ ጠይቀው ወደ መጸዳጃ ቤት ሄዱ። የነሱ መሄድ ለካሣሁንና ለፈጠነ አንዳንድ ነገር ለማውራት አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው።

"ምንድነው የሚዘጋህ?" አለው ካሣሁንን።

"ምን ላድርግ? እንደነሱ ልበላቀጥ?" ይላል ፈጠነ።

"ደስ አላለችህም ልጅቷ?" አለ ካሣሁን በፈገግታ።

"እና?" ይላል ፈጠነ ታዲያ ምን ይሁን የሚል ይመስላል። ሲንቲያ ደስ እንዳለችው ሊደብቅ አልፈለገም።

"እሷም የወደደችህ ይመስላል?"

"እና?" ይለዋል አሁንም።

"አዋራታ! ጅል!" ይለዋል ካሣሁን።

"መቼ ፋታ አገኘቼ? ባወራስ ምን ብዬ?"

"ውበቷን አድንቅላት፤ ደግሞ እኔ የማወራውን አታይም?" ይላል ካሣሁን።

ፈጠነ ሳቀ።

"ምን ያስቅሃህ? " አለው ካሣሁን።

"እኔ የማወራውን ስትል ጊዜ ነዋ፤" ይልና ሳቁን ያቀጥላል።

"እኔ የማወራው ምን ሆነ?" አለ ካሣሁን።

"እይ ካሣሁን! ዛሬ ገረምከኝ። የማውቅህ ካሣሁን መስለህ አልታየኝ አልከ።

"ምን አደረግሁ? ወሬዬ ነው"

"አአይ! እነሱን ልምሰል እያልክ የምትለውና የምታደርገው ነገር ከእውነተኛው አንተነትህ ጋር እየተጋጨ ሳየው ገረመኝ፤" አለ ፈጠነ ከሳቁ መለስ እያለ።

"ሲገርምህ ይኖራል፤ ጅል ነህ? አይገባህም፤ ከምታወራው ሰው ጋር ተመሳስለህ መቅረብ ምን ክፋት አለበት?" ይለዋል ካሣሁን።

"ራስን ሆኖ መቅረቡ ሳይሻል ይቀራል? ባክህ አትጨቅጭቀኝ፤ ብቻ ምናለፋህ ታስቃለህ እንደዚያ ስሆን" አለው ፈጠነ የመጣበትን ሳቅ እንደማፈን ብሎ።

"እኔን እንዳሻህ በለኝ! አንተ ግን ስትጃጃል በጅህ የገባችው ወርቅ እንዳታመልጥህ!" ይለዋል ካሣሁን።

"ለሱ ግዴለህም፤ እኔነቴን ሳልቀይር አገኛታለሁ፤ ደግሞ አግኝቻታለሁ።"

"ልናይ አይደል?" ይለዋል ካሣሁን ፈጠነን።

እነ ዴብራ ተመለሱ። የዴብራ ዓይን ደፍረስረስ ማለቱን ካሣሁን ሲያይ ያደረገችውን ለማወቅ አልተሳነውም። ሲንቲያ ግን ደህና ነበረች። ፈጠነ ምንም ነገር አላስተዋለም። ሂሣቡን ካሣሁንና ፈጠነ ተጋግዘው ከፍለው ተያይዘው ወጡ። ሁለት መኪና ስላለ ለመከታተል ወሰኑ። ሲንትያ ቀድማ የፈጠነን እጅ ያዘችና አንተ ከኔ ጋር ነህ፣ እነሱ ይከተሉናል ብላ መኪናዋ ይዛው ገባች። እጁን እንዳላበው ያወቀው መኪና ልትገባ ስትለቀው ነው። ካሣሁንና ዴብራ በካሣሁን መኪና ተከተሉ።

መንገድ እንደጀመሩ ሲንቲያ ወሬ ጀመረች።

"ምንም ነገር ከመጀመራችን በፊት አንድ ነገር ልጠይቅህ? " አለችው ፈጠነን።

"ጠይቂኝ የፈለግሽውን፤" አላት።

"Are you into drugs?" አትደብቀኝ" አለችው።

ፈጠነ በጣም ገረመው። "ለምንድነው የጠየቅሺኝ?" አላት።

"እንደዚያ ከሆንክ አልፈልግህም! ይህን እወቅ አለችው"

"በምን ጠረጠርሺኝ? እመስላለሁ እንዴ?" አላት።

"በዴብራ በኩል የመጣ ሰው እንደዚያ ነው የሚመስለኝ" አለች።

ጓደኛዋን ያማችለት መሰለው። "እንዴት በዴብራ?" አላት ለማወቅ ጓጉቶ።

"Silly ጥያቄ አትጠይቀኝ። ነህ! አይደለህም? እውነተኛ መልስ እፈልጋለሁ" አለችው ቁርጥ አድርጋ።

"በፍፁም አይደለሁም! መጠርጠርሽም ገርሞኛል" አላት።

"የጠረጠርኩህ ዴብራ ራሷ እንደዚያ ስለሆነች የምታገኘው ሰው ሁሉ እንደዚያ መስሎኝ ነው፤ ይቅርታ" አለችው።
"ምንም አይደለም! እኔ በሕይወቴ ቀምሼም አላውቅ፤" አላት።
"እና እንዴት ነው፤ ደስ ብዬሃለሁ" አለችው።
እሱ ቀድሞ አለማለቱ አሳፈረው። ካሣሁን ያለው ነገር ትዝ አለው። "ደስ ትያለሽ። በተለይ ዓይንሽንና ፈገግታሽን ወድጄልሻለሁ" አላት።
"አመሰግናለሁ!" አለችውና በቀኝ እጇ እጁን ፈልጋ ጨበጥ አደረገችው። "ዓይናፋር ወንድ ደስ ይለኛል" አለችው።
"እኔ ዓይናፋር ነኝ እንዴ?" አላት። የአበሻ ሴቶች 'ዓይናውጣ ነህ' ሲሉት ነው የሚያውቅ።
"አዎ! ልክ የምፈልገው ዓይነት" አለችው። እና ረጋ እንድትል ነው የምፈልገው። ለአልጋ ጨዋታ አታጣድፈኝ። እንደዚያ አሚያደርግ ወንድ ዕቃ ነው መስሎ የሚታየኝ" አለችው።
ካሣሁን ቀድሞ ከነገረው ነገር ጋር አልጣጣም አለው ይህ አባባል። ካሣሁን እንደነገረው ልክ እንደ ዴብራ ወስዳ አልጋ ላይ የምትወረውረው ነበር የመሰለው። "ለምን እንደዚያ አልሽ?" አላት። "አንደኛ ለአንተ ይኖረኛል የምለውን ግምት እንዳይቀንስብኝ፤ ሁለተኛ ደግሞ ያወጣሁት ወንድ ለፍትወት ርካታ ብቻ የተፈጠርኩ አድርጐ የወሰደኝ ስለሚመስለኝ ነው።" አለችው።

"ይህን ጥያቄ ለምን እንዳነሳሽው ገርሞኛል፤ እኔ መጀመሪያ ነገር አልጠየቅሁም።" አላት።

"በሃሳቤ አልነበረም እንዳትለኝ?" አለችና ዞር ብላ ያንን ማራኪ ፈገግታዋን ሰጠችው።

"ይህ ለማለት ትንሽም ቢሆን ምክንያት ሊኖርሽ ይገባል" አላትና እሱም ፈገግ አለ።

"ስማ ማንም ሴት ያንድን ወንድ ፍላጐት ካይኑ ታነባለች፤ እናም እኔም ያነበብኩትን አንብቤ ነው፤ ብዙ ከአፍሪካ የምትመጡ ወንዶች ይህ ድክመት አለባችሁ፤" አለችው። "ደግሞ ይህን ስልህ የወሲብ ስሜቴ ደካማ የሆነ እንዳይመስልህ፤ መጀመሪያ እንግባባ፣ እኔም አንተን ልወቅህ፣ ያኔ ከኔ የምታገኘው ስሜት ሌላ ይሆናል፤ እኔም ካንተ የማገኘው፤ እንዲሁ።" አለችው።

ያላሰበው ርዕስ በመነሳቱ አባባሏ፣ አነጋገሯ ውስጣዊ ስሜቱን ቀሰቀሰው፤ ሰውነቱን ውርር አደረገው፤ ገላዋ በዓይኑ ሕሊናው ታየው፤ ወደዳት፤ ሊያስቀይማትም አልፈለገም። ፈገግታዋና ዓይኗ ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቧም ልዩ ስበት እንዳለው ተሰማው።

ይህችን ሴት የሚያስቀይም ሁኔታ ከመፍጠር መቆጠብ ብልህነት ነው ብሎም ወሰነ።

"ፍቅር ለካ ወሰን የለውም!"

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

---



ውብሸት ገሠሠ



መኩሪያ በቀለ

ከአዲስ አበባ ቤታቸው በ ፲፱፻፸፯
እንደወጡ የጠፉ
ያሉበት ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው
በትልቅ ጭንቅ ላይ ናቸው።
ስለነሱ የምታውቁ
ለላንዳፍታ አስታውቁልን።

ቤተሰቦቻቸው

ብዙ አንባቢ ባተረፈችው
የቤተሰብ መጽሔት በ"ላንዳፍታ"
ድርጅትዎን ወይም የንግድ
ሥራዎን በርካሽ ያስተዋውቁ

# « በእምነት ዙሪያ መሰባሰብ! »

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

ባለፈው እትማችን በአትላንታ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች በማድረግ ላይ ስላሉት እንቅስቃሴ በመጠኑ አትተን ቤተክርስትያን ለመግዛት ያደረጉትን ጥረት ዘግበን እንዳቀረብን ይታወሳል። ዛሬ ይህ በእምነት ጽናት ዙሪያ የተፈጠረው አንድነት ለምልሞ ውጤት በማምጣት ቤተክርስትያኑ ሊገዛ መቻሉን ስናበስር ደስ እያለን ነው። ለዚህ የተቀደሰ ተግባር የተደረገውን የጋራ ጥረትና በዚህም ጥረት ሳቢያ የተገኘውን አኩሪ ውጤት ስናወሳ ከዚህ ልናገኝ የምንችለውን ቸምህርት ጠቀስ ሳናደርግ ማለፍ አንፈልግም። በእምነት ጽናት ዙሪያ የሚደረግ መሰባሰብ መደማመጥን፣ መተሳሰብንና መተጋገዝን እንዲሁም አንድነትን ሊፈጥር መቻሉን የምንማርበት ሁኔታ ነው። ዛሬ በአትላንታ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አማኞች የራሳቸው የሆነ ቤተ ክርስትያን አላቸው። ዛሬ እነኚሁ አማኞች የሀይማኖት ጽናታቸውን የሚያጠናክሩላቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከዕለት ዕለት የኑሮ ሕይወታቸው ጋር እያገናዘቡ የሚያስተምሩ አባት አላቸው። ዛሬ ስለአገራቸው፣ ስለወገናቸውና ስለራሳቸውም የሚጸልዩበት ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑበት ንጹህ የሃይማኖት መድረክ የሆነ የቅድስት ማርያምን ቤተክርስትያን አላቸው።

ዛሬ አትላንታ አካባቢ በስፋት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሲወሳ በአብዛኛው የሚሰማው 'ይህ ሁሉ ሊሳካ የቻለው የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሚገባን ሁኔታ እያስተማሩ ሃይማኖታችንን ጠብቀን በፈጣሪያችን አምነን እንድንኖር ትምህርት የሚሰጡን ካህን በማግኘታችን ነው' የሚል ነው። እኚህ ካህን፣ እኚህ አባት ማናቸው? ስለ እምነት ጽናት አስፈላጊነትስ ምን ይሉናል? ለባዕድ አገር ኑሮአችን ምንስ ምክር ይሰጡናል? ይህንና ይህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ በዚህኛው እትም እናተኩራለን።

የ31 ዓመት ለጋ ዕድሜ ያላቸው አባ ገብረ መስቀል መኩሪያ ወደ አትላንታ የመጡት ከኦክላንድ ነው። ከመጡም ገና 6 ወራቸው ነው። ከኢትዮጵያ ከወጡ ገና ዓመት አልሞላቸውም።



አዲሱ የአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

አባ ገብረመስቀል ወደ አትላንታ አገረ ስብከት ከመጡ ወዲህ ወደ ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን የሚመጡ ምዕመናን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እጥፍ በእጥፍ እየጨመረ መምጣቱን ስንመለከት በአትላንታ ይህን ያህል ኢትዮጵያዊ ነበረ ወይ የሚያሰኝ ሁኔታ ፈጥሮብናል። ለምዕመናን በብዛት ወደዚህ መምጣት ልዩ ታምር ተፈጥሮ አይደለም። "እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በሚገባ ሁኔታ የሚያስተምሩ አባት በማግኘታችን ነው" ይላሉ ምዕመናን።

"ዛሬ ከመቼውም ቀን የበለጠ የሚናፍቀኝ እሁድ ነው፤ እሁድ ደርሶ ቤተክርስትያን ሄጄ የአባ ገብረ መስቀልን ትምህርት ሰምቼ፤ ከምዕመናን ጋር አብሬ ምሳ በልቼ . . . አገሬንና ወገኔን ይበልጥ አስታውሼ የምመጣበት ቀን በመሆኑ ነው" ያለን አንድ ወጣት ልባችንን ነካው።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ የመጽሔቱ ክፍል ባልደረባ ሳላሰልስ እሁድ እሁድ በቤተክርስቲያኑ በመገኘት ካየሁት፣ ከሰማሁትና ከተረዳሁት በመነሳት አባ ገብረ መስቀልን አንዳንድ ጥያቄዎች አቅርቤላቸው ነበር።



አባ ገብረ መስቀል መኩሪያ

ላንዳፍታ፤

አትላንታ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን አማኞች ጉላ ያለ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑ በግልጽ ይታያል። የቅድስት ማርያም ቤተክርስትያንም ሕዝቦችን በእምነት ዙሪያ በማሰባሰብ ላይ ነች።ይህ ተግባር የሚያኮራና ለሌላው ቦታ ምሳሌ ሊሆን ስለሚችል የተፈጸሙትን ተግባራት፣ የታቀዱትን፣ የተደረገውን ጥረት፣ የተገኘውን ትብብር፣ የተገኘውን ውጤት በተለይ ደግሞ ይህን ለማከናወን የገጠመውን ችግርና ችግሩን ለመወጣት የተወሰዱትን እርምጃዎች በተመለከተ ማብራሪያ ቢሰጡን።

አባ ገብረ መስቀል፤

በመጀመሪያ እግዚአብሔር አምላካችን ዕለቱንና ሰዓቱን ባርኮ ስለሰጠን እናመሰግነዋለን። የላንዳፍታ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም ይህንን ጥያቄ እኔ እንድመልሰው ስለጠየቀኝ እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግነዋለሁ። በመሠረቱ እኔ ወደ አትላንታ የመጣሁት በፈረንጆች አቆጣጠር ታህሣስ 10 1994 ነው። ጥያቄውን ለመመለስ የምችለው ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ያለውን ሁኔታ ነው።

በአትላንታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን አማኞች በራሳቸው አነሳሽነት በእግዚአብሔር ረዳትነት የሰማይ አባታቸውን አፍቅረው የለመኑትን ሁሉ ሊሰጥ የሚችል እርሱ እንደሆነ አምነው ሁሉ ካለው ጌታ የሚፈልጉትን ለማግኘት በመሰባሰብ ላይ ይገኛሉ። በተለይ ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ከቁጥር 16 ጀምሮ የበጐች እረኛ፣ የበጐች ጠባቂ እሱ እንደሆነ፣ በጐቹም እንደሚከተሉት ድምጹን እንደሚሰሙት፣ቃሉን እንደሚሰሙት ተናግሯል።

የአትላንታ አማኞች በቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ጥላ ስር ተሰባስበው አምላካቸውን እያገለገሉ ጸሎታቸውን እያደረሱ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ከጌታቸው እየጠየቁ የእግዚአብሔርን ቃል ለመመገብ ወደ ቤተክርስቲያን ተሰባስበው እናገኛለን። የአምላካቸውን ድምጽ ይሰማሉ፤ ይከተላሉ፤ አምላካቸውንም ወደማወቅም ለመድረስ እየመጡ እየተሰባሰቡ እናገኛለን። በአጠቃላይ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡት እግዚአብሔርን ለማግኘት ነው። ጌታን ከመፈለግ ሌላ የሚያኮራና የሚያስመካ ሌላ ሃሳብ የለም። የሚመጡት እግዚአብሔርን ፍለጋ ከሆነ እግዚአብሔር ደግሞ የሕሊናቸውን ሃሳብ ካኃጥያት በስተቀር ያሟላላቸዋል። በአማኞች እየተደረገ ስላለውም ጥረት ለሌላው ምሳሌ እንዲሆን መጠየቃችሁ ደስ የሚያሰኝ ነው። ዕቅድ ወጥቷል፤ ጥረት ተደርጓል፣ ሥራ ተከናውኗል፣ ችግር ገጥሞናል፤ ችግሮች ደግሞ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ተወግደዋል። የመጀመሪያውና ዋናው ዕቅድ ኅብረተሰቡን በእግዚአብሔር በቤተክርስቲያኒቱ ጥላ ስር ለማሰባሰብና እግዚአብሔርን የበለጠ እንዲወዱት እንዲያፈቅሩት እንዲለምኑት የልመናቸውን ዋጋ



እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርንና ሰዎችን ማገናኘት ነው። ሰውም በቤተክርስትያን ጥላ ስር እተሰባሰበ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰማ በትምህርቱም ሕይወቱን እያነጸ ይገኛል። ራሱንም ለንስሐ እያዘጋጀ ወደ እግዚአብሔርም እየቀረበ ይገኛል። ሁለተኛው ዕቅዳችን እንደምታውቁት እንሰባሰባለን እንጂ የራሳችን የሆነ ሕንፃ አልነበረንም። ያንን መግዛት ነበረ። ዕቅዱን ብናቅደውም ያንን ፍፃሜ ላይ ለማድረስ ችግር ነበረ። ይኸውም ችግር ገንዘብ የማጣት ጉዳይ ነበረ። ይሁን እንጂ የለመኑትን የማይነሳ፣ የነገሩትን ቸል የማይል፣ ጊዜ አይቶ የማይከዳ አምላካችን የለመኑትን መልካሙን የልብ ምኞት የሚፈጽም አምላክ ረድቶን ያው በሕዝቡ ትብብር እንዲገዛ ሆኗል። ይህንንም ገንዘብ ለማግኘት የተደረገው ጥረት ኮሚቴ በማቋቋም ሕዝቡን በዛ ስር በማሰባሰብ የተደረገው ርብርብና ትብብር ለሌላው ምሳሌ ከመሆን አልፎ ታሪክ የማይረሳው ለዘላለም ሲነገር የሚኖር ነው። ለኔ በሕይወቴ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነገር ቢኖር ይኸው የአትላንታ ሕዝብ ሕንጻውን ለመግዛት ያደረገው ርብርብ ነበር። ገንዘብ ለማግኘት በተዘጋጀው በዓል ምዕመናን ምግብና ሌሎች ቁሳቁሶችን፤ በጉልበትና በተለያዩ ነገሮች ጊዜአቸውን፣ አዕምሮአቸውን በመሰዋት ያደረጉት ጥረት የማይረሳ ነው። ሕዝቡም የመግቢያ ቲኬት እየገዛ ገባ። የአትላንታ ሕዝብ አንድ የቀረ አይመስልም ነበር። ሁሉም ከፊታቸው እንደማነበው ደስታ ነበረ። በዚያ ወቅት የተገኘው ገንዘብ ቤተክርሰትያናችንን ለመግዛት የመጀመሪያ ክፍያ ለመክፈል በጣም ረድቶናል። አሁንም የተገዛውን ቤተክርስትያን ለማደስ በምንፈልግበት ጊዜ ቤተክርስትያኑንን ለመግዛት ያዋጣው የአትላንታ ሕዝብ ለምንጣፍ፣ ለሻንድለር መብራቶች፣ ለመንበር ማሠሪያ ለቀለም መቀቢያና ለተለያዩ አስፈላጊ ነገሮች ባለው ባቅሙ ምንም ከሌለው አንስቶ ብዙ ሀብት ካለው ሀብታም ድረስ ባቅሙ ያለውን ሁሉም ለእግዚአብሔር ቤት አበርክቷል። አሁንም ይህ ቤተክርስትያን በእድሳት ላይ ይገኛል። የተገኘው ውጤት እንግዲህ ቤተክርስትያን ነው።

የቤተክርስትያን ሕንፃ አግኝተናል። ሌላው ውጤት እንግዲህ አንድነት አግኝተናል። ታላቅና የሚያኮራ ደስ የሚያሰኝ ውጤት ነው። አንድነትን አግኝተናል። የተገኘውም ውጤት ቤተክርስቲያኒቱ ሕዝቡን አሰባስባ አንድ የማድረግ ዓላማ ስለነበራት ሕዝቡ በአሁኑ ሰዓት አንድ ሆኖ በቤተክርስቲያኒቱጥላ ስር ተሰባስቦ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ለስሙ ዝማሬ እያቀረበ መጽሐፍ ቅዱስን እየተማረ ይገኛል። በርግጥ ሰይጣን ጠላታችን ላይተኛ ይችላል። ሰይጣን እንደሚያገሳ አንበሳ ሆኖ ዙሪያውን ሊዞር ይችላል። ዓለምን ድል ያደረገ ኃጥያትን ድል ያደረገ ዲያብሎስን ያሸነፈ ምንግዜም በሰልፍ ኃያል የሚሆን እግዚአብሔር አምላካችን ዲያብሎስን ይዋጋዋል፤ ያሸንፍልናል። እስራኤላውያን በባርነት ተይዘው በነበረ ጊዜ በሙሴ አማካይነት ነፃ ሲያወጣቸው ባህሩን ከፍሎ ያሻገራቸው መና ከሰማይ አውርዶ የመገባቸው ከአለት ውሃ አፍልቆ ያጠጣቸው በስደታቸው ጊዜ እንዳባት እንደናት እንደወንድም እንደእህት ሆኖ ደግፎ ይዞአቸው የነበረ እግዚአብሔር ይዋጋላቸው ነበረ። ለዚህ ነው በኦሪት ዘፀዓት ም.15 ቁ. 5 ላይ "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፤ ስሙም እግዚአብሔር ነው፤ የእስራኤል አምላክ አሸናፊ ነው" እያሉ ሙሴና ተከታዮቹ ሁሉ የዘመሩለት። እኛም ይህን ሁሉ ችግር ልንወጣው የምንችለው በእግዚአብሔር ነውና እስካሁን የታገለልንና ያሸነፈልን፣ እስካሁን የጠበቀንና በክብር ያኖረን፣ የምንፈልገውን ሁሉ የሰጠን እግዚአብሔር ለወደፊትም በፊታችን ይጓዛል ብለን እናምናለን። ችግሮች ሁሉ ይወገዳሉ። መለያየት ሁሉ ይወገዳል፤ ደግሞም ተወግዷል፤ እንግዲህ ችግሮች ቢገጥሙንም ከችግር አንቆጥራቸውም፤ ምንግዜም በእግዚአብሔር ቤት ሆነን መንፈሳዊ ሥራ በምንሠራበት ጊዜ ሁሉ ችግር አይገጥመንም ብለን ማሰብ የለብንም፤ መልካም ሥራ ከተጀመረ ችግር አለ፤ ጥሩ ሥራ ካለ መጥፎ ሥራ አለ፤ ጨለማ ካለ ብርሃን አለ፤ ማዘን ካለ መደሰት አለ፤ ማልቀስ ካለ መሳቅ አለ፤ ለእያንዳንዱ ነገር ተቃራኒ ነገር አለው። ስለዚህ መልካም ነገር ከጀመርን መጥፎው ነገር ምንጊዜም ይዋጋል። እናም ባለመሰልቸት ጉዞአችንን እንቀጥላለን። ቤተክርስቲያናችንን በቅርብ ጊዜ አስመርቀን እንገባለን። እግዚአብሔር አምላካችን ይርዳን፤ ለወደፊት ሕጻናትን፣ ሽማግሌዎችን በአጠቃላይ ዕድሜን፣ ጾታን ዘርን ሳይለይ ቤተክርስቲያኒቱ የስብከት ወንጌልን ሥራ በበለጠ ለማስፋፋትና ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ በእግዚአብሔር ጥላ ስር ተሰባስቦ ለአገሩ ለኢትዮጵያም እግዚአብሔርን እየለመነ በተቻለ አቅሙ በሚፈቅድለት ሁሉ ትብብርናጥረት እንዲያደርግ ይህች ቤተክርስቲያን ዓላማዋ ነው።

ላንዳፍታ

በጠቅላላ በሰሜን አሜሪካ ስላለው የቤተክርስቲኒቱ እንቅስቃሴ መጠነኛ መግለጫ ቢሰጡን። እነኚህን በየቦታው የተቋቋሙትን ቤተክርስትያናት የሚያሰባስብ ሁኔታ ተፈጥሯል ወይ? ከሌለስ ይህን ሁኔታ ለመፍጠር እንዴት ይቻላል?

አባ ገብረ መስቀል፤

ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ከመጣሁ ገና ዓመት እንኳ አልሞላኝም። በአሜሪካ ስላለው የኦርቶዶክስሃይማኖት እንቅስቃሴ አጠቃላይ መግለጫ ለመስጠት ሊያዳግተኝ ይችላል። መጀመሪያ መጥቼ መንፈሳዊ ማለት ወንጌላዊ ሥራዬን የጀመርኩት ካሊፎርኒያ ኦክላንድ በርክሊ ከምትባል ቦታ መካነሰላም መድኃኒያለም ቤተክርስቲያን ነው። ሁለተኛ ደግሞ እዚሁ አትላንታ ነው። በዚህ ዓመት ባልሞላ ጊዜያት ውስጥ በዓይኔ ያየሁዋቸው ሁለት አብያተ ክርስቲያናት በበለጠ መናገር እችላለሁ። በተለይ በርክሌ መድኃኒያለም በብጹህ አባታችን አቡነ መልከ ጻዴቅ አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን ብፁዕ አባታችን ኢትዮጵያውያኑን ያስተምሯቸዋል፣ ያጽናኗቸዋል፣ ያረጋጉዋቸዋል፤ በተቻላቸው ሁሉ አባታዊ ምክራቸው አይለያቸውም። እዚያም ያለ ሕዝብ እንደ ብረት የጠነከረ፣ መሠረቱ ክርስቶስ የሆነ አንድ ሕዝብ ነው። የሕዝቡ ትብብር ለሌላው ምሳሌ የሚሆን ነው። መልካም ፍሬ ያፈራ ሕዝብ ነው ብዬ ብናገር እችላለሁ። እነሱም እንደዚሁ ቤተክርስቲያን ገዝተዋል። ቤተክርስቲያን ሲገዙም ችግር ገጥሞአቸዋል፤ ችግሩንም የተወጡት ባንድነት ነው። ከኦክላንድ፣ ከሳንፍራንሲስኮ፤ከሳን ሆዜ ከተለያዩ ቦታዎች ኦርቶዶክስ ክርስትያን የሆኑ ኢትዮጵያውያን በመሰባሰብ ይህን ቤተክርስቲያን አቁመውታል። ፪ኛ የማውቀው እዚሁ አትላንታ ያለውን የቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ነው። እነኚህ ሁለቶቹ በጣም የተጠናከሩ መሆናቸውን ያየሁት ነው። በሌሎቹም ቦታዎች የተጠናከሩ እንዳሉ አውቃለሁ። በዓይኔ አላየሁም፣ በጆሮዬ ሰማለሁ፤ሎስ አንጀለስ ቅድስት ማርያም፤ በሳንዲዬጎ ቅዱስ ገብሬል፤ ዋሺንግተን ዲ ሲ፤ ኒው ዮርክ፤ ቺካጎ፣ ዳላስ፤ ካናዳ፣ በደሴቶቹም፣ በአውሮፓም በአጠቃላይ በዓለም ዙሪያ ብዙ እንዳሉ እሰማለሁ። በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ከአባቶቻቸው የወረሱትን ቅርስ ተዋህደውት በስደት ዓለምም ቢኖሩ እንኳ እምነታቸው አልተለያቸውም። በፊታቸው ያለው የእግዚአብሔር ብርሃን እያበራ ነው ያለው። እንቅስቃሴውም ስብከተ ወንጌልን የመስበክ፣ ሕዝቡን አንድ የማድረግ፤ የማረጋጋት፣ ሕጻናቱን ቋንቋቸውንና ባህላቸውን እንዲያውቁ የመርዳት ሁኔታ እንዳለ ነው የምረዳው። ይህ እንቅስቃሴ ወደፊት በጣም እንደሚያድግም ነው የሚታየኝ። በየቦታው የተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት የሚያሰባስብ ሁኔታ ተፈጥሯል ወይ ለሚለው አሁን ወደ መፈጠሩ ገደማ ነው። ለአገሩ እንግዳ ስለሆንኩኝ ምናልባት ይህን ሰፋ አድርጌ ለመመለስ ይቸግረኝ ይሆናል። ሁኔታውን ለመፍጠር የሚቻልበትን መንገድ መናገር እችላለሁ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ምዕራፍ ፬ ቁ ፭ ላይ "አንድ ጌታ አለ፤ አንዲት ሃይማኖት አለች፤ አንድ ቤተክርስቲያን አለች፤ የሁሉም ፈጣሪ የሆነ አንድ እግዚአብሔር አለ።" አንዲት ቤተክርስቲያን ካለች አንድ ሕዝብ አለ ማለት ነው፤ ያ ሕዝብ ደግሞ የእግዚአብሔር

ሕዝብ ነው፤ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሕዝብ ሁሉ አንድ መሆን አለበት። እያንዳንዱ ሰው የሚያስበው ሃሳብ አንድ ከሆነ፣ ያ ደግሞ በቤተክርስቲያን ደረጃ ሲሰባሰብ ቤተክርስቲያን ማለት ደግሞ የክርስቲያኖች ጉባኤ ማለት ጥምር ነው፤ በየቦታው ያለው እምነቱ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት የሆነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እየተሰባሰበ አንድ እየሆነ በደብዳቤም በስልክም ተገናኝቶ አንድነቱን አጠናክሮ ማስፋፋት ይቻላል። ለዚህ በመጀመሪያ በያለበት አንድነትን መፍጠር ያስፈልጋል። መጀመሪያ አባትና እናት፤ ባልና ሚስት በአጠቃላይ ቤተሰብ አንድ ሊሆን ይገባል። ከዚያ ደግሞ ጐረቤታሞች አንድ ሊሆኑ ያገባቸዋል፣ ከዚያም በአንድ ከተማ፣ ከዚያም በእስቴት እያለ በአገር ደረጃ ያሉ ክርስቲያኖች አንድ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ሕዝቡ የቆመለትን ዓላማ ማወቅ አንድ ሊያደርገው ይችላል። በቤተክርስቲያን ጥላ ስር መሰባሰቡ ዓላማው ምንድነው? ዓላማውን ካወቀ ወደ አንድነት ያደርሰዋል፤ ይህን ሁኔታ ለመፍጠር እያንዳንዱ ክርስቲያን የቆመለትን ክርስቲያናዊ ዓላማ ማወቅ አለበት። ፫ ነገሮች አሉ። በእምነቱ ላይ አቋም ይኖረዋል፤ በአቋሙ ላይ ደግሞ ዓላማ ይኖረዋል፤ ሶስተኛው ደግሞ ተስፋ ነው። አቋሙ ክርስቲያናዊ አቋም ነው። በክርስትና እምነቱ ሊደርስበት የሚችለውን ነገር ሁሉ ቢደርስብኝስ፣ ይድረስብኝም ብሎ ራሱን መስዋዕት ማድረግ አለበት፤ ራሱን አሳልፎ መስጠት አለበት ለቆመበት ዓላማ። ዓላማው ደግሞ ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋት፤ ራሱን ለንስሐ ማቅረብ፣ ቅዱስ ቁርባን መቀበል፣ ከጎብረተሰቡ ጋራ በፍቅር መኖር መቻል ናቸው። ተስፋው ደግሞ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነው። እንግዲህ በየቦታው ያለው ክርስቲያን ሁሉ አንድ የሚያደርገውን ይህን ዓላማ መመርኮዝ አለበት። ዓላማችን የሚጸናው ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ስንመሠረት ነው። ይህ ዓይነቱ ዓላማና እንቅስቃሴ አንድነትን ሊፈጥር ይችላል ብዬ እምናለሁ።

ላንዳፍታ
በስደትም ሆነ በሌላ መልኩ በዚህ በሰው አገር ያለውን ኢትዮጵያዊ በማሰባሰብ፣ በመደገፍና በመርዳት በኩል ቤተክርስቲያኒቱ ልታደርገው ስለምትችለው ነገር በርሶ በኩል የሚሰማዎትን ቢገልጹልን? እየተደረገም ካለም ስለዚሁ ቢያብራሩልን?

አባ ገብረ መስቀል፤
ስደት በተለያዩ ሁኔታዎች ሊከፈል ይችላል። የራስን አገር ለቆ መሄድ ስደት ነው። እንደገና ደግሞ ከባህል፣ ከእምነት ተሰዶ መሄድ አለ። አገርን ለቆ የሚሰደደውን በብዙ መልኩ ልናየው እንችላለን። ከዚህ ውስጥ እውነትን እየተናገረ ተቀባይ አጥቶ እውነትን በመናገሩ ብቻ ችግር ላይ ወድቆ የሚሰደድ አለ። ሌሎችም ምክንያቶች ይኖራሉ አገርን ለቅቆ ለመሰደድ። እግዚአብሔር ባርኮ ከሰጠው አገሩ ሳይወድም ሆነ ወዶ የወጣ ይኖራል።

ይህን ስደተኛ ማሰባሰብ ራሱ አንድ የቤተክርስቲያን ዓላማ ነው። ምክንያቱም የሰዎችን አንድነት እግዚአብሔር ይወዳልና። የባህል ስደተኞችንም፣ የእምነት ስደተኞችንም የአገር ስደተኞችንም ቢሆን በአንድ ላይ ማሰባሰብ ቤተክርስቲያን ይኖርባታል። በመጀመሪያ ሊያሰባስብና አንድ ሊያደርግ የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉን ከሰማንና አንድ ሃሳብ አንድ ዓላማ ከኖረን አንድ ነው የምንሆነው። እንግዲህ ቤተክርስቲያን ሕዝቡን ለማሰባሰብ በቅድሚያ ዓላማዋ የሚሆነው ስብከተ ወንጌል ማስተማር ነው። ይህ ስብከተ ወንጌል ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ያሉትን ሁሉ አንድ ያደርጋል። እግዚአብሔር እሱ አንድ ነው፣ እኛንም ደግሞ አንድ ያደርገናል። "በርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት ያገኛልና"። በሁሉም ነገር እንዲረዳዱ እንዲሰባሰቡ እሁድ እሁድ ስብከተ ወንጌልን በማስተማር አገራቸው እግዚአብሔር ባርኮ የሰጣቸው የተፈጥሮ ጸጋ እንደሆነች ባንድነት ብንሆን፣ ብንስማማ በአንድ መንገድ ብንሄድ አንድ አመለካከት ቢኖረን ቀና አመለካከት ቢኖረን ይህን እግዚአብሔር የሰጠንን የተፈጥሮ ሀብት ሁሉ ልንጠቀምበት እንደምንችል፤ አገራችን ሁልጊዜ የረሀብ፣ የድርቅ የጦርነት አገር ከመሆን አልፋ የምርት፣ የትምህርት፣ የቴክኖሎጂ የተለያዩ ጥሩ ውጤቶች የሚገኙባት የተቀደሰች የተባረከች አገር ልትሆንልን ትችላለች። ቤተክርስቲያኒቱ ያላት ዓላማ እነዚህን ለማሰባሰብ መጀመሪያ በጥላዋ ስር እያሰባሰበች ትምህርቷን መስጠት ነው።

ላንዳፍታ
የባህልና የእምነት ስደተኛ ሲሉ ምን ዓይነቱን ስደት እንደሆነ ቢገልጹልን፤

አባ ገብረመስቀል
አገራችን የራሷ ባህልና ታሪክ ያላት አገር ናት፤ ነቢዩ ዳዊት "ኢትዮጵያ ፈጥና እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ብሎ የተነገረላት አገር ናት። ችግር ሲደርስባት እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ከመዘርጋት ያላረፈች አገር ናት። ይህች ቅድስት አገር የራሷ ባህል አላት። ከእግዚአብሔር ያገኘችው፣ መጀመሪያ በብሉይ ኪዳን የኦሪትን መስዋዕት ስትሰዋ የቆየች አገር ናት፣ በአዲስ ኪዳንም ከክርስቶስ ልደት በኋላ የክርስቶስ ደም መፍሰሱን ለኃጥዓን መስዋዕት ሆኖ የተሰዋ መሆኑን፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ መንገድ፣ በር መሆኑን አምና የተቀበለች አገር ናት። ይህን እምነት፣ ይህን ባህል ያላትን አገር ልጆቿ ተምረው አውቀው ጊዜው ሲገጥም ወደ ሌላም አገር ይሁን ወይም በዚያው ባሉበትም አንዳንድ እንግዳ የሆኑ ነገሮች በመጡ ጊዜ የራሳቸውን ትተው ሌላ ለመፈለግ ይሄዱ ይሆናል። ብዙዎች በጊዜአዊ ነገር፤ ያው የሰው ሕሊና አዲሱን ነገር ብልጭልጩን ይወዳልና ይኸው ብልጭልጩ ነገር እያታለላቸው የራሳቸውን ባህልና እምነት ትተው ወደሌላ የሚሄዱትን ነው የባህልና የእምነት ስደተኞች የምላቸው።

ላንዳፍታ

አገራችን ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ባለው ሁኔታ የተነሳ በውጪው ያለው ወገናችን በተለያየ አስተሳሰብና፣ አመለካከት ተከፋፍሎ፣ ተናቁሮ እየተለያየ እንደ ጠላትም ከመተያየት ደረጃ ደርሷል። ለዚህ ወገናችን የሚሰጡት አባታዊ ምክር ካለ? እንዲያው ምን ያሻለናል ይላሉ? ቤተክርስትያናችን ይህን የተበታተነ ሕዝብ ለማሰባሰብ ማድረግ ስለሚገባትም ጥረት ቢገልጹልን?

አባ ገብረ መስቀል

ይህን ጥያቄ ለመመለስ ማስረጃዬ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መለያየት፣ መናቆር ወይም ደግሞ በሀሳብ አለመግባባት የፍቅር ጉድለት ይመስለኛል። መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በሠራው ኃጥያት ቸል ሊለው አልፈለገም። በምህረቱ፣ በቸርነቱ በፍቅሩ ሊያየውና ሊያስበው ፈለገ። አስቦም አልቀረም መጣ። ወደዚህ ዓለም ሥጋችንን ለብሶ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰዎችን ሊያድን ስለፍቅር በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አፈሰሰ። ለኛ ሲል ሕያወቱን ሰጠ። ስለ ፍቅር አስተምሮናል። በማቴዎስ ወንጌል ም ፳፪ ከቁጥር ፴፯ – ፵ ያለውን ብንመለከት እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍስ፣ በፍጹም ሃሳብ መውደድ የመጀመሪያውና ታላቁ ትዕዛዝ እንደሆነ ያስተምረናል። ሁለተኛው ትዕዛዝ ደግሞ ይህንኑ የሚመስል "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" የሚለው ነው። ኦሪትና ነቢያት ሁለቱም በዚህ ትዕዛዝ ይጸናል ይላሉ። አንድነት ራሱ በዚህ ይጸናል። መጀመሪያ ፍቅር ሊኖረን ይገባል። እግዚአብሔር አምላካችንን በፍጹም ልባችን በፍጹም ሕያወታችን ወደን ይህችን ትዕዛዝ ደግሞ መፈጸም መቻል አለብንን። በዮሐንስ ወንጌል ም ፲፫ ቁ ፴፬ –፴፭ ድረስ ያለውን ብንመለከት "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ ወይም ተከታዮቼ ናችሁ። ሰዎች ሁሉ ደቀመዛሙርቴ እንደሆኑ በዚህ ይታወቃሉና፤"ይላል። በአጠቃላይ እኛ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደሆን፤ የሰላም ሰዎች እንደሆን የምንታወቀው እግዚአብሔር ስር ሆነን እግዚአብሔርን አፍቅረን ወንድሞቻችንንም ስንወድ ነው። እንግዲህ ይህ ፍቅር ሊጠና እንዲችል በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ ሊያደርግ የሚገባው ነገር አለ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፊሊጲሲዮስ ም ፪ ከቁ ፩ – ፫ ያለውን እንዳለ እንመልከተው፤ "በክርስቶስ አንዳች ምክር ቢሆን፣ የፍቅር መጽናት ቢሆን፣ ምህረትና ርህራሄ ቢሆን ደስታዬን ፈጽሙልኝ። በአንድ ሃሳብ ተስማሙ፤ አንድ ፍቅር፣ አንድ ልብ አንድ ሃሳብ ይሁንላችሁ። ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድስ ስንኳ አታድርጉ። ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራውን ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትህትና ይቁጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን ብቻ አይመልከት፣ ለባልንጀራውም ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሃሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን፤" ይላል። እንግዲህ ማንኛውም ከራሱ ጥቅም ይልቅ የወንድሙን ጥቅም የሚያስጠብቅ ከሆነ፣ ከራሱ ይልቅ እግዚአብሔርንና ወንድሞቹን የሚወድ የሚያፈቅር ከሆነ በእውነት ለአንድነት መሠረት እየጣለ ነው፤ ግድግዳውን እየገነባ ነው። በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ የሚበጀው እንዲህ ያለው ኅብረተሰብ ነው። ለምሳሌ ያህል እኔ ሌላውን ብወደው፣ ሌላው እኔን ቢወደኝ፤ እኛ ደግሞ ተሰባስበን ሌሎቹን ብንወዳቸው፤ ሌሎች ደግሞ እኛን ቢወዱን፣ ለአንተ ይሻልሃል፣ ለአንተ ይሁን፣ ለአንቺ ይሁን ብንል ለእኔ የምንለውን ለኛ ብንለው፣ የእኛ የምንለውን ደግሞ የጋራ ብናደርገው በአጠቃላይ ለራሳችን ጥቅም ብቻ ከምንሯሯጥ ለኅብረተሰቡ ጥቅም ብንሯሯጥ በአጠቃላይ የእኔ ብቻ የሚል ነገር ከሌለና ወንድሞቻችንን መውደድ ከጀመርን መለያየት አይኖርም። ይህ መናቆር፣ መጋጨት፣ መጣላት የሚኖረው የራስ ጥቅም ሃሳብ ብቻ ሲኖር ነው። ምናልባት አንዱ አሸንፎ ብዙ ገንዘብ ማግኘት ይፈልጋል፤ አንዱ አንዱን አሸንፎ ዝና ማግኘት ይፈልጋል፣ አንዱ አንዱን አሸንፎ ወንበር ማግኘት ይፈልጋል። አንዱ ሌውን አሸንፎ ይህንን ኋላ የቀረ ደሀ ሕዝብ መግዛት ይፈልጋል። በአጠቃላይ ማገልገል ከሚለው ይልቅ መግዛት፣ ማስጨነቅ፣ ማሰቃየት፤ ደግሞ ስመጥር ሆኖ ለመታወቅ ብቻ መርጦ ይፈልጋል። ይህ ከሆነ አሁንም መናቆሩ ይቀጥላል ማለት ነው። እኔ ብቻ ልብላ ማለት የለበትም፤ ወንድሜም ይርበዋል ብሎ ማሰብ አለበት። እኔ ብቻ ልጠቀም ማለት የለበትም፤ ወንድሜም ይጠቀም ማለት ይኖርበታል። እግዚአብሔር ለሁሉም የሚያደርገው እኩል ስለሆነ፣ በፍቅር ላይ ደግሞ እግዚአብሔር ስለሚገኝ አንዱ አንዱን ቢያስበው በዚያ ፍቅር ያለንን ሕግ እንፈጽማለን። መጣላት አይኖርም መጋፋት አይኖርም ፤ መቃማት አይኖርም መጋደል አይኖርም፤ ሕግ ሁሉ በፍቅር ይፈጸማልና። ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ም ፲፫ ቁ ፰ – ፲ ላይ "እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይቅርባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞለታልና። አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፤ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትዕዛዝ ሁሉ ጋር በዚሁ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቃሏል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።" ይላል። እግዚአብሔርን ከወደድነው ኃጥያት አናደርግም። ወንድማችንን ከወደድነው ደግሞ በእርሱ ላይ የማይገባውን አናደርግም። ስለዚህ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በእግዚአብሔር ፍቅር ከኖረ፣ ወንድሙንም ከወደደ በወንድሙ ላይ ክፉውን አያደርግም። በ፩ኛ ዮሐንስ ም ፬ ከቁጥር ፯ ጀምሮ ያለውን እንመልከት" ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ የሚወደው ሁሉ እግዚአብሔር ስለተወለደ፣ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ እላለሁ። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን

እያውቅምናᎵ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ስለተገለጸ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮታልናᎵ" ይለናል። በፍቅር ብንኖር እግዚአብሔር የሰጠንን ሁሉ ያንን የተጻፈው ቃል ይፈጽምልናል። አገራችንን ይባርክልናል። የአገራችን የተፈጥሮ ሀብትም ተጠቃሚ እንሆናለን። አንድ ምሳሌ ልመስል እወዳለሁ። ሁለት ስስታም ልጆች ያሏት እናት ምግብ በትሪ ሞልታ ለልጆቿ ብትሰጣቸው እነሱን አጥግቦ የሚተርፍ ነው የምትሰጣቸውᎵ መቼም የእናት አሰጣጥ የተለየ ነው። ነገር ግን ሁለቱ ልጆቿ ፍቅር ከሌላቸው ሲጣሉ ምግቡን እነሱ ሳይበሉት ይደፋል። አሁን ምግብም ሳይኖራቸው፣ እነሱም ሳይረኩ እናት ያዘጋጀችው ምግብ ሁሉ ወደ መሬት ይደፋል። እና ከእናት የሚበልጥ እንደ እናት ሆኖ የያዘን እግዚአብሔር አምላካችን ፲፫ ወራት የጸሐይ ብርሃን የማይለያትᎵ ክረምትና በጋው ለሰው ልጅ ተስማሚ የሆነᎵ በበጋ ማቀዝቀዣᎵ በክረምት ማሞቂያ የማትፈልግ አገራችን ኢትዮጵያ ማንም በድህነቱ ሊኖርባት የሚችል የበረከት አገር፣ የተፈጥሮ ሀብቷ ገና ያልተነካ ታላቅ አገር ናት። እግዚአብሔር የሰጠንን ይህችን አገር ተፋቅረን በአንድነት ሆነን ለጠላት በር ሳንከፍት፣ ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖሩ እንኳ እነዚያን በእግዚአብሔር ፍቅር ሆነን በመቻቻል 'ነገም ሌላ ቀን ነው' እያልን ነገ ለራሱ ቀን አለውና ዛሬ የሥራ ቀን፣ የምትቀጥለዋን ለአንድነት፣ የምትቀጥለዋን ለፍቅር ብናደርግ የሰጠንን የበረከት ስጦታ ልንጠቀምበት እንችላለን። በዚች አገራችን ላይ ራሳችን ከመሬት ተነስተን በምንጣላው ጠብ አንድ ባለመሆን ግጭትን እየፈጠርን የምናመጣ ከሆነ አገራችን ለእኛ አትሆንም ማለት ነው። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት በአንድነት ነው። ዓለምን ዞረው ያስተማሩት በአንድነት ነውᎵ ወደ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ያቀረቡት በአንድነት ነው። እኛም ለትውልድ ታሪክ ትተን ማለፍ የምንችለው በአንድነት ነው። አባቶቻችን ቅርስ ትተውልን ያለፉት በአንድነት ነው። ተቻችለው ተፋቅረው ተስማምተው ስለኖሩ ነው። እኔም ዛሬ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት በአገራችን ውስጥም ሆነ በውጪ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አስወግደው ሁሉም ለጋራ ጥቅም፣ ሁሉም ለአንድ ሀሳብ እንዲነሱ ነው። ዛሬ ኢትዮጵያን የሚፈልጓት ሁሉ ለእኛ ይድላን ብለው ከሆነና ለኅብተሰቡ ጥቅም ካልሆኑ እነሱ የህብረተሰብ ጠንቆች ናቸው። የራስን ድሎትና ምቾት ከመፈለግ ለዚህ ወገናችን ኑሮ መሻሻልና ለዕድገቱ ሁላችንም ብናስብ በአምላካችን ፈቃድ ኢትዮጵያን እንገነባታለን ብዬ አስባለሁ። በምሥራቅም በምዕራብም በሰሜንም በደቡብም በየትም በየትም ያለው ሁሉ ለእኔ ይድላኝ ብሎ ከሆነ የሚታገለው ምንጊዜም ቢሆን ተናክሰው እንደሚያልቁ ጉንዳኖች ነው የምንሆነውᎵ ወይም እንደሚዋጉ ዶሮዎች። ሁለት አውራ ዶሮዎች ከተጣሉ አንዱ ሌላኛውን ዓይኑን ያወጣዋል፣ ሌላኛውም አንደኛውን ዓይኑን ያወጣዋል።

በአሪት 'ጥርስ ለጥርስ' ይባል እንደነበረው ይሆናል። ዛሬ ግን በአዲስ ኪዳን የለም። አንዱ አንዱን ለመበቀል፣ አንዱ አንዱን ዓይኑን ለማውጣት ከሆነ እርግጠኛ ነኝ በአገራችን ብዙ ዕውሮች ይኖራሉ። አንዱ መጥፎ ቢያደርግ መጥላት ያለብን ያንን መጥፎውን ሥራ ነው። አንዱ ዘረኛ ቢሆን እኛ ዘረኛ መሆን የለብንም።ምክንያቱም በሌላው ላይ የምጠላውን እኔ ማድረግ የለብኝምና። ሁላችንም ኃጥያትን እየናቅን፣ መለያየትን እየናቅን መጠላላትን እየናቅን፣ ለራስ ብቻ ማሰብን እየናቅን፣ የግል ዝናንና ጥቅምን እየናቅን እያስወገድን በፍቅር በመተሳሰብ ለጋራ ጥቅም መሆን አለብን። ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖሩን እነዚያን ማቻቻል አለብን። በአንድ እጅ ከማጨብጨብ በሁለት እጅ ከዚያም በብዙ እጆች ቢጨበጨብ ይደምቃል። ይህ የሚሆነው እንግዲህ ፍቅርና መተሳሰብ ሲኖር ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ፩ኛው ቆሮንቶስ ም ፲፫ ከቁጥር ፬ ጀምሮ እንዲህ በማለት ያስረዳናልᎵ– "ፍቅር ይታገሳልᎵ ቸርነትንም ያደርጋልᎵ ፍቅር አይቀናምᎵ ፍቅር አይመካምᎵ አይታበይምᎵ የማይገባውን አያደርግምᎵ የራሱንም አይፈልግምᎵ አይበሳጭምᎵ በደልን አይቆጥርምᎵ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም። ሁሉን ይታገሳልᎵ ሁሉን ያምናልᎵ ሁሉን ተስፋ ያደርጋልᎵ በሁሉ ያጸናልᎵ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም።"

እግዚአብሔር የሰጠንን አገር አባቶቻችን እንዳቆዩልን ለልጆቻችን ለማቆየት፣ ቤተክርስቲያኒቱም ኅብረተሰቡም በአንድነት መረባረብ ይኖርባቸዋል ብዬ አምናለሁ። ለዚህም ቸርነቱ የማያልቅበት አምላካችን ይርዳንᎵ አሜን።

---



የአትላንታ ምዕመናን በጽሞና አባን ሲያዳምጡ

# ዜናዎች በፎቶ

## አትላንታ

### አትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ተጠናከረ። 300 አባላት ተመዘገቡ።



አዲስ የተመረጡት የቦርድ አባላት




የምርጫው ሥነ ሥርዓት በተከናወነበት ወቅት



የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን
አዲስ የቦርድ አባላት ተመረጡ




የወይዘሪት ኤለሳ ሙጨና
የአቶ በላንተ ጌታሁን ጋብቻ ተከበረ።



በአትላንታ የፋሲካ በዓል ሲከበር



የመስከረም የባህል ኦርኬስትራ በአትላንታ




# ጓደኛ ለሚፈልጉ

ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን አስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና ትክክለኛ አድራሻ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና አድራሻ ፋንታ የኮድ ቁጥር ይወጣል። የኮዱን ቁጥር የምንሰጠው እኛ ነን። በስምና አድራሻ ምትክ የኮዱ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ በምስጢር ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ግን እኛ ጋ መድረስ አለበት።በጣም አጠር ተደርጎ ቢጻፍ ዕድሉን ለብዙ ሰው ማዳረስ ይቻላል።

ለመተዋወቅ የምትፈልጉት ሰው ዓይነት ወጥቶ ካገኛችሁ ቁጥሩን በመጥቀስ ደብዳቤ ጽፋችሁለት/ጽፋችሁላት አነስ ያለ ኤንቨሎፕ ውስጥ አሽጋችሁ ኤንቨሎፑ ላይ የናንተን ሙሉ አድራሻ በቀለም፣ የሚላክለትን/የሚላክላትን ሰው ኮድ ቁጥር በእርሳስ ጥጉ ላይ ጽፋችሁ በሌላ ከፍ ባለ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከታችሁ አሽጋችሁ በአድራሻችን ትልካላችሁ። እኛም የኛን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ኤንቨሎፕ አውጥተን የኮድ ቁጥር የተጠቀሰውን ግለሰብ ትክክለኛ አድራሻ ከመዝገባችን ኤንቬሎፑ ላይ በመሙላት እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንደፍጥርጥራችሁ።

የሚከተሉትን መመሪያዎች በደምብ አጢኑ።

1ኛ. ለፖስታና ለአገልግሎት አከፋፈሉ በሚቀጥለው ዓይነት ይሆናል፤
 ከአሜሪካ - $5.00 (በmoney order)
 ከካናዳና አውሮፓ - $6.00 (በአሜሪካ ገንዘብ፣ money order)
 ከኢትዮጵያ - ምንም አይከፈልም።
 ለ"ላንዳፍታ ቋሚ ደምበኞች (subscribers)
 (ላንዳፍታ ግዘግ ቅጽ ሞልታችሁ ከፍያ የላካችሁ) $4.00 ብቻ ነው።
2ኛ. ዕድሜአቸው ከ18 በታች ለሆኑ ይህ አገልግሎት አይሰጥም።
3ኛ. ይህ አምድ ዓላማው መተዋወቂያ መድረክ ለመፍጠር ብቻ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።
4ኛ. እባካችሁ እንዲጻፍላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አሳጥሩት።
5ኛ. በመጀመሪያ የብዕር ጓደኝነትን በማጠንከር የበለጠ መተዋወቅን እንመክራለን።

አዲሱ አድራሻችን፤

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

## ጓደኛ የሚፈልጉ ሴቶች

**ስም 1069፤ ዕድሜ 34፤ መኖርያ ዩናይትድ እስቴትስ፤ የትምህርት ደረጃ 12+13 ወር ኮርስ፤ ላለሁበት ኑሮ በቂ ደሞዝ አለኝ። ክርስትያን፤ ልጅ አለኝ። ቤተ ክርስቲያን እገለግላለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤-ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ የተቀበለና ሃይማኖተኛ የሆነ፤ ቢቻል በሚሄድብ ቤተክርስቲያን አገልጋይ የሆነው፤ ቢቻል እዚሁ U.S. የሚኖር፤ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)**

## ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች

**ስም 1070፤ ዕድሜ 33፤ መኖርያ ዩናይትድ እስቴትስ፤ የትምህርት ደረጃ B.A. መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት፤ በኢትዮጵያዊነቷ የምታምን፣ ጥሩ ጠባይና መልክ ያላት፤ቢያንስ የኮሌጅ ዲፕሎም ያላት፤ ዕድሜዋ እስከ 28 ዓመት ድረስ፤ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)**

አዳም ሔዋን

# « አላለልኝ ይሆን!»

ከትዝታ አለብኝ (L.A.)

(ካለፈው የቀጠለ)

ጥሎኝ መሄዱን፣ በተለይም ደግሞ እኔ ባደረግሁት ነገር ተከፍቶ እኔን ብሎ የመጣው ሰው ሊሄድ መቁረጡን ስረዳ መንፈሴ ተለወጠ። ለመለወጡ ምክንያት ይህ ነው የምለው አይኖርም። "እንዴት አይለማመጠኝም" የሚል እልህ ይሆን? ጥንት ያኔ ገና አፍላ እያለሁ ወንድ ልጅ ሲቀርበኝ ምንም ብፈቅደውም ወዲያው እሺ የማልለው ትዝ ብሎኝ ይሆን? ምኑንም አላውቀውም። ወይስ "ቆራጥ በመሆኑ ወንዳወንድነቱ ታይቶኝ ይሆን? ብቻ እንዳይሄድ ፈለግሁ። በተለይ በዚህ ሁኔታ እኔን ትቶ መሄዱን ልቀበለው አልፈለግሁም። "ማንም ወንድ ረግጦኝ ሊሄድ አይችልም እኔ ካላሰናበትኩት በስተቀር" ብዬ አስቤስ እንደሆነ?

"Please don't do that?" አልኩት ስልኩን ከእጁ ተቀብዬ እየዘጋሁት።

"Do what?" አለኝ በመገረም፤ ስልኩን ለቀቀልኝና በመገረም እየኝ።

ፊቴን ከሱ መለስ አደረግሁና "ሂድ ማለቴ እኮ አይደለም" አልኩት።

"አልገባኝም፤" አለኝ በመገረም ፊት።

"ሂድ ከቤት ውጣልኝ የሚል ቃል ከአፌ አልወጣም፤"

"ሁኔታሽ ግን ከዚያ የባሰ ነው የሆነብኝ፤" አለ።

"ትዕግስተኛ ነኝ" ብለህ አልነበረም የተዋወቅኸኝ? አልኩት።

"ትዕግስት እኮ ወሰን አለው" አለኝ።

"ይኼን ያህል የሚያስከፋ ነገር የተናገርኩ አይመስለኝም።"

"ምን ለየው ብለሽ ነው? ለማንኛውም አሁን የኔን መቆየት መፈለግሽ ለምንድነው? እንደተረዳሁት ከሆነ መንፈስሽ የተቀበለኝ አልመሰለኝም፤" አለ።

"ምንድነው እንደዚህ ያሰኘህ?" አልኩት።

"በስልክ በተነጋገርነው ሁኔታ ሆነሽ አልተቀበልሽኝም። እዚህ ስመጣ አንቺ ጋ ለመምጣት እንጂ ሌላ ጉዳይ ኖሮኝ እንዳልሆነ ታውቂዋለሽ? ከመጣሁ ጀምሮ ሳይሽ በጣም comfortable አልሆንሽም፤ ከዚህ በተረፈ ደግሞ በአንቺ ላይ advantage የወሰድኩ አድርገሽው የተናገርሺው ነገር በጣም ነው የተሰማኝ፤" አለ። ውይይቱ እንዲቀጥል አልፈለግሁም። የምሰጠው መልስ ስለሌለኝም ሊሆን ይችላል።

"አሁን እስቲ መንፈሳችንን ረጋ እናድርገው። ከተማውን ሳስጐብኝህ፤ ትንሽ ወጣ እንበል" አልኩት። ልብሳችንን ለባበስንና ተያይዘን ወጣን። ይገርው ስወጣ በጣም ተጠንቅቄ ነበር። አበሻ የማይገኝበትን ቦታ እየመረጥኩ አሳየሁት።

የምኖርበት ከተማ የሚታወቅባቸውን የሚጐበኙ ቦታዎችን በከፊል አሳየሁት። በዙረታችን ወቅት ስለማስጐበኘው ቦታ፣ ስለከተማው እንጅ ስለእኛ ጉዳይ አላነሳንም። በአብዛኛው ዝምታ የሰፈነበት ሁኔታ ነበር። የሱን እንጃ እንጂ በእኔ በኩል አፌ ዝም ያለ ይምሰል እንጂ ውስጡ ብዙ ያወራ ነበር።

ፊት እንደገለፅኩላችሁ በአብዛኛው ያስጐበኘሁት ቦታ አበሻ የማይገኝበትን አካባቢ እየመረጥኩ ነበር። ቀትር አለፍ እንዳለ አንድ ቦታ ምሳ መብላት እንዳለብን ተረዳሁ። ራቅ ወዳለበት ቦታ ይዤው ሄድኩና ምሳ አዘን በላን። በዙረታችንም ሆነ በምሳችን ወቅት የምናወራው ስለአሜሪካን ኑሮ፣ ስለጐበኘናቸው ነገሮች ብቻ ነበር። አልፎ አልፎ በወሬ በወሬ የኛ ጉዳይ ከተነሳ ቶሎ አርዕስት እቀይራለሁ። ለምን በኛ ጉዳይ ላይ ለማውራት እንደፈራሁ አላውቅም። ትላንት ፍርሃት ሳይሆን ትዕቢት ነበር ያየለው። ዛሬ ግን ፍርሃት ፍርሃት አለኝ። የሱም ዝምታ ማብዛት ይጨንቀኝ ጀመር። በሆዱ ይኼኔ ምን ያስብ ይሆን እያልኩ አስብ ጀመር። በጉብኝታችን ወቅት አንድ ደስ የሚል ቦታ ፎቶ እንድነሳ ቢጠይቀኝ እምቢ አልኩ። እሱ ብቻውን ተነሳ። ብቻዬን እንድነሳም ቢጠይቀኝ አሻፈረኝ አልኩ። ለምን እንደሆነ ራሴም አይገባኝም አሁን ሳስበው። ምሳ እኔም ሆንኩ እሱ እንደነገሩ ነው ነካ ነካ ያደረግነው እንጂ በላን ማለት አይቻልም። የሂሣብ ትኬት ሲመጣ ለመክፈልም አልተግደረደርኩም። እሱ መክፈል አለበት የሚል ውሳኔ ነበረኝ። እንዴ ሰው ቢያይስ "ወንድ እየጋበዘች ነው" መባል ለስምስ ምን ደስ ይላል። ደግሞ አላደግሁበትም፣ አላውቀውምም። እኔ የማውቀው ወንዶች እየጋበዙኝ ነው እንጂ አብረውኝ የሚወጡት እኔ ጋብዤ ...የማይሆን ነው! እና እሱ ከፈለ። ለአሳላፊው ጉርሻ ጠብ የማድረጉን ጉዳይም ለሱ ተውኩለት።

ሂሣብ ተከፍሎ እንዳበቃ ግራ የተጋባውን ሰውዬዬን ይዤ ወጣሁ። ወዴት እንደምንሄድ ግን የማውቀው ነገር አልነበረም። ትንሽ ዘወር ዘወር አልንና ወደ ቤት አመራን።

"እርግጠኛ ነሽ አሁን፣ አንቺ ጋ መቆየት ያለብኝ ይመስልሻል?" አለ።

"ምነው አንተ መቆየት አልፈለግህም ማለት ነው?" አልኩት ወደቤት የሚወስደውን መንገድ እንደያዝኩት።

"እኔማ አንቺ ጋ ብዬ ነው አመጣጤ!"

"ታዲያ ምን ተፈጠረ? እኔ ውጣልኝ አላልኩም" አልኩት።

"በጠቅላላ ሁኔታሽ ሁሉ እኔን ፈቅዶ የተቀበለ አይመስለኝም። በስልክ ያወራነውና ያለምነው ሁሉ እዚህ ስመጣ ሌላ ሆኖ ነው ያገኘሁት፤ በጣም ነው ግራ የገባኝ" አለ።

ደነገጥኩ። ምንድነው እዚህ ሲመጣ ሌላ ሆኖ ያገኘው። ይህንን ልጠይቀው ግን አልፈለግሁም ዝም ብዬ ብቻ መኪናዬን መንዳት ቀጠልኩ። ወደ ቤቴ።

እቤቴ እንደደረስን ቡና ጣድኩና ሂጄ እሱ የተቀመጠበት ፊት ለፊት ካለው ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ። ላወራው የፈለግሁት ነገር ነበር። ግን እንዴት እንደምጀምረው ጨነቀኝ።

በሃሣብ ማዕበል ውስጥ እንዳለሁ የቡናው መፍላት ማስማያው ድምፅ ቀሰቀሰኝና ሂጄ ቡናውን አዘጋጅቼ አቀረብኩ። በጣም ትልቅ ጭንቀት ውስጥ እንዳለ ተሰማኝ። ይታያችሁ እስቲ፣ የሰው ሰው ደህና ከሚኖርበት ቦታ አምጥቶ በዚህ ዓይነት ግራ በተጋባ ሁኔታ ማስተናገድ ምን ይባላል?

ቡናዬን አንድ ሁለቴ ፉት ብዬ መንፈሴን ካረጋጋሁ በኋላ ያሰብኩትን ለማውራት ተዘጋጀሁ።

"አንድ ነገር ልጠይቅህ እስቲ?" አልኩት የሞት ሞቴን።

"የፈለግሺውን ጠይቂኝ" አለና ለመስማት ተመቻቸ።

"የምትሰጠኝ መልስ ግን ግልጽና እውነተኛ መሆን አለበት፤" አልኩት።

"ግድየለሽም፤ ስለጠባዬ ቀደም ብዬ ነግሬሻለሁ። የማውቀውን ነገር የምናገር ሰው ነኝ፤" አለኝ።

"ስለእኔ ምን ተሰማህ?" አልኩት።

"ስለአንቺ ስትይ ምን ማለትሽ ነው?"

"ማለቴ አንተ ስታየኝ ፈቀድኸኝ ወይ?"

"ፈቅጄማ ነው የመጣሁት!"

"ማለቴ በፎቶ ብቻ ነው ያየኸኝ፣ እና ቁመናዬንና መልኬን ከፎቶ ካየኸው የተለየ ሆኜ ነው የታየሁህ?"

"ፎቶግራፍ እኮ የሌለውን አያነሳም?" ትንሽ እንደመሳቅ ብሎ።

"ምን ማለትህ ነው?" አልኩት።

"ማለቴ በፎቶግራፍ ያየሁዋትን ልጅ ነው ያገኘሁት፤" አለኝ።

"ለምን ጥያቄዬን በቀጥታ አትመልስም? እኔ የጠየቅሁህ በውን ስታየኝ ወደድከኝ ወይስ ከግምትህ ውጪ ሆኜ ታየሁህ?"

"በቁመናሽና በመልክሽ ምንም ከግምቴ ውጪ ሆነሽ አላገኘሁሽም፤"

"እና ወደድከኝ ወይስ ጠላኸኝ?"

"በቁመናሽ እንደነገርኩሽ የምወድሽ ልጅ ነሽ" አለኝ። ደስ አለኝ። መወደድን ማን ይጠላል?

"በሌላውስ?" አልኩት፤

"አልገባኝም?" አለኝ።

"ማለቴ ጠባዬን እንዴት አየኸው?"

"ግልጽ ልሁንልሽና ግራ ነው የገባኝ፤ ምን እንደሆንሽ ማወቅ አልቻልኩም። ያቺ በስልክ ተጫዋች አዝናኝና ተግባቢ የሆነችውን ልጅ ግን ያየሁ አልመሰለኝም፤" አለኝ።

"ለምን ይሆን እንደዚያ የሆንኩት?" አልኩት።

"እሱንማ አንቺ ነሽ መመለስ ያለብሽ፤"

"አንተ ምን መስሎ ታየህ?"

"ምንም ልገምት አልቻልኩም። ምናልባት አካላዊ አቋሜን ስታይ ከግምትሽ ውጪ ሆኜ እንደሆነ ብዬ ገምቻለሁ፤" አለኝ።

"እንደዚያ እንድትል ያበቃህ ምን ሁኔታ አየህብኝ" አልኩት።

"ከዚህ ሁሉ ለምን ፍርጥ አድርገሽ አትነግሪኝም? አንቺው እራስሽ ምን እንደሆንሽ፣ ወይም ምን እንዲህ እንዳደረገሽ ብትነግሪኝ በግምት እኔ ከምለው የሚሻል አይመስልሽም? " አለኝ።

"እኔ ይህን ሆንኩ የምለው ነገር የለም። አንተ ነህ እስሬ 'ምን ሆነሻል፣ Comfortable የሆንሽ አትመስይኝም" ስትለኝ የቆየኸው" አልኩት። ሽምጥጥ አድርጐ መካድ ይሏችኋል ይህ ነው።

"ባክሽ ቀልዱን ተይና እውነቱን እንነጋገር። የእንግዳ አቀባበል ባህርይሽ ይህ እንደሆን ምንም ግምቴ ውስጥ አልነበረም። በተለይ የትዳር ጓድኛ ሊሆንሽ ያሰበውን ሰው አቀባበልሽ ይህ ነው የሚል ሃሣቡም አልነበረኝም።"

"ልንጋባ እኮ አልነበረም የመጣኸው?" አልኩት።

"እሱንማ እውቃለሁ። ልንተያይ ትንሽ ቀናት አብረን ቆይተን ሁኔታውን ለመነጋገር፤ ከሆነ ሆነ፣ ካልሆነም ነገሩን ለመርሳት፤" አለ።

"እና ታድያ እኔ ምን አጠፋሁ?"

"አቀባበልሽ ደስ የሚል ካልሆነ በርግጥም እንደገመትኩት Physically እኔን አልተቀበልሽም ማለት ሊሆን ይችላል?" አለኝ።

"እኔ እንደዚያ አላልኩም!"

"ተቀብለሻል ማለት ነው?"

"እንደዚያም አላልኩም!" አልኩት።

"ይህ ነው እንግዲህ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ያልኩሽ፤"

"አንተ ግን ወድደኸኛል ማለት ነው?"

"ስንቴ ልመልሽልሽ፤ ብወድሽ አይደለም የመጣሁት"

"እና ልታገባኝ ወስነሃል ማለት ነው?"

"እሱ የኔ ውሳኔ ብቻ አይደለም።"

"ማለቴ ባንተ በኩል physically ካየኸኝ በኋላ ያለውን ማለቴ ነው።"

"ነገርኩሽ እኮ፤ አንድ ሰው እንዲህ ያለውን ትልቅ ቁም ነገር ለመወሰን በሌላው በኩል ያለውንም አጢኖ መሆን አለበት።"

አንቺ የምታስቢውን ሳላውቅ የኔን አልነገርሽም ማለቱ እንደሆ ገብቶኛል። ቢሆንም እሱ ከቃሉ አውጥቶ ለምን አይነግረኝም። ከዚያ በኋላ የኔን መልስ እሰጠዋለሁ። ይህን ነበር ሒሊናዬ የሚያሰበው።

"እሺ እሱን እንተወውና እንዳው ለምን እኔ እንዲህ አንተ እንዳልከው act ያደረግሁት ለምን መስሎ ታየህ? አልኩት። ደጋግሜ እንደጠየቅሁት ይሰማኛል።

"ነገርኩሽኮ፣" አለኝ።

"እሺ ሴት ልጅ ከአንድ ወንድ ጋር ስትሆን የዚህ ዓይነቱን ባህርይ ካሳየች ምን ማለቷ ነው?" ይህን ጥያቄ የጠየቅሁት ከልቤ ነበር። በውነት ለምን እንደዚያ እንደሆንኩ አላወቅሁም። እሱን አቋሙን አይቼ ጠላሁት እንዳልል በፎቶ ካየሁት እንዲያውም ከግምቴ በላይ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ባህርይውን እንደሆነ ወድጄዋለሁ።

"ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ቅድም እንዳልኩሽ ስሜቷ ላይፈቅደው ይችላል። ማለቴ ላትወደው ትችላለች። ይህ አንድ ምክንያት ነው። ሌላም ሊኖር ይችላል።"

"አልጠላችው እንደሆነስ?" አልኩት። ወድዳኛለች ብሎ ቢንቀባረርም የራሱ ጉዳይ። በርግጥ ይህን ስል እሱ መውደዴን ሆነ መጥላቴን ለማወቅ ስለተሳነኝም መሰለኝ የምጠይቀው።

"አልጠላችው ከሆነማ ምናልባት ከግምቷ በላይ ሆኖ ስላገኘችው እውነት አልመሰላት ብሎ ሊሆን ይችላላ፤" አለኝ።

ይህችን ትወዳለች! ከውስጤ አንድ ነገር ሰውነቴን ውርር አደረገው። በተለይ "ከግምቷ በላይ ሆኖ" የሚለው አባባል ቆጠቆጠኝ። ረጋ ብሎ የነበረው መንፈሴ እልህ ገባ። "ከግምቷ በላይ ሆኖ... ስትል አልገባኝም?" አልኩት በችኮላ ለማለት የፈለገውን መጨረስ አለመጨረሱን ሳልረዳ።

"አየሽ፤ አንዳንዴ እኮ የሰው ልጅ አንድ ነገር ጠብቆ፣ የጠበቀው ነገር ከግምቱ በላይ ሆኖ ካገኘው አቀባበሉን ያጣበታል፤ ያልተዘጋጀበት ነገር ነውና፤ እና ..." ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ

"እና እንደዚያ መስሎ ነው የታየህ?" አልኩት በችኰላ ከውስጤ የትዕቢትና የእልህ ስሜት እየቆጠቆጠኝ።

"አልገባኝም ጥያቄሽ! መስሎ የታየህ ስትይኝ?" አለ።

"የኔ እንደዚህ መሆን ምክንያቱ ይህ ነው ብለህ አሰብክ እንዴ?" አልኩት። የእልህ ሲቃ ድምፄን የቀየረው መሰለኝ።

"አላልኩም፤ ወጣኝ እንዴ?" አለና ፈገግ አለ።

ፈገግታው ልዩ መልዕክት እንዳለው ሁሉ አናደደኝ። ውስጤ በገነ።

"በል ያሰብከው ገብቶኛል። እንደዚያ ከመሰለህ ግን ተሳስተሃል" አልኩት ሲቃ በያዘው ድምፅ፣ ቁጣዬ ያስታውቅብኛል።

"ለጠየቅሽኝ ጥያቄ መልስ ብዬ ነው የሰጠሁት፣ ምን እንዲህ እንዳስቆጣሽ ግን አላውቅም፤" አለኝ።

"ግምትህ በጣም የሚገርም ነው። እንዴት ብትገምተኝ ነው፣ ወይም ራስህን ምን ያህል ከፍ ብታደርግ ነው ይህ የሚታሰብህ?" አልኩት አሁንም በእልህ ድምፅ።

"እኔ ራሴን ከፍ አላደረግሁትም፤ አንቺም እንደዚህ አስበሽ ይሆናል አላልኩም በደፈናው ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን ስገልፅ ነው ይህን ያልኩት፤ ጥፋት ከመሰለሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤" አለ።

"የልብን እየተናገሩ ይቅርታ መጠየቅ አይገባኝም" አልኩት፤ ንዴትና እልህ ጠቅላላ ሰውነቴን አንዘፈዘፈው።

. ብድግ ብዬ እየተቆናጠርኩ ሄጄ ማታ ከተረፈው የወይን ጠጅ በብርጭቆ ሞልቼ ተመለስኩ እግረመንገዴን አንዴ ተጐነጨሁት። የገባሁበትን እልህ እንደሚያበርድልኝ ሁሉ፤ ስበግን ወይ ስደሰት ብርጭቆና ወይን ጠጅ ለምን እንደሚታየኝ አላውቅም። እሱ ይፈልግ እንደሆነ ለምን እንዳልጠየቅሁት ሳትረዱ አትቀሩም።

ቁጭ ብዬ ድጋሚ ተጐነጨሁ፤

"ከግምትሽ በላይ ሆኜ ታይቼሽ ነው ካልከኝ ገደል የሚያክል ስህተት ተሳስተሃል። እኔን ልጅትን ባታውቅ ነው፣ ወይኔ ... ለዚህ በቃሁ" አልኩ።

"የአላልኩትን፤ ምነው ብታዳምጪኝ"

"ምን ቀረህና ነው የምሰማህ? ሌላ ከተማ ተሻግሬ የተዋወቅሁህ ባል አጥቼ ቆሜ የቀረሁ መስዬ ታየሁህ መሰለኝ፤ ወይኔ አለማወቅ፤"

"ለምን እንዳስረዳሽ ዕድል አትሰጪኝም፣"

"ይኸው ናችሁ የኛ ወንዶች። እንዳው ይውጣልህ እንግዲህ እንደዚያ ያደረገኝ በአንተ ስላልተማረኩ ነው፤ I am not attracted to you። ፍርጥ አድርገው ልካችሁን ካልነገሯችሁ አይገባችሁም፤"

"እሱንም እኮ ቀደም ሲል ገምቼው ነበር፤" አለ።

ያበጠው ይፈንዳ በዬ ለእልሄ መወጫ የተናገርኩት ቃል ምንም ስሜት የሰጠው ባለመምሰሉ በሸቅሁ። "አልማረከኸኝም ፤ I am not attracted to you" ስለው ምን ያህል ከሱ የተሻለ እንደማገኝ እንዲረዳልኝ ነበር፤ መሰለኝ።

"ምናልባት ካሰብሽው በላይ ሆኜ ታይቼሽ ይሆናል" ብሎ ለሚያስበው ጥሩ የበቀል እርምጃ ነው። ያኔ እንደዚያ ነበር። ልኩን ማወቅ አለበት።

እኔ ልጂት ስንቱን እንደማንከረባብት ያወቀ አልመሰለኝም። እና የእኔ እንደዚያ ማለት ውስጣዊ እርካታ ሰጠኝ በወቅቱ። በርግጥ ግን እንዳልኩትም ለሱ መማረክ አለመማረኬን ለማወቅ አለመቻሌን ሕልናዬ ያውቀዋል። እሱ እንዳሰበው ከተውኩት ያቺ ኩሩ ልቤ ልትበጠበጥ ነው፤ እጅ ሰጠሁ ማለት ነው። የማላደርገውን! አድርጌ የማላውቀውን! ወንድ ልጅ ልኩን አውቆ በቁጥጥሬ ሥር ሲገባ ማየትን የመሰለ እርካታ የሚሰጠኝ ነገር የለም። ያኔ! ከግምትሽ በላይ ሆንኩብሽ ብሎ የሚያስበውን ቀብራራ ደግሞ ልክ አግብቼ እንዲለማመጠኝ ማድረግ አለብኝ። ችሎታውም ነበረኝና። ታድያ ያቺ በውስጧ አብራ ያደገችው ልበ ኩሩነት ግን ዕድሜዬ ሲያረጅ አብራኝ አላረጀችም። እና ታድያ እንደዚያ ስለው እንዲለማመጠኝም ፈልጌ ሊሆን ይችላል። ብቻ "አልማረክሽኝም" አልኩት። ይህን ስለው ከሱ የጠበቅሁት ነገር ነበር። መለማመጥ፤ እመቤቱ ልሆን እንደምችል ማወቅ። ያሰብኩት ሳይሆን ያላሰብኩት ሆነ። አጅሬ ስሜትም አልሰጠው ጭራሽ በሽሙጥ አስተያየት ያየኝ መሰለኝ። አሁን ተናደድኩ፤ በገንኩ፤ እልሄ ከውስጤ ይትነከነክ ጀመር።

"ሰምተሽኛል አይደል ያልኩትን? አልማረክሽኝም፣ ያሰብኩት ሰው ሆነህ አላገኘሁህም፤" አልኩት ደግሜ፤ ድምፄ መንቀጥቀጡ ይሰማኛል ፤ ከወይን ጠጁ ተጐነጨሁ።

"ሰምቼሻለሁ፤ " አለኝ በረጋ መንፈስ። "ታድያ ይህ እኮ ያለ ነው። እንደተባባልነው ለመሞከር ነበር። ስለዚህ ሞከርን፣ አልሆነም እና የሚያስቆጣ ነገር የለም፤ በፀጋ እንቀበለዋለን።

ዓይኑን ትክ ብዬ አየሁት፤ ምንም የስሜት ለውጥ አላየሁበትም። ለእኔ ያለው ስሜት እንገብግቦት እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል ብሎ አልተለማመጠኝም፤ አላሞካሸኝም፤ ያልኩትን ቃል እንድቀይር አልለመነኝም። ውስጤ በእልህ ተቃጠለ።

ይግረምሽ ብሎ ተነሳና ወደ መኝታ ቤት ሄደ። አልተከተልኩትም። ትንሽ ቆይቶ ሲመለስ ዕቃውን ይዞ ነበር። ዝም ብዬ አየሁት። ስልኩን ብድግ አድርጐ ደወለ። ታክሲ ጠራ።

ዝምታ በዛ፤ ቁጭ አለ። ከአንድ ከሃያ ደቂቃ በኋላ ታክሲው ሲመጣ ዕቃውን ይዞ ወደ በሩ አመራ።

"ስለመስተንግዶሽ አመሰግናለሁ። በይ ደህና ሁኚ፣ ይቅናሽ" ብሎኝ ወጣ።

ደህና ሁን አላልኩትም፤ ከመቀመጫዬም አልተነሳሁም፤ ምንም መልስ አልሰጠሁም፤ እዚያው ቁጭ ብዬ ቀረሁ።

"መሄዱ ነው እንዴ?" አልኩኝ በሆዴ። ተነስቼ በመስኮት ለእፍታ አየሁት።

. . . (በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል፤)



# ዕጣዬ

(ከአብረኸት)

(ካለፈው እትም የቀጠለ)

ሰይፉ እኔነን ወደቤቴ እንድመለስ መፈለጉ ለኔ እንዳሰበልኝ ነው የታየኝ። እወደዋለሁና የሚለውን እሰማለሁ። ቢሆንም ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ብዙ ሞከረ። አንተ እንዳልከው ይሁን ባልኩት በሳምንቱ አባቴ ከሚሠራበት ድርጅት ሄዶ እንደተዋወቀውና አባቴም በጽሞና እንዳነጋገረው ነገረኝ። የአባቴ እንዲሁም የሌሎች ዘመዶቼ በኔ መጥፋት ሻክሮ የነበረው ስሜታቸው እንደታደሰና አባቴም በጣም ደስ እንዳለው፣ እኔንም ለመቀበል ፈቃደኛ እንደሆነ መረዳቱን ገለጸልኝ። ነገር ግን አባቴ ለምን ሰይፉን 'አንተ ምኗ ነህ? እንዴት ልታገኛት በቃህ? ብሎ አለመጠየቁ ገረመኝ። አባቴ በተፈጥሮው ተጠራጣሪ ስለሆነ ወደፊት ያጋጥመኛል ብሎ ለሚፈራው ነገር በቅድሚያ ተዘጋጅቶ ነው የሚጠብቀው። ቢሆንም ሰይፉን ለማስደሰት ስል አንድ እሁድ ቀጠሮ ተያዘና አባቴ ቤት ሰይፉ ይዞኝ ሄደ። ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ ጠበቀኝ። እናቴና እህቴ መጀመሪያ ላይ አኮረፉኝ። እህቴ ስታየኝ እንባዋ ዓይኗን ሞላው። "ሳላይሽ መሄዴ ነበር ያስጨነቀኝ" አለችኝ። አሜሪካ አገር ለመሄድ ፕሮሴሱ እንዳለቀላትና ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደምትሄድ ነገረችኝ። ቤተሰብ በሙሉ በደስታ ተቀበለኝ። ሰይፉንም አመሰጋገኑት። የሄድኩ ዕለት ትዝ ይለኛል ምስ ተበልቶ እንዳበቃ አባቴ ሰይፉን ጠርቶ ተያይዘው ወደ በረንዳው ወጡ። ሃሳብ ገባኝ። ቀልቤ ያለው እዛ እነሱ ጋ ነበርና እቤት ውስጥ ዘመዶቼ ለሚያቀርቡልኝ ጥያቄ የምሰጠው መልስ አጫጭር ነበር። ከአንድ ግማሽ ሰዓት በኋላ ሰይፉ ብቻውን ወደ ቤት ውስጥ ገባ። ፊቱ ተለዋውጧል። ደነገጥኩ። በቀጥታ ወደኔ መጣና የስልክ ወረቀት የጻፈበትን ወረቀት ሰጥቶኝ ደህና ሁኚ ደውይልኝ ብሎ ብቻ ሌሎቹንም ሳይሰናበት ወጥቶ ሄደ። ደነገጥኩና ከተል አልኩት። እደጅ ካይ የቆመውን አባቴን "አመሰኖታለሁ" ብሎ ብቻ እኔ እየጠራሁት ዝም ብሎኝ አጥሩን በር ወጥቶ ሄደ። እንባ ባዘለ ዓይኔ ዞር ብዬ አባቴን ተመለከትኩ።

"ምን ሆኖ ነው?" አልኩት።

'አይነግርሽም ነበር? መቼም ልጅን ላገኘልኝ ሰው ውለታ መክፈል ወንጀል አይደለም፤ ይህ አሁን ምኑ ነው የሚያስቆጣው?" አለኝ።

የተናገረው ነገር ኖሮ እንጂ ልክፈልህ ስላለው ብቻ እንዳልሆነ መንፈሴ ያውዋል።

"ምን ብለሽው ነው? ባክህ ንገረኝ?"አልኩና እንደገና ተማጸንኩት።

"ልጄን ስላገኘህልኝ አመሰግንሃለሁ ብዬ ጉርሻ ብጤ ሰጠሁት፤ ካነሰው አነሰኝ ማለት፤ ከአምስት መቶ ብር በላይ ከፈለገ!" አለኝ።

"በቃሉ የተናገረው ነገር አለ?"አልኩኝ፤ አባቴ ሊደብቀኝ የፈለገው ነገር እንዳለሰውነቴ አውቆታል።

"እሱ ያለው ምን ያደርግላሻል?" አለኝ።

"አንድ ነገር ሳይል አልቀረም፤ እባክህ አባዬ ንገረኝ፤" ብዬ አጥብቄ ተማጠንኩት።

"ትንሽ ደፋር ብጤ ነው። 'እኔ ልጅን ከቤተሰቧ እንድትገናኝ ያደረግሁት ስለምወዳት እንጂ ገንዘብ እንዲከፈለኝ አይደለም' አለኝ። ይህ ደግሞ ትንሽ ድፍረት ነው። ምን ቢሆን ምን እኔ እኮ አባት ነኝ።" አለኝ።

"ምን አልከው ታዲያ?" አልኩት።

"ያልኩት ምን ያደርግልሻል። አባት ስለልጁ ማለት የሚገባውን ብያለሁ። በይ አሁን ቤት ግቢና እረፊ፤ አለኝ።

አባቴ መርዛም ነገር ቢናገረው እንጂ እንዲህ ተናዶ አይሄድም። ስለዚህ ከአባቴ ጋር መከራከሩ የሚበጅ ስላልመሰለኝ ጥዬው ገባው ወደ ውስጥ። ብዙ በተከራከርኩት ቁጥር በሰይፉ ላይ ያለውን ጥላቻ ያጠናክርና በሱ ላይ ተንኮል ከማሰራት ወደ ኋላ እንደማይል ጥርጣሬ ገባኝ፤ አባቴ በገንዘብ ኃይል የማያደርገው ነገር የለምና።

እንደምንም የሆዴን በሆዴ ይዤ ሶስት ቀን ምንም ጥያቄ ሳላነሳ፣ ሰይፉም ጋ ስልክ ሳልደውል እቤት ውስጥ ደስተኛ ለመምሰል ሞከርኩ። የአባቴን መንፈስ ለማረጋጋትና ምናልባትም በሰይፉ ላይ ያሰበው ተንኮል ካለ ያንን እንዲረሳ። በተለይ ደግሞ በቅርቡ አሜሪካ የምትሄደውን ታናሽ እህቴን ሆድ እንዳይብሳት በማሰብም ነበር። በሶስተኛው ቀን ከሰዓት በኋላ ሰው ቤት ውስጥ መኖር አለመኖሩን አረጋግጬ ሰይፉ ጋ በሰጠኝ ስልክ ደወልኩ።

"አልምዬ ጠፋሽብኝ" ሲል ወከክ አልኩ።

"አልጠፋሁም ሰይፍዬ፣ እዚህ ነገር ይብረድ ብዬ ነው።"

"ምነው ችግር ተፈጠረ እንዴ?" አለኝ

"እኔ ምኑን አውቀዋለሁ ብለህ ነው። የዛን ዕለት እንደዚያ ተቆጥተህ የወጣህበትን ምክንያት አባቴም በቅጡ አልነገረኝም፣ ከዚያም ወዲህ የተነሳ ነገር የለም።"

"አልተቆጡሽም አይደለም?" አለኝ በችኮላ።

"አላነሱም፣ እኔም ያን ዕለት አባቴን አንተ ለምን እንደተቆጣህ ከመጠየቅ በስተቀር ነገሩን አላነሳሁም፤" አልኩት።

"አባትሽ ልጄን ስላመጣህልኝ ጉርሻ ብለው ሰጥተውኝ ነበር"

"እሱን ነግሮኛል።

"እኔና አንቺ ደግሞ እንደምንዋደድ ነግርኳቸው።"

"ምናለ ታዲያ እንደዚያ ስትለው?"

"እንደመቆጣትም ሞከሩ፣ 'እሱን እንኳ ገና በልጅነቷ ቃል የገባሁላት የጓደኛዬ ልጅ ስላለ እሱን ተወው' አሉኝና ላስረዳ ስሞክር 'እንዲያውም ልጄን ከቤቷ ያስኮበለልክ አንተ ነህ' አይሉኝም መሰለሽ።

"ምን?" አልኩ፤ ንዴት ከውስጤ ገነፈለች።

ላስረዳቸው ስሞክር ገንዘብ እንደሚጨምሩልኝና እኔም አንቺ አጠገብ እንዳልደርስ ጠየቁኝ። 'ፍቅርን በገንዘብ እንዴት መቀየር ይቻላል?

ስላቸው 'ያደረግሽው ነገር በወንጀል እንደሚያስጠይቅህ አታውቅም?' አሉኝ፤ 'ምን አጥፍቼ' ብላቸው 'ልጄን ከቤቶ አስኮብልለሃል፣ በዚህ ላይ ደግሞ ፀረ አብዮተኛም ሳትሆን የምትቀር አይመስለኝም' ሲሉኝ ሌላው መስማት ስላልፈለግሁ መሄዴን መረጥኩ" አለኝ።

"የምትሠራበትን መሥሪያ ቤት ነገርከው ወይ?" አልኩት በችኮላ።

"አዎ ነግሬአቸዋለሁ፤" አለኝ።

"ስማ ሰይፍዬ እንደነገርኩህ ቀደም ብዬ ባልመለስ ይሻል ነበር። አሁን ከመጣሁ ወዲህም እንደነገርኩኝ ችግር ውስጥ ልንገባ እንችላለን። እንጊህ አንተን ሰምቼ ይህ ሆኗል። አሁን ደግሞ እኔ የምልህን እስቲ ስማኝ" አልኩት።

"ምንድነው?"

"እህቴ በቅርቡ ወደ አሜሪካ ትሄዳለች። እሷ እስከምትሄድ እዚሁ ልቆይ፤ ወር ያህል፤ እስከዚያም የኔና ያንተ ግንኙነት በስልክ ብቻ አልፎ አልፎ ይሁን።"

"ከዚያ በኋላስ?" አለኝ በጉጉት።

"እሱን እንነጋገራለን፣ ለማንኛውም እህቴ የምትሄድ ስለሆነ ብዙ የማነጋግራት ጉዳይ ይኖረኛል፤" አልኩት። ያሰብኩትን ሁሉ ብነግረው ተከራክሮ ሊያፋርስብኝ ይችላል ብዬ ስለፈራሁ አልነገርኩትም፤ እሱም አላስቸገረኝም።

"አንድ ነገር ልጠይቅሽ አልምዬ፤" አለኝ።

"ምንድነውሱ?" አልኩት።

"እውነት አባትሽ እንዳሉት ያጨልሽ ሰው አለ እንዴ?" አለ።

"እኔ እስከማውቀው የለም፤ ውሸቱን ነው፤ ፊት ነግሬሃለሁ ለምን እንዲህ እንዳለህ? አሁን እርሳው እሱን" አልኩት። ስልኩን ዘጋን።

እቤት ውስጥ ጠባዬን ሁሉ ቀየርኩ። ጨዋ ከቤት የማለወጣ፣ ያሉኝን ሁሉ እሺ የምል ሆንኩ። አባቴንም በሁኔታዬ ነገሩን ሁሉ እንዲረሳ ለማድረግ ሞከርኩ። እህቴና እኔ የምንተኛው አንድ ክፍል ውስጥ ስለነበረ ለሷ ሁሉን ነገር አጫወትኳት፤ የደረሰብኝን፣ የሆነውን፣ ፔሌ ቡና ቤት እንደነበርኩ፣ ሰይፉ ያደረገውን ሁሉ ምንም ሳልደብቃት ነገርኳት። የናቴ ልጅ ልብ ብላ ሰማችኝ። እንባዋ በዓይኗ ሞላ፤ ከዚያ ሁሉ መከራ አላቅቆ አሳምኖ ያዳነኝን ሰይፉን በጣም አመሰገነችው፣ ወደደችው። እሷም እንደኔውየተሰማት ነገር ነበር።

"ለመሆኑ እነ አባዬ በተለይ አባዬ ያንቺንና የሰይፉን ግንኙነት እንደማይፈልግ አታውቂም?" አለችኝ።

መቼ አጣሁትና፤ አባዬ ለምን እንደማይፈልግ አውቀዋለሁ። ምክንያቱም ሰይፉ ከኛ ዘር አይደለም። እህቴ ግን የእኔን ከሰይፉ ጋር መዋደድ በፀጋ ነበር የተቀበለችው። "የሚያስብልሽ ከሆነ ይወድሻል ማለት ነው፣ አንቺም ከወደድሽው የምትገናኙበትን ዘዴ መሻት ነው፤ እንዲህ ብለሽ አባባን አስምነው ብለሽ አትሞክሪ፤ እንዲያውም አታንሺበት፤" አለችኝ።

ምናለ ፍቅርን እንኳ ነፃ ቢተውት። ዘር፣ ቀለም፣ የፖለቲካ አመለካከት ምንም ምንም የማይበግረው ኃያል ነገር እንደሆነ እንዴት ሊረዱ አልቻሉም። ይህ ነበር በሁለታችን አዕምሮ የሚመላለሰው። በመጨረሻም እሷ አሜሪካን እንደደረሰች እኔን በቶሎ ለማስወጣት እንደምትችልና እኔ ደግሞ እሱ ከቀደመ ጥሩ፣ ካልሆነ እኔ ተሯሩጬ ላስወጣው በዚህ ከእህቴ ጋር ተስማማ። ተስፋዬ ለመለመ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ቤተሰብ እንዳላስቀይም እህቴ መከረችኝ።

አንድ ወር ሙሉ ከቤት ሳልወጣ፣ እናቴን እያገዝኩ ቆየሁ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሰይፍዬን የማገኘው በስልክ ብቻ በሁለት ወይ በሶስት ቀን አንዴ ነው። እህቴ ለመሄድ አንድ ቀን ሲቀራት እናቴን እመኝታ ቤታችን ጠርታ ዘግታ የኔንና የሰይፉን ሁኔታ ነገረቻት፣ እኔ ባለሁበት። ደግ፣ የዋኋ እናቴ ሰምታ ሰምታ "ያባትሽን ነገር ታውቂው የለ?" ብቻ ነበር መልሷ። እናቴ አባቴን ስለምትፈራው ከሱ ቃል እንደማትወጣ እናውቅ ነበር። ቢሆንም በእህቴ መሄድ ሆዷ የባባ በመሆኑና ከእንግዲህ እዚህ ቀሪ ሴት ልጅዋ እኔ ብቻ በመሆኔ ምናልባት እሷ ትደግፈኝ ይሆናል ብለን በመገመት ነበር። ለማንኛውም ማወቋን አልጠላነውም። ለአባባም ደፍራ እንደማትነግረው እናውቅ ነበር።

እህቴም ሄደች። እኔም ብቻዬን ቀረሁ። በእህቴ መሄድ ቤተሰቡ ለጥቂት ቀናት በዝምታ ተዋጠ። እኔም ሆድ ይብሰኝ ጀመር። እህቴ በሄደች በሳምንቱ አባቴ አንደኛው የመኪና ዕቃ መሸጫ መደብሩ ቀን ቀን እንድሠራ አደረገኝ። ቤት ከመዋል ይሻላል። ባይሻልም ሌላ ምርጫ አልነበረኝም። ጠዋት ከቤት ስንወጣ እሱ ራሱ እዛው ያደርሰኛል። እሱም ከሌሎቹ መደብሮቹ ይልቅ እዚህ ነበር አብዛኛውን የሚውለው። ምሽት ላይ መደብሩ ሲዘጋ እራሱ ይዞኝ እቤት ይመለሳል። ለመቆጣጠርም ያለው እንደሆነ ገባኝ። መደብሩ ውስጥ ዋናው ሥራዬ ዕቃ መሸጥና ገንዘብ መቀበል ነበር። አባቴ አንዳንዴ ወጣ ሲል ወይም ሌሎቹ መደብሮቹ ሲሄድ ሰይፉ ጋ ስልክ እደውላለሁ። ለሰይፉም ከእህቴ ጋር የተመካከርነውን ነገር አሁን ባለሁበት ሁኔታ ላጫውተው አልፈለግሁም። ብቻ በመዋደዳችን አብረን መሆናችን የማይቀር ነገር እንደሆነ እንዲያምንልኝ አደረገሁት። በርግጥ በኔ በኩል ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበርኩ።

"ጊዜ እስኪያልፍ ያለፋልና አይዞአችን" የሚላትን የሰይፉን አባባል የምኞቴ መለምለሚያ መመሪያ ሆነ። ዛሬ እንደልቤ ከሰይፉ አለመገናኘቴ ቢያስጨንቀኝም፣ ሰይፍዬ ቢናፍቀኝም መቻል እንዳለብኝ ተረዳሁ። እሱም እንዲሁ መቻል እንዳለበት ይረዳል። አሁንማ እዚህ መደብር መሥራቴ ተመቸና አባቴ ወጣ ሲል እግሩን ጠብቄ ስልኬን ማንሳት ነው። ድምፁ መጽናኛዬ፣ ቃሉ ተስፋዬ ነው። የፈለገው ኃይል ሊያፈርሰው የማያችለው ኃያሉ ፍቅር በመካከላችን ስላለ ሁለታችንም አንድ ቀን አብረን እንደምንኖር፣ ልጆችም ወልደንእንደምናሳድግ እናውቀዋለን።ይህ በዚህ እንዳለአባቴ እኔን በሌላ ሰው ግንኙነት

ለማጥመድ እንደተዘጋጀ ተረዳሁ። ለዚህም ቢል እዚህ መደብር እንድሠራ ማድረጉ የተሰማኝ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ነበር። ሰውዬው ተከስተ ይባላል። አባቴ ንብረቱ በሆነ በአንድ ጋራዥ ውስጥ የታወቀ መካኒክ ነው። ይኸው መካኒክ የመኪና ዕቃ መለዋወጫ ዕቃ በመውሰድ ሳቢያ እዚህ መደብር መመላለስ የጀመረው እኔ ከመጣሁ በኋላ መሆኑን አወቅሁ። በመጣሁ በሁለተኛ ሳምንት ላይ ነው አባቴ ጋር ይመጡና አባቴ ያስተዋውቀኛል።ልክ ማንኛውንም ሰው እንደሚያስተዋውቅ። የቅርብ ጓደኛው ልጅ እንደሆነና ለጋራዡ ዓይን የሆነ ጐበዝ መካኒክ መሆኑን ደጋግሞ ገለጸልኝ። ከዚያ በኋላ ምናለፋችሁ በቀን ሶስቴ ካልሆነም ሁለቴ ይመላለስ ጀመር። መቼም ይህ ለእድሳት የገባ መኪና ሁሉ በጁ ነው በየጊዜው መኪና እየቀያየረ ይመጣ ጀመር። የሚፈልገውን ዕቃ ይዞ በመሄድ ፋንታ ይቆይና ወሬ ይጀምረኛል። ስለ ትምህርቴ፣ ስለ አብዮት፣ የማያነሳው ነገር የለም። ርዕስ አያጣም። በመጀመሪያ አካባቢ ነገሩ ስላልተከሰተልኝ በቅን መንፈስ በደምብ አነጋግረው ነበር። በኋላ ግን ነገር እየቀየረ ሲመጣ መልሴ ሁሉ አጫጭር መሆን ጀመረ። ነገሩ የገባኝ ትንሽ ቆየት ብሎ ነው። በተለይ እሱ በመጣ ቁጥር አባቴ ጉዳይ አለኝ እያለ ሁለታችንን ለብቻ ትቶ መውጣቱ ሲታወቀኝ። የተከስተን እግር እየጠበቀ የሚመጣ ጉዳይ አልገባ አለኝ። ከዚያም ወደ ቤት ሲወስደኝ ሆነ ጠዋት ወደ ሥራ ሲያሸጣኝ መኪና ውስጥ የሚያወራኝ ስለ ተከስተ ጉብዝና፤ ተከስተ ለሱ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ፤ ምን ዓይነት ጥሩ የተባረከ ሰው እንደሆነ ነበር። እኔ አስተያየት ከመስጠት እቆጠብ ነበር። አባቴ የተከስተን ጉብዝናና ጥሩነት ሲያወራልኝ ከርሞ ከኔ ምንም ዓይነት አስተያየት በማጣቱ በሆነው ባልሆነው እንደ መቆጣትም ይከጃጅለው ጀመር። እሱም ተከስተን ለኔ ባልነት ብቻ ሳይሆን የፈለገው በጥሩ ሁኔታ የሚሠራለትን ሜካኒክ በዝምድና ለመያዝ ነው። ተከስተ በጣም የሚወራለት መካኒክ በመሆኑ ለአባቴ ጋራዥ ብዙ ደምበኞች ማፍራት ዋናው ምክንያት እሱ ነው። እና ዓላማው የኤኮኖሚ ጋብቻ ለመፈጸም ነው። እኔ ልጁን ለሱ ንግድ ሥራ ና የጥቅም ምንጭ ለማድረግ፣ የኔን ውስጣዊ ስሜትና ፍላጐት አለማጤኑ አናደደኝ።

ይህ ሁኔታ እየገረመኝ እያለ ተከስተ እንደተለመደው የምሠራበት መደብር ይመጣል፤ አባቴም ጉዳይ አለኝ ብሎ ወጣ። ተከስተ ኬክ ገዝቶ ነበር የመጣው።

"የኤንሪኮን ኬክትጃለሽ ሲሉኝ ገዝቼልሽ መጣሁ" አለኝና ፈገግ አለ።

ማን እንደነገረው መገመት አላቃተኝም።

"አመሰግናለሁ፤ ድሮ ነበር እንጂ አሁን አልወድም" አልኩት።

"ነውር አይደለም እንዴ?" አለኝ።

"እውነቴን ነው፣ አልፈልግም" አልኩት።

" ሰው ስጦታ ሲያመጣ እንደዚያ አይባልም፤" አለና ኬኩን በመሸጫው ባንኮ ላይ እኔ ወዳለሁበት ገፋ አደረገው።እኔም ዝም ብዬ ባንኮውን ተደግፌ ውጪ ውጪ ማየት ጀመርኩ፤ ከዓይኑ ለመሸሽ ስል።

"ለምንድነው አንቺ እንዲህ የምትሆኚው?" አለ።

"ምን ሆንኩ? አልፈልግም ማለት ወንጀል አለው እንዴ?" አልኩኝ።

"አአይ! እንዳው እኔን ስታይ ቆጣ ቆጣ ትያለሽ፤ ምን ያደረግሁሽ ነገር አለ?" አለ በማስተዛዘን።

"እኔ አልተቆጣሁም፤ አንተ ያደረግኸኝም ነገር የለም፤" አልኩት።

"ፊት ትነሺኛለሽ፤" አለ አሁንም በማሳዘን።

ዝም አልኩት። ከገባው ታዲያ ለምን ያደርቀኛል።

"እሺ የፊታችን ቅዳሜ ሲኒማ ልጋብዝሽ፤" አለኝ፣ ጥያቄ ይሁን ትዕዛዝ አልገባ አለኝ።

"እኔ ሲኒማ አልሄድም፤ ቤተሰቦቼም አይፈቅዱልኝም" አልኩት። የቤተሰቦቼን ነገር ያነሳሁት የሚለውን ልሰማ ነበር።

"ቤተሰብ የት ያውቃል?" አለኝ።

ቱሪስት ብላ አልኩት በሆዴ። " ጋሼ ተከስተ እኔ ሲኒማም ሆነ ኬክ አልፈልግም፤ ምናለ ቢተውኝ" አልኩት እንዲያዝንልኝ በማለሳለስ።

"ጋሼ ማለቱን ደግሞ ብትተይው ደስ ይለኛል" አለ።

በርግጥ እስከዛሬ ስሙን ጠርቼ አላውቅም። ምንም መልስ ሳልሰጠው ጥግ ያለው ወንበር ላይ ሄጄ ቁጭ አልኩ። መጽሐፍ ብጤ አንስቼ ማገላበጥ ጀመርኩ። እንደዘጋሁት ቢገባው ብዬ።

ዓመሉ ነው መሰለኝ፣ ቱግ አለና ኬኩን እዚያው ትቶት ሄደ። ብድግ ብዬ ኬኩን ሁሌ መደብራችን በር አጠገብ ሁሌ ለሚቀመጠው ለማኝ ለመስጠት ይዤው ስወጣ የአባቴ መኪና ከመንገዱ ባሻገር ቆሞ አየሁት። ኬኩን ለለማኙ ሰጥቼ መለስ ስል ተከስተ የአባቴ መኪና ገቢና ውስጥ ቁጭ ብሎ ከአባቴ ጋር ሲያወራ አየሁት።

ይታያችሁ ያለሁበት ሁኔታ። ደነገጥሁ። ትልቅ ነገር እንደሚመጣብኝም ተረዳሁ። ማየቴን እንዳያዩ ቶሎ ብዬ ወደ መደብሩ ገባሁ። አባቴ ሲመጣ የሚመጣብኝን አወቅሁ። ስልኩን በቶሎ አንስቼ ወደ ሰይፉ ደወልኩ። ምን ልለው ፈልጌ እንደደወልኩ አላውቀውም። ብቻ ከሱ ነጥቀው ለማልፈልገው ጭራቅ የሚሰጡኝ መስሎ ታየኝ።

"ስማ ሰይፍዬ ደህና ነህ" አልኩት።

"ደህና ነኝ፤ ምነው ምን ሆነሻል፤ ደምጽሽ ተለወጠብኝ።" አለ።

የሆነውን ልነግረው አልፈለግሁም። ብቻ ድምጹን ሰምቼ መከታ ቢሆነኝ ብዬ ነበር የደወልኩለት።

"ሰይፍዬ ስለናፈቅኸኝ ነው . . ."

"የማነው ሰይፍዬ . . ." አለና አባቴ በቁጣ ስልኩን ከጄ ነጠቀኝ። መምጣቱን አላየሁም ነበር።

"ስማ!" አለ በስልኩ፤ "እዚህ ቤት ሁለተኛ ብትደውል በፖሊስ ነው የማስይዝህ፣ " ብሎ ስልኩን በኃይል ዘጋው። ዞር ብሎ በቁጣ ዓይን አየኝ። ደንግጬ ክው ብዬ ቀረሁ። ተፋጠጥን . . .

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# "እውነትም ጣጤ!"

ሀይሉ ሮበሌ (ከአትላንታ)

ባለፈው ላንዳፍታ መጽሔት ላይ "ላንዳፍታ በሞቅታ" በሚል ርዕስ ሥር ከአትላንታው ጣጤ የጻፈውን ተመልክቻለሁ።

በእውነቱ አቶ ጣጤውን ያበሳጫቸውና ያናደዳቸው የወይዘሪት ትዝታ ሥነ ድሑፍ ሳይሆን ተፈጥሮ የለገሰቻቸው ድንክዬ ቁመት ወይንም የምድር አጫዋች በመሆናቸው መሰለኝ። ያልተረዱት ነገር ቢኖር ግን መለካት ከአንገት በላይ እንጂ ከቁርጭምጭሚቱ ወይም ከመጨሚያው እስከ ራስ ፀጉሩ አለመሆኑን አውቀው ግፋ ቢል ወታደርነት መቀጠር ብቻ ነው የሚቀርብኝ ብለው በተገነዘቡት ነበር አቶ ጣጤው።

እኔ እንኳን አነሳሴ አቶ ጣጤውን ለመዝለፍ ሳይሆን ስንጽፍም ሆነ ስንነጋገር በማህበራዊ ሕይወታችንና በግል ሕይወታችንም ውስጥ ነውርን ነገር ማወቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ነውርን አለማወቅ ደግሞ ምን ያህል ነውረኛ እንደሚያሰኝ ለማስገንዘብ ያህል ነው።

ምክንያቱም አቶ ጣጤው የወይዘሪት ትዝታንና የሌሎችንም ጽሁፍ ለመተቸት ብለው ብዙ ቅሌት ውስጥ የገቡ ይምስለኛል። የወይዘሪት ትዝታን የገጠመኝ ሥነ ጽሁፍ ሲጀምሩ በዚች "ገጠሬ" ካሉ በኋላ የቅሌት መረባቸውን ዘርግተው ሴት ልጅን ወስለት ቀጠፍ በማድረግ አስፈላጊ እንደሆነና እሳቸውም በአቅሚቲ በዚች ቁመታቸው በመወስለት ዝናን ያተረፉ መሆናቸውን ገልፀውልናል። ይቺ ናት ጀግንነት! ለጥቀውም ትዝታ ሐሙስ ሐሙስ ፔኒሲሊን ማግኘት ይገባት ነበር ብለው በጥብቅ ተከራክረዋል። በመጨረሻም ትዝታን ሲሰነባበቱ እስከአሁን ያሉት የትዝታ ወዳጆች ስለማያወጧት እሳቸው ከአሁኑ ሐሙስ ሐሙስ off የሚሆኑበትን አመቻችተው ከትዝታ ጋር ለመገናኘት ሲሆን ይህ ሁሉ ሊሳካ የሚችል ግን ትዝታ ከወደ መቀመጫ ያለውን (consideration) ስታልፍ ብቻ መሆኑን አስጠንቅቋታል።

ከዚህ በኋላ አቶ ጣጤው ወደ ባለትዳሮቹ ነበር ፊረሳቸውን የጫኑት። በባለቤትዋና በእርሷ መካከል በፖለቲካ ምክንያት የተፈጠረውን ችግር አማክሩኝ ብላ ያለችውን ባለትዳር እሳቸው ብድግ ብለው "የእኔ እህት ጣጣ ሳታበዢ መለያየት ከፈለግሽ የራስሽ ጉዳይ" ብሏል እስቲ ምን አገባዎ አቶ ጣጤው? በእኛ ባህል ዋሽቶ ማስታረቅ እንጂ ማጣላት አለመደብን። እርሶ ከየት የመጡ ጉድ ነዎት? ምናልባት እርሶ በዚህ አጥንት በሚሰብር አፍዎ ይሆን ሚስት አጥተው ትዝታን በላንዳፍታ መጽሔት ላይ የቀጠሩዋት? ላንዳፍታ ፒያሳ ያላው የገብረትንሣይ ኬክ ቤት መሰለችዎ እንዴ?

መቸም ጣጤው ጽሑፋቻውን ሲዳመድሙ "ሰው ሁሉ የሚያወራው ሌላ እኔ የሚሰማኝ ሌላ" ብለው እሳቸው ከሰው ሁሉ የተለዩ መሆናቸውን /Admit/ባያረጉ ፣ ኖሮ ጉዳዩ ብዙዎቻችንን ባነጋገረ ነበር።

"ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው" እንደተባለው የአባቶቻችን ተረት ደግሞ ለአገራችን ነፃነትና ያገራችንን የፖለቲካ ችግር በሰላም ለመፍታት የሚጓዙትን እውነተኛ ኢትዮጲያውያንን "ሥልጣን እንዲሁ አይገኝም" "ካይሮ ከመመለስ ይልቅ አዲስ አባ ሄዶ መታሰር ነበር" ብለው ለመተቸት ሞክረዋል። ሚስኪኑ ጣጤ! ቢቻል እኮ እየገደሉ እንጂ እየሞቱ አይደለም ትግል። ካልሆነም በሁለቱም። እየገደሉም እየሞቱም። አቶ ጣጤው ሥልጣንም የሚፈልጉ ይመስላሉ፤ ውጣ ውረድ ባይኖርበት። ስማርትዬ! እሱን እንኳን ይተዉ እባኮትን! "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" ይኼ እርስዎ የማክዶናል /Cheese Burger/ እየገመጡ ለሰዎች እስራትና ስቃይ የሚመኙት ነገር ግን ቢቀርብዎ ይሻላል። ሌላው ደግሞ አቶ ጣጤው የእኛ አገር ፖለቲከኞች ከፈረንጅ ቂጥ ሥር አይወጡም ብለዋል። ኸረ እርሶስ ቢሆኑ የት ነው አሁን ያሉት? "አለው መላ! መላ! ጨዋታን አያውቁም እንዴ እርስዎ? ኸረ የርስዎስ ጉድ አያልቅም መቸም ጉደኛ ነዎት። "ድርቅ ሲመጣ ፈረንጅ አያስፈልግም" ብለውም ተከራክረዋል። እናት ሀገሬ ኢትዮጲያ ስትራብ፣ ሶማሊያ በረሀብ አለንጋ ስትገረፍ፣ የጫፍና የመሀላ አፍሪካ ሀገሮች በረሀብና በበሽታ ሲቆሉ፣ የደረሰላቸው የካረቢያን የጥቁር ሀገሮች፣ ዩጋንዳ፣ ዛየር፣ ኬንያ፣ ናይጀርያ፣ ወይስ እርሶ አሁን እንዲህ የቆጠሩዋቸው የፈረንጅ ሀገሮች ናቸው? እስቲ ይንገሩኝ በሞቴ? ኤዲያ አሁንስ አበዙት አቶ ጣጤው ከምሬ ነው የምልዎት የበሉበትን አይርገጡ Okay!

* ይህንን ጽሑፍ የምታነብ ኢትዮጲያዊ ሁሉ ስትጨርስ ለኢትዮጲያ ነፃነት፣ እኩልነት፣ ዲሞክራሲ የአንድ ደቂቃ ፀሎት አድርግ። ጣጤውም ቢሆኑ! መቼም ጣጤ ነዎት እርስዎ! አይ ጣጤው!



#  የአበው ቅርስ 

## አማርኛ ቅኔ

፩.ቆላ ወርጄ ጥጥ ብዘራ
 አላብብ አለኝ አላፈራ።
 ምንእለብስ ብዬ ሲጨንቀኝ፤
 አፈራለሁ አለኝ።
፪. አንድ በሬ ቢኖር ከበረቴ
 አበያ ሆነ በሀብቴ።
 አላርስ አለ ብጠምደው
 ተው አርጂ ልብላው።
፫. የልጃገረድ አውታታ
 ከአውራ መንገድ ዳር ተኝታ፤
 ተነሽ ተነሽ ምነው
 ይህ ሁሉ አለማፈር ነው።

## ውስጠ ወይራ የቀረርቶ ግጥሞች

፩. በገደል ላይ በሬ እየጠመዳችሁ
 እስቲ መመላሻው እንዳይቸግራችሁ።
፪. ምስለኔው ቀበሮ ጭቃው ሶለግ ውሻ
 ካባታችን አገር አሳጡን መድረሻ።
፫. ጒራው ተለብልቦ ይታያል እሳቱ
 የጒበዝ መነሻው ደረሰ ሰዓቱ።
፬. የሱ ቤት ተከድኖ የኛው ቤት ያፈሳል
 የሱ ማሳ ታርሶ የኛ ዳዋ ለብሷል
 የኛም መሄጃችን የሱም ጊዜው ደርሷል።
፭. ወዲያ ማዶ ሆኖ ብዙ ሰው ተጣራ
 ተው አቤት እንበል ቢደርስም መከራ።

## ምሳሌአዊ አነጋገሮች

፩. ሾላ ፈልፋይ ትል አያጣም።
፪. ሀሰት አያቀላ እውነት አያዳላ።
፫. በቁሙ የከሳ ታሞ አይነሳ
፬. እጅግም ስለት ይቀዳል አፎት
፭. መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች
፮. ብዙ ቧልት ያፈርሳል ንብረት

## እንቆቅልህ? ምን አውቅልህ?

፩. ምን ቢወዱት ወንዝ አያሻግሯት
፪. ሃምሳ ጨፋሪ አንድ በርባሪ

## ተቆጥቶ የሚያስታርቅ ሽማግሌ

በዕለት ጠብ ወይም በቆየ ቂም በቀል የሚፈላለግን ባላጋራ አስታርቆ በሰላም እንዲኖሩ በማድረግ በአገራችን ባህል መሰረት የአገር ሽማግሌዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው። ባለፈው የቡልጋን ሕዝብ እንዳቀረብንላችሁ ዛሬ ደግሞ የቆቱ ሕዝብ ባህላዊ ዳኝነትና የዕርቅ ስርዓትን አቶ ግርማ ገላዬ ከፃፉት ጥናታዊ ፅሁፍና ከብሄረሰቡ አባላት ያገኘነውን አቅርበንላችኋል። ቆቱዎች ኦሮሞዎች ናቸው። በአብዛኛው የሚኖሩትና የሚገኙት በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በባሌና በሐረርጌ ክፍለሃገራት ነው። በቆቱዎች ዘንድ ዳኝነት የሚከናወነው በብሄረሰቡ ባሕላዊ ሕግ መሠረት በሶስት ዳኞች ነው። ዳኞቹ እኩል ስልጣን ያላቸው ሆኖ የሚመረጡትም ከበዳይ ወይም ከተበዳይ ወገን ሳይሆን ገለልተኛ የሆኑ ሽማግሌዎች ናቸው። እነዚህ ሽማግሌዎች አንዴ ከተመረጡ የማይዳኙት ከስልጣናቸው በላይ የሆነ ጉዳይ አይኖርም።

በቆቱዎቹ ባሕላዊ ሕግ መሠረት ማንኛውም ክስም ሆነ አቤቱታ በዳኝነት ለተመረጡ ሽማግሌዎች የሚቀርበው በተበዳይ አማካይነት ሳይሆን በተበዳይ ጎሳ በኩል ነው። የተበደለ ሰው ቢኖር የደረሰበትን ጉዳት ዘርዝሮ ለራሱ ጎሳ ሽማግሌዎች ያሳውቃል። ጉዳዩ የሰው ሕይወት የጠፋበት የነፍስ ግዳይ ከሆነ ለጎሳ ሽማግሌዎች የማሳወቁ ኃላፊነት የሟች የቅርብ ዘመዶች ይሆናል። እንዲሁም ደግሞ የሰው ሕይወት በእጁ የጠፋበት ሰው ውሎ ሳያድር የገደለውን ሰው ስም ጭምር በመንገር ለራሱ ጎሳ ሽማግሌዎች ማሳወቅ አለበት። ይህን ካደረገ ጉዳዩ በሽማግሌዎች እጅ የገባ ስለሆነ ያለአንዳች ስጋት ኑሮውን መቀጠል ይችላል። ይህን ሳያደርግ ቢቀር ወይም ቢዘገይ ግን የሟች ወገኖች ደማቸውን ለመበቀል ሲሉ ሊገሉት ይችላሉ። በፍርድ አሰጣጡ ሂደት ሽምጋዮቹ የነፍስ ግዳይ የተፈፀመበትን ሁኔታ በጥንቃቄ ይመረምራሉ። ሟች የተገደለው በቅድሚያ ሳያውቀውና ራሱንም ለመከላከል ሳይዘጋጅ እንደሆነ ያጣራሉ። ምክንያቱም ሟች ሳያውቅና ራሱንም እንዲከላከል ሳይዘጋጅ ከሆነ የተገደለው ደባ ተፈፅሞበታል ተብሎ ስለሚቆጠር የሚከፈለውም የደም ዋጋ (ጉማ) ከፍ ይላል። ለዚህ ዓይነቱ ግድያ የደም ዋጋ (ጉማ) 150 ከብቶች ይከፈላል። በውሳኔው ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ለማለት አንድ ዕድል ይኖረዋል። በይግባኙ ላይ የሚሰጠው ፍርድ የመጨረሻ ይሆናል። የሰው ሕይወት ባጠፋ ወንጀለኛ ላይ የሚወሰነውን የደም ዋጋ (ጉማ) የመክፈል ባለዕዳነት የገዳዩ

(ወደ ገጽ 43 ይዞራል)

# ባላገርና ፖለቲካ

ባላገር ሲባል በግብርና የሚተዳደረውን ገጠሬ ኢትዮጵያዊ ማለቴ ነው። በአገሩ አፈር ላይ ጎጆ ቀልሶ አፈር ገፍቶ አፈር መስሎ የሚኖረውን። ዳመና ሲዳምን፣ ዝናብ ሲጥልለት እምላኩን ተማምኖ ዘር የሚበትነውን። ዓመት ደክሞ ከአዕዋፍና ከአራዊት ጋር ተካፍሎ እንደነገሩ ኑሮውን የሚገፋውን ኢትዮጵያዊ ማለቴ ነው። ውሃ የለውም፣ መብራት የለውም፣ መንገድ የለውም፣ ትራንስፖርት የለውም።

የከተማውን ቀለብ የሚያመርት የስንዴው፣ የጤፉ፣ የጥራጥሬው ባለቤት ይህ ባላገር ነው። ለቤተመንግስት መኳንንት የሚቀርበው ጮማና ብርንዶ፣ የእነ ጌቶች ምሳ ሙክትና ዶሮው፣ ዕንቁላሉ ጮማውና ክትፎው ከዚሁ የአገሬ ባላገር ድካም ነው የሚገኘው። እነእሜቴ ሙያቸውን የሚያሳዩበት ማርና ቅቤ፣ እነእንኮይት የሚሞናሞኑበት ጠጅና አረቂ፣ የከተማው ኮረዳ የሚገምጠው ፓስቲና ኬክ፣ የእኔ ቢጤው ወስፋቱን የሚሞላበት ፉርኖ ዳቦ የባላገር የድካም ውጤት ነው። የእይብ የወተቱ፣ የእንኮይ የብርቱካኑ አባት ሌላ ማንም አይደለም። ይኼው ባላገር ነው። ባላገር እጁ ጎልዳፋ፣ ፊቱ ወዝ የለው፣ ልብሱ እድፍ ብቻ! ባላገር ትምህርት የለውም። አያነብም፣ አይፅፍም። እንግሊዝኛ አይናገርም አይሰማም፣ የተፈጥሮ ብልህነቱና አርቆ አስተዋይነቱ ግን እጅግ ድንቅ ነው። ሲያጠቁትና ሲንቁት አይወድም። ጥቃትና ንቀት ሞቱ ናት። ፖለቲካ የሚባል አያውቅም። ሹም ያከብራል። ካላስከፉትና ፍርድ ካልገመደሉበት በቀር ልቡ ቂም አይዝም። ባህሪው ግልጽ ነው። እንግዳ አክባሪ ቅንና ገራም ነው። ለባላገር ፖለቲካ ማለት የስድብ ያህል ነው። እከሌ ፖለቲከኛ ነው ቢባል የዋሾ፣ የቀጣፊ፣ የአጭበርባሪ ያህል መታየትን ያስከትላል። ይህ ደግሞ የቡዳ ያህል ከአገር ይለያል። የሚያገባው የሚድረው አያገኝም። ባላገር ሲከፋው ሲበደል ያጉረመርማል። ሲብስበት ማንጎራጎር ይጀምራል። የሚታየው የአገሩ ጫካና ዱር ወንዙና ሸንተረሩ እንጂ ሌላ አገር አያውቅም። ባላገር ቪዛ የለው፤ ፖስፖርት አያውቅ!

የባላጋራውን እከርካሪ ሰብሮ ብድሩን እስኪመልስ ወይም በአገር ሽማግሌ እስኪታረቅ ድረስ ሲያደባና ሲያንጎራጉር ይቆያል። ጎጆዬ ናት ያስጠቃችኝ እያለ ብቻውን ያጉተመትማል እንዲህ እያለ ...

ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ፣
እንደምነሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ።
እህህ እያሉ የበሉት እንጀራ፣
ቀን ይገፋል እንጂ መች ይሆናል ጤና።
ካላጉረመረመ አይበላም አንበሳ፣
ወንድ ልጅ በሬ ነው በደሉን ከረሳ።
ድመትን አይጥ ገደለቻት፣
ወይ ጥቃት ወይ ጥቃት ።

እያለ የደረሰበትን ጥቃት ያሰላስላል። ደግሞ ወዲያው የቀለሳት ጎጆ፣ ሚስቱና ልጆቹ፣ ንብረቱና የአባቱ ቀዬ ሲታወሱት ትንሽ ልታገስ ይሆን በማለት ያቅማማል። ልቡ ለሁለት ይከፈላል።

ዘንድሮስ በልኬ ያሰፋሁት ሱሪ፣
ልሄድ አስቸገረኝ ልቀመጥ ቸገረኝ፣
ቀድጄ ቀድጄ ልጣለው መሰለኝ።
መሄድ መሄድ አለኝ መንኮለል መንኮለል፣
አፌ ባይናገር ልቤ አስቧል ተንኮል።
ዘንድሮስ ሱሪዬን አገለድመዋለሁ፣
ቀን ያገኘሁ ጊዜ እታጠቀዋለሁ።

እያለ ጥቃቱን ለመታገስ ይሞክራል።
ደግሞ ጥቃቱ ሲታሰበው የባላጋራው ንቀት ትዝ ሲለው የልቡ እሳት ይቀጣጠላል።

ሱሪዬ ተቀዶ ከጉልበቴ ላይ፣
ከእንግዲህ ብሰፋው ሱሪ አይሆንም ወይ።
ከአባቴ ባድማ ቢተኛ ያ በሬ፣
ነካክተው ቀስቅሰው አደረጉት እውሬ።
አባቴም እናቴም ሰው ገዳይ ነበሩ፣
እኔን ያፈዘዘኝ ምንድነው ነገሩ።
አረ! ይሄ ጅል ሰው ምንኛ ሰለለኝ፣
ልጅ አሳድጋለሁ ስል ሰምቶኛል መሰለኝ፣
ቤቴ ቤቴ ስል ሰምቶኛል መሰለኝ።
አልበን መጠንሰሻ መውዜር መቀነሻ፣
ይህንን አድርጌ እኔ ጠንስሻለሁ፣
የጠራልኝ እንደሁ እኔ እግትሃለሁ።
አፈጀፈጀ ልቤ እንደ ሙጃ፣
አገሬ መከረሜን ዘንድሮስ እንጃ።

እያለ ልቡ የቆረጠ መሆኑን እያንጎራጎረ ለዘመድ አዝማዱ፣ ለጠላት ለወዳጁ ያሳውቃል። የእርሻ በሬውን ሸጦ ደህና ጠመንጃ ይገዛል። ሁነኛ የአገር ሽማግሌ ካልገባበት ባላጋራውን ገድሎ ከአገር ይወጣል። ዱር ይገባል።

ጥቃቱና በደሉ በመንግስት ሹመኞች በአገሬው ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለ ከሆነ እንጉርጎሮውንና ብሶቱን በየለቅሶው ላይ በሙሾ መልክ፣ በሰርግና በየበዓሉም ላይ በዘፈንና በቀረርቶ ይገልፀዋል።

ለምስለኔው ሙክት ለጭቃ ሹሙ ወጠጤ፣
እንዲህ ሆኜ ነው ወይ በአገር መቀመጤ።

እያለ አልገዛም አሻፈረኝ ለማለት ይቃጣዋል።

በደርግ ዘመነ መንግስት ባላገሩ በግዳጅ ሰፈራ፣ በመንደር ምስረታ፣ በእምራቾች፣ በመዋጮ፣ በማሳ ድልደላው፣ በወታደር ምልመላው በመንግስት ላይ ኩርፊያ ነበረው። ሹመኞችና የራሱ የኮሚቴ ተመራጮች ያሰቃዩት ስለነበር ብዙ ብሶት ነበረው። በመንግስትም ላይ በእጅጉ ቅር ተሰኝቶ ነበር። ባላገሩ እያንዳንዱን የኮሚቴ ተመራጭ ኮሚቴ እያለ ነው የሚጠራው። በጊዜው እንዲህ ተብሏል . . .

ሰላሳ ኮሚቴ ሰላሳ ኮፒ አለው እየለቀለቀ፣
መንግስትም አልሰማ ድሃውም አለቀ።
ስጠው ለኮሚቴ ይጠጣ በፎከት፣
ስጠው ለሊቀመንበር ይጠጣ በፎከት፣

ድምብል ድምብል መሬት ዓይኑ እንዲያይለት።
እኛስ ተወጣነው በመላ በመላ፣
አንዱን ስናጠጣ አንዱን ስናበላ።

ለሊቀመንበሩ ወይም ለኮሚቴ ተመራጮች የሚሰጠው ያጣ አቅም ያነሰው ደግሞ

ለሰባት ኮሚቴ ሰባት ብር አጥቼ፣
ከውሃ ገብ መሬት ቀረሁ ተለይቼ።
ኮሚቴም እጅ አየ እኔም እጅ አጠረኝ፣
ከቦዳው ማሳዬ አሽቀንጥሮ ጣለኝ። ሲል

የደረሰበትን በደል በእንጉርጉሮ ይገልፀዋል።

አንድ ክረምት በጎጃም ክፍለ ሀገር ውስጥ የኮሚቴ ተመራጮች ስብሰባ እያደረጉ ሳለ መብረቅ ወርዶ አንደኛውን ይገለዋል። የኮሚቴው አባላት ማሳ በማከፋፈል አድልኦ ፈፅመዋል ተብሎ አገሬው ቅር ተሰኝቶባቸዋል። በማግስቱ በሟቹ ቀብር ላይ እንዲህ ተባለ:-

ትናንትና ማታ ደግ ዝናብ ጣለ፣
ደጋግሞማ ቢሆን እህል በበላነ።
መቼ እንዲህ ነበር ኮሚቴ ሲቀበር፣
ከላይ ግራር እሾህ ከስር አጣጥ ነበር።

በማለት የወረደው መብረቅ አንጀቱን እንዳራሰውና ደገምገም አድርጎ ሁሉንም ፈጅቶአቸው ቢሆን የማለት ምኞቱን በለቅሶ እንጉርጉሮ ገልጿል።

በ1982 ዓ.ም ኢሕአዴግ በሰሜን ኢትዮጵያ እየተጠናከረ ድል በድል ሲሆን የወደቀው መንግስት ደግሞ በብዛት ወታደር ለመመልመል ታጥቆ ተነስቶ ነበር። ይህን ለማስፈጸም በተለይም በጎጃምና በጎንደር ሹሙ ሁሉ ወደ ገጠር ተሰማርቷል። ባላገሩ ደግሞ ቀድሞውኑ በመንግስት ላይ አኩርፎ ነበርና ተማምሎ አሻፈረኝ ይላል።

የሕዝቡን እምቢተኝነት በሰላ ምላሳቸው ለማለዘብ የፈለጉ አንድ ሹመኛ ሕዝቡን ይሰበስቡታል። ሹመኛው ጥሩ ተናጋሪ ነበሩና ስለአገር መወረር፣ ስለዳር ድንበሯ መደፈር ይዘረዝራሉ። ሕዝቡ ኩርፊያውን ትቶ ከመሃሉ ዘማች መልምሎ እንዲሰጥ "ትኋን ያዘ ተብሎ ቤት አይቃጠልም" ሲሉ ይመክራሉ። ቀድሞውኑ ተማክሮና ተማምሎ የቆየው ባላገር መናኛ መስሎ ሲያዳምጥ ይቆያል። በኋላም አንድ ሽማግሌ ይነሱና

"መቼም ጌታው! እርስዎም ያውቁታል ለአገር ሲባል አባቶቻችን ሲዋደቁ ኖረዋል። እኛም ወደ ኋላ የምንል አይደለንም። ትኋን ያዘ ብለን የምናቃጥለውም ቤት የለንም። እናንተው አፍርሳችሁልናል።"

ብለው የልባቸውን ብሶት ከተናገሩ በኋላ

"ከሆነስ ሆነና ይሄ የምትሉት ወራሪ ጦር ከዬት አገር የመጣ ነው ይባላል?" በማለት በአሽሙር ይጠይቁታል። ነገሩ እናንተው የለኮሳችሁት የእርስ በእርስ ጦርነት ነው ማለታቸው ነበር።

ሁኔታው ያላማረው ሹመኛ ቀስ ብሎ ሹልክ ብሎ ይሄዳል። የመንግስት አቅም እየተዳከመ ሲሄድ በሕዝቡ ላይ ዝርፊያና ጥፋት እንዳይፈፀም ለመከላከል ባላገሩ በየጎጥ በየጎጡ በየቀበሌው በጎበዝ አለቃ መደራጀት ይጀምራል። በየለቅሶውና በየበዓሉ በየሰርጉ ላይ በእንጉርጉሮ፣ በዘፈንና በቀረርቶ አስመስሎ መልዕክት መቀባበል ጀመረ።

ወልቃይት ጠገዴ የወንዶቹ አገር፣
እንሴና እነብሴ ጎንቻ ሣር ምድር።
ሞጣና ብቸና ቆላ ደጋ ዳሞት፣
ቋሪትና ሰከላ ሽኩዳድ ግምጃ ቤት።
ጣሊያን ልጅ አምበራ የጎበዞቹ አገር፣
እናርጅና እናውጋ የአባ ግለጥ አገር፣
ገዥ መጥቶልሃል ዋጋህን ተናገር።
ጋይንት እሪ በል ንገር ለስማዳ፣
ስማዳ እሪ በል ንገረው ለእስቴ፣
እስቴም እሪ በል ንገረው ለሣር ምድር፣
እየከዳ ሄዷል መንግስትና ምድር።

በማለት መንግስት መዳከሙንና አስተዳደሩ መናጋቱን ሥርዓቱ እያለቀለት መሆኑን ሁሉም እንዲያውቅ አመልክቷል። ባላገሩ በደርግ መንግስት፣ በኢሕአዴግና በስልጣን ላይ ባለው የሽግግር መንግሥት ላይ የሰማውን እሮሮ በሚቀጥለው እናቀርባለን።

(ይቀጥላል)

(የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ከኢትዮጵያ ናቸው። ዝግጅታቸው ሲያልቅ ስማቸው ይወጣል።)

## ዋሽቶ የሚያስታርቅ . . .

(ከገጽ 41 የዞረ)

ብቻ ሳይሆን የእርሱ ጎሳ ጭምር ነው። የጎሳው አባላት በሙሉ የደም ዋጋውን የማዋጣትና ከዕዳው ነፃ የመሆን ግዴታ አለባቸው። በሌላ በኩል ለሟች ወገኖች የሚከፈለው የደም ዋጋ የሚሰጠው ለወራሾቹና ለቅርብ ዘመዶቹ ብቻ ሳይሆን እንደየዝምድናው ቅርበት ድርሻቸውን በማበላለጥ ለሁሉም የሟች ጎሳ ነው። ገዳይና ሟች ከአንድ ጎሳ ከሆኑ ጉማውን ማዋጣትም ሆነ መከፋፈል የቅርብ ዘመዶቻቸው ድርሻ ይሆናል። ባላገባች ልጃገረድ ወይም ባል በሌላት ሴት ላይ ምንም ዓይነት የአካል ጉዳት ያደረሰ ሰው ጉዳት ያደረሰባትን ልጃገረድ ወይም ሴት እንዲያገባት ይገደዳል። የአገር ሽማግሌዎች በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነፍስ ገዳዩን ከባለደሙ ጋር አስታርቀው፤ የበደለና የተበደለን አካክሰው ሕዝቡ በሰላም እንዲኖር ያደርጋሉ። ተቆጥቶ የሚያስታርቅ ሽማግሌ እያሳጣን!!

# የግጥም ጉባኤ

## የጥቁር ግሥላ ማንዴላ

ከመሪጌታ ልሣኑ ሥምረት (ሴንትሉዊስ)

ፍትሕ ሲረገጥ የምትፈላ
የፍልሚያ ዘዴ አባ መላ
ሲገርፉህ ወፌይ ላላ
ጥቁር ጅማትህ 'ሚቀላ
ሲረዝም የማትላላ
ሯጭ እንደቢቂላ
ሲያላንሱህ የምትሞላ
ሲቀብሩህ የማትተላ
የጥቁር ግሥላ ማንዴላ።
ሲወግሩህ የምታርግ
የንብ አውራዎች ፍታግ
ፀረሬሲስት ፀረ-ልጋግ
ሲሚንቶ የቋጥኝ ምርግ፤
ፊት ሲነሱህ የማትባባ
ለግሬቭ-ያርድ የማትተባ፤
ሲያበላሹህ የምትቀና
በምግባርህ የምትፀና፤
ሲጠሉህ የማታዳላ
እጅ ልንሳህ አባመላ
የጥቁር ግሥላ ማንዴላ።
የወደፊቱን እንጀ
መጪውን የታሪክ ፍርጃ፤
ያሁኑ የትግል እትብት
የነሶልዘኒስትን አሥራት
ነበልባል የኔግሮ እሳት
የሎስአንጀለስ ቅራት፤
ያልደነበርክ በቱልቱላ
በነቡተሌዚ ኀይላ
በነአጎት ቶም ፈልፈላ
የጥቁር ግሥላ ማንዴላ።
የንክሩማህ አክርማ
የነሉሙምባ እርማ
የነምኒልክ ግርማ፤
የፋኖን የካብራል ኬላ
ያድዋ ማይጨው ቡችላ
የኩሩ ሕዝቦች ናላ
ሲቀብሩህ የማትተላ
አባአፍሪቃ ማንዴላ።
በፌሮ የተቀፈደድክ
በአኮርባጅ የተጠበስክ
ከገደል አፋፍ የተጣልክ
ጎልጎልታ የተቀበርክ፤
መልስህ የተነሳህ
ላንቃምላስ ያልከዳህ
ማንቡር ያልጨመደደህ፤
ሲቀብሩህ የማትተላ
የጥቁር ግሥላ ማንዴላ።
ጨቡዴ ጋዜጠኛ
የጀንጂስካን ጦረኛ
እስመሳይ ተንፋሽ ፈኛ፤
የሊትሬቸር ቪክትማይዘር
የሂፖክራሲ ሁሉ ማዘር፤
ልቦናህን ያላዛገው
ወኔህን ያልሸረሸረው
ቃልህን ያላጠፈው፤
ሲቀብሩህ የማትተላ
የጥቁር ግሥላ ማንዴላ።
የሎንሻርክ ክሬዲት ካርድ
የባህል ሁሉ እንክርዳድ
የጅል እፍያ የምርት ግርድ
ፎረን-ኤይድ ወለድ አግድ፤
ፍንክች ያላስደረገህ
ዓላማህን ያላሳተህ፤
ርካሽ የወሲብ ወግ
የኒው ወርልድ ኦርደር መርግ፤
ሲያልፍ ያልቆነፀለህ
ብላክሜል ያላስከዳህ
ልብህን ያልቦረቦረህ፤
የዕድገት ረድፍህ ተሟላ
ያረመምክበት ትግል ጎላ
ሲቀብሩህ የማትተላ
የጥቁር ግሥላ ማንዴላ።
የይለፍ ካርድህ ተቀደደ
ናዚ በቅናት አበደ፤
የሻርፕቪል ፍሬህ ጐመራ
የታውንሺፕህ መንደር በራ፤
ጎዶሎ ቅምጫናህ ሞላ
ነጭ ታመሰ ተቆላ
እስረኛው አያ ማንዴላ፤
የሕፀፅ ሁሉ ምህላ
የቅርንጫፍ ሁሉ ባላ
እንቀርቃቢ ቶምቦላ
ነራች ባሊጅና ዱላ
ርዕሰ ብሔር ማንዴላ።

# ቢስቁም ባይስቁም



## ወፈፍ እያደረገኝ!


ሞቅ ያለ ትዳር ያለው አንድ ንፉግ (ስስታም) አባ ወራ ዘወትር ዶሮ እያረደ አለሙን ይቀጫል። ታዲያ ዶሮ በታረደ ቁጥር እግር እየጣላቸው የሚስቱ እናት (አማቱ) ይመጣሉ። ይህ ነገር በመደጋገሙ አባ ወራው ይናደዳል። ሚስቱን ለብቻዋ አግኝቶ የሚሰድብበትንም አጋጣሚ ይጠብቃል። አንድ ቀን እንዲሁ ዶሮውን አርዶ ወጣ ብሎ ሲመለስ አማቱ እቤቱ ቁጭ ብለው ያገኛቸዋል። በድንብም ሰላምታ ሳይሰጣቸው ላም ለማለብ ወደ በረት ይገባል። ሚስት ሥራ እያዋከባት ነበርና አማት ቀልጠፍ ብለው ጥጃዋን ሊይዙለት ጠጋ ይላሉ። አባወራውም ጀርባውን እንደሰጠ ጥጃውን ከጡቱ መንጭቆ ለአማቱ ከሰጣቸው በኋላ ልብም ሳይል "አንቺ እኝህ እናትሽ ዶሮ ስናርድ ስናርድ ነው እንዴ የሚመጡት? ይላል" አማትም ደንገጥ ይሉና "ዶሮ ታርዶል እንዴ ልጄ አረ እኔ አላወቅኩኝም" ሲሉት እሱም ይደነግጥና "እሜቴ ኖት እንዴ! እኔ እኮ አንዳንዴ ወፈፍ እያደረገኝ የምናገረውን አላውቅም አላቸው" ይባላል።

## ምቀኛ ሰው

በባሕርይው ምቀኛ የሆነ ሰው አንድ ቀን ሲዘዋወር የእግዚአብሔርን መልዓክ ያገኘዋል። ሰውዬውም መልአኩን በማግኘቱ በደስታ ተውጦ ሲፍነከነክ መልአኩ ተመልክቶት "ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?" ብሎ ይጠይቀዋል። ሰውዬውም በደስታ ብዛት መልአኩ እንዲያደርግለት የሚፈልገው ተምታቶበት ሲያሰላስል መልአኩ ያየውና "ልብ አድርግ። ለአንተ የማደርገውን በእጥፍ ለባልንጀራህ አድርግለታለሁ" ይለዋል። በዚህን ጊዜ ሰውዬው ከሃሳቡ ምልስ ይልና "እንግዲያውስ አንድ ዓይኔን አጥፋልኝ" አለው ይባላል።

## በል ተወው


ሁለት ጥንብዝ ብለው የሰከሩ ጓደኞሞች አልጋ ለመያዝ ወደአንድ አልቤርጎ ይሄዳሉ። የሚፈልጉትን ለአስተናጋጁ ለማስረዳት ተስኗቸው አንደኛው "ገባህ ሁለት ክፍል ያለው አንድ አልጋ እንፈልጋለን" ይላል።
ሁለት አልጋ ያለው ክፍል መጠያቀቸው መሆኑ የገባው አስተናጋጅ ሁለት አልጋ ያለው አንድ ክፍል ይሰጣቸዋል። እነሱም ይገቡና ልብሳቸውን ሳያወልቁ አንዱ አልጋ ላይ ሁለቱም ይወድቃሉ።
ትንሽ እንደቆዩ አንደኛው በእጁ ዳበስ ያደርጋና " ስማ አልጋዬ ላይ ሌላ ሰው ተኝቷል! ይለዋል። ያኛውም ዳበስ ያደርግና "እኔም ጋ ሌላ ሰው አለ!" ይለዋል።
"ገፍትርና ወርውረህ ጣለው! እኔም ልጥለው ነው!" ይለዋል ጓደኛው።
"በል ያዝ እንግዲህ!" ይባባሉና ድብልቅልቅ ያለ ግብ ግብ ሲካሄድ ቆይቶ ጸጥ ይላል።
"የት አባቱንስና! እኔስ ወርውሬ ጣልሁት!" ይለዋል አንደኛው።
"የኔውንስ አልቻልኩትም! እሱ ወርውሮ ጣለኝ!" ይለዋል መሬት የወደቀው።
"በል ተወውና ና ከኔ ጋር ተኛ!" ይለውና እንደገና አብረው ተኙ።

# እ ስ ፖ ር ት



## ከአምና ትዝታዎች



የአምናው ሻምፒዮን የሳንፍራንሲስኮ ቡድን




፪ኛ የወጣው የአትላንታው ቡድን




አምና ያልተሳተፈው የሺካጎ ቡድን

# ጨዋታና ሰንጠረዥ ?

ያለፈው መልስ →





### ወደ ጎን

1. He stayed outdoor
6. very far away
11. worm
14. delinquent
19. he came
23. he talked to
29. honey
31. he sowed on it
36. speech
41. let it get red
45. o.k..
51. actor
57. saying
64. after she considers
68. a tick
71. he became slow
76. he kissed
79. a country in West Africa
81. he hated
85. of the throat
91. by a lucky person
96. Eth. month

### ወደ ታች

1. a town near Mojo
2. fool
4. fresh
6. of your side
7. let her clean
9. of learning
10. let her work hard
15. near
23. he let her eat
32. a distant relative
38. copy
50. knows good recipe
54. he cursed
59. if I calm her
66. if it causes pain
71. he washed
73. he killed
77. herd (for cattle)
88. worn during cold (Eth.)

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለ6 ተከታታይ እትሞች | U.S. | $16.00 | (including postage & handling) |
| | Canada | $22.00 | (including postage & handling) |
| | Europe & Asia | $30.00 | (including postage & handling) |

**የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።**
**በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።**

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ     LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ____________________ STATE __________ ZIP ______________

PHONE ( ________ ) ____________________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይሆን ይጥቀሱ
ከፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ____________________ STATE __________ ZIP ______________


PHONE ( ________ ) ____________________

አባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# ADVERTISE ON LANDAFTA

# በላንዳፍታ ላይ ድርጅቶን ያስተዋውቁ




**ADVERTISMENT ORDER FORM**

I would like to place an advertisment on LANDAFTA.

Name: ____________________

Address: ____________________

City: ____________________

St. ___ Zip: ____________

Phone: ____________________

PLEASE, MARK THE SPACE BELOW TO INDICATE YOUR CHIOCE LIKE THIS (X)

## SINGLE ISSUE RATES

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $200.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $175.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $140.00 |
| ◯ HALF PAGE | $90.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $65.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $50.00 |

## TWO CONSECUTIVE ISSUES RATE

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $350.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $300.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $250.00 |
| ◯ HALF PAGE | $150.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $110.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $90.00 |

ላ
ን
ዳ
ፍ
ታ

Enclosed, please find: 1. A copy of the advertisment to be placed.
2. A check for the amount marked above.

Please, send a copy of the proof before printing. ☐

I Want my ad Translated in Amharic ☐
(no extra fee - please indicate words or phrases to be translated)

For Information, Please Call Advertisment Department:
Publisher at: Phone/Fax (404)728-9122

Please, Send check or money order payable to LANDAFTA along with your order.
LANDAFTA, P.O.Box 49301, Atlanta GA 30359

# MRA'G TRAVEL

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*


ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን



92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305




# ካሊፎርኒያ ማርት በአትላንታ

# CALIFORNIA MART
## IN ATLANTA

2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD
ATLANTA, GA 30324
(404)320-6747

የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች መደብር

| | |
|---|---|
| በርበሬ | እንጀራ |
| ሚጥሚጣ | ጤፍ |
| ቅንጨ | ጌሾ |
| ቡላ ዱቄት | ቡና |
| መከለሻ | እጣን |
| ምስር | የተነጠረ ቅቤ |
| ሽሮ | ተልባ |
| አዋዜ | ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመሞች |

*በተጨማሪ ከትፎ ጥብስ እና ጎረድ ጎረድ እናዘጋጃለን።*

ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን !!

*MAIL ORDER AVAILABLE*
*Please, Call for arrangements*